መስከረም

የማርክሲስት ሌኒኒስት ርዕዮተ ዓለም መጽሔት

ቅጽ 2 ቁጥር 6
መስከረም 1974

መስከረም

ቅጽ 2 ቁጥር 6
መስከረም 1974

የማርክሲስት ሌኒኒስት ርዕዮተ ዓለም መጽሔት

ማ ው ጫ

ገጽ

- የዝግጅት ገፅ - 3

- የጊዜው የፀረ ኮምኒዝም ዋንኛው ገፅታ - - - - - - - - - - - 7
  — ዳንኤል ገ/ኪዳን

- የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም በቀድመ አብዮት ኢትዮጵያ (ክፍል 2) - - - - - - - - - - - - - 28
  — ዶ/ር ለገሠ ለማ

- ምሁርና አብዮታዊ ሚናው (ክፍል 2)
  የኢትዮጵያ ምሁር መደባዊ ጠባይና ሚናው - - - - - - - - - - 53
  — ተስፋዬ ለማ

- የኢትዮጵያ አንድነት ታሪክ፤ በኤርትራ ክፍለ ሃገር የመገንጠል እንቅስቃሴ አነሳስና የደረሰበት ደረጃ (ክፍል 2) - - - - - 68
  — ግርማዬ ገ/የሱስ

— የመስከረም መፅሄት ስድስተኛ እትም ሽፋን ዲዛይን ትርጉም - - - - - - - - - - - - - - - - 96

በኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ

ርዕዮተ ዓለም መምሪያ እየተዘጋጀ በየሦስት ወር የሚወጣ።

አድራሻ

የፖስታ ሣጥን ቁጥር — 80001
የስልክ ቁጥር — 113000

ያለ አብዮቲዊ ንድፈ ሃሳብ
አብዮታዊ እንቅስቃሴ ሊኖር አይችልም !

የርእዮተዓለም ይዘት ፤ እድገትና ሥርጭት

ርዕዮተዓለም ምንድነው ? በኅብረተሰብ እድገት ውስጥ ምን ሚና ይጫወታል ? ከሌሎቹ የንቃተ ሕሊና ፈርጆች ጋር ምን ግንኙነት አለው ? ይዘቱ ምንድነው ? ስርጭቱስ እንደት ነው ? ርዕዮተዓለም ግልፅም ስውርም ቀላልም ከባድም መሆኑን እነዚህን ጥያቄዎች በመመለስ ከማየታችን በፊት በመጀመሪያ ምንነቱን መገንዘብ ይገባናል ።

ርዕዮተዓለም (አይዲዮሎጅ) በታላቁ የሶቭዬት ኢንሳይክሎፒዲያ አተረጓጎም «ሰዎች ርስ በርሳቸውና ከእውነታ ጋር ያላቸውን ግንኙነቶች ፤ ማህበራዊ ችግሮችንና ግጭቶችን የሚገነዘቡበትና የሚገመግሙበት ፤ ማህበራዊ ግንኙነቶችን ለማጠናከር ወይም ለመለወጥ (ለማሳደግ) የሚያስችሉ የማህበራዊ ተግባራዊ ግቦችን (መርሀ ግብሮችን) የሚያከናውንበት የአመለካከትና የአስተሳሰብ ቁንብር ነው ።»

ርዕዮተዓለም የአመለካከትና የአስተሳሰብ ቀንብር እንደመሆኑ የማኅበራዊ ንቃተ ሕሊና ፈርጅ ነው ፤ ርዕዮተዓለም የንቃተ ሕሊና ፈርጅ ይሁን እንጅ በመደባዊ ባህርዩ በአጠቃላይነቱ በስፋቱና በጥልቀቱ ከሌሎቹ የማህበራዊ ንቃተ ሕሊና ፈርጆች ይለያል ። ልዩ ልዩዎቹ የማህበራዊ ንቃተሕሊና ፈርጆች ለምሳሌ እንደ ስነ ልቡና፣ (ሳይኮሎጅ) ፍልስፍና ስነ ምግባር ህግ ፖለቲካ ወዘተ . . . ያሉት ርዕዮተዓለምን ሲያንፀባርቁና ተሸካሚው ማስተላለፊያው ሲሆኑ ርዕዮተዓለም ግን የእነዚህ የአመጣጥ የአመሠራረት የአሠራር የአገልግሎት የለውጥ የእድገት ህግጋትን ከመደብ አንፃር ያጠናል ፤ ያቀናብራል ፤ ያጠቃልላል ። ይሁንና ርዕዮተዓለምም ሆነ ሌሎቹ የንቃተ ሕሊና ፈርጆች ታላቆቹ የሳይንሳዊ ሶሻሊዝም መሥራቾች እንደ አረጋገጡት ከኅብረተሰብ ቁሳዊ ሕይወት ከማምረትና የሰውን ፍላጎቶች ለማሟላት ከሚደረገው እንቅስቃሴ የተለየ የራሳቸው ሕልውና ወይም ታሪክ የላቸውም ።

በመደብ በተከፋፈለ ህብረተሰብ የእያንዳንዱ መደብ ሁኔታ፣ ፍላጎት፣ ምኞት ወዘተ . . . ለየቅሉ እንደመሆኑ የልዩ ልዩ መደቦች የአመለካከትና የአስተሳሰብ ቀንብር ወይም ርዕዮተዓለም የተለያየ ይሆናል ። የርእዮተዓለም መደባዊ ክስተትም ከዚሁ የሚመነጭ ነው ። እንደዚህ ሲባል ግን ርእዮተዓለም ሳይንሳዊ አይደለም ፤ በአጠቃላይ የላዕላይ መዋቀር ዘርፎችን ህግጋት አያጠናም ፤ በእነርሱም አማካይነት አይንፀባረቅም ማለት እንዳልሆ መገንዘብ ያስፈልጋል ። የማሌ ርዕዮተዓለም ሳይንሳዊነት በእነሌኒን የተብራራና በሶሻሊስት አብዮቶች ተግባራዊነቱ የተረጋገጠ ስለሆነ ሳይንሳዊነቱ የሚያጠያይቅ አይደለም ።

ርእዮተዓለም የግለሰብ የቀን ተቀን ኑሮ የሚያመነጨው የእምነት ፤ የፍላጎት ፤ የጭንቀትና የቅዠት ድምር ወይም ጥርቀም ሳይሆን ፤ የአንድ መደብ ተጨባጭ የሆነ ማህበራዊ ጥቅም የሚገለፅበት ፤ ፍላጎቱና ምኞቱ የሚንፀባረቅበት ንድፈሃሳባዊ ቀንጅት ያለው የአመለካከትና የአስተሳሰብ ቀንብር ነው ። አንድ መደብ ከሌሎች መደቦች ጋር ያለው ግንኙነት ፤ ስለአለውም ግንኙነት የሚኖረው አመለካከት ስለ ህብረተሰብ ስለ ፍትህ ስለ እኩልነት ስለ ብልፅግና ስለ ተፈጥሮ ወዘተ . . . ያለው አስተሳሰብ በተቀናጀና በተዋሃደ መልኩ የርዕዮተዓለሙ መከሰቻ ይሆናል ።

እያንዳንዱ መደብ የራሱ የሆነ ርእዮተዓለም ለማመንጨት የሚገደድበት ምክንያት ፤ ተፃራሪ መደቦች ባሉበት ስርዓተ ማህበር ሁሉ እያንዳንዱ መደብ ከተጨባጭ ጥቅሙ አንፃር የተለየ ማህበራዊ ቦታ የያዘና የራሱ የሆነ ታሪካዊ ተግባር ያለው በመሆኑ ነው ። እያንዳንዱ አዲስ የገዥ መደብ የተለየ ታሪካዊ ተግባሩን ለማሟላት የበላይነቱን ለማረጋገጥና ጥቅሙን ዘላለማዊ ገፅታ ለማስያዝ የቀድሞውን ገዥ መደብ ርዕዮተዓለም አስወግዶ የራሱን ርዕዮተዓለም ማስፋፋት ይጀምራል ። አዲሱ የገዥ መደብ ርዕዮተዓለሙን በሚያስፋፋበት ጊዜ ቀደም ሲል በነበረው የእድገት ደረጃ ቀስ በቀስ እየተጠራቀመና እየተከማቸ ከመጣው የእውቀትና የሃሳብ ጥርቀም ፤ የአመለካከትና የፅንሰሃሳብ ክምችት የሚስማሙትን በመውሰድ ይገለገልባቸዋል ፤ ይዘቱን በመለወጥ የራሱ ርዕዮተዓለም በነበረው ወይም በቀድሞው ቅርፅና ቃላት ውስጥ ቀስ በቀስ እያሳደገና እያዳበረ ይመጣል ።

ከዚህ በላይ በጥቅል ያስቀመጥነውን ሃሳብ የበለጠ ግልፅ ለማድረግ ለምሳሌ እኩልነት የሚለውን ቃል እንውሰድ ። ይህ ቃል ያዘለው ፅንሰሃሳብ በተለያዩ ሥርዓት ማህበሮች ውስጥ እንደዋንኛ የታሪክ አንቀሳቃሽ ሃሳብ ሆኖ ሲቀርብ ቆይቶአል ። በባሪያ አሳዳሪው ሥርዓተማህበር በመጀመሪያ የምዝብሮችንና የጭቁኖችን ርእዮተዓለም በማንፀባረቅ የተከሰተው የክርስትና ሃይማኖት የእኩልነትን ጥያቄ ያቀረበው ሰው ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት እኩል መሆኑን ለማረጋገጥ ነበር ። በፊውዳሉ ሥርዓት የገዥው መደብ ርዕዮተዓለም ማስተላለፊያ መሣሪያ የሆነው የክርስትና ሃይማኖት ሰው ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት እኩል ቢሆንም የያንዳንዱ ሰው ስፍራ በአርባ ቀን እድሉ የተወሰነ ስለሆነ ሁሉም ከላይ የተሰጠውን በደስታና በፈገግታ አሜን ብሎ መቀበል ይኖርበታል ፤ ጌታንም ጌታ ደሃንም ደሃ አድርጎ የፈጠረው እግዚአብሔር ነውና! ይኸንን ሁኔታ ለመለወጥ መሞከር በፈጣሪ ላይ ማመፅ ስለሆነ የዘላለም ቀጣት ያስከትላል ፤ በዝባዥም ይበዝብዝ ተበዝባዥም ይበዝበዝ የሚለውን ትርጉም ለእኩልነት ለመስጠት ሞክሯል ።

በካፒታሊስቱ ሥርዓተ ማኅበር ፤ የዚህ ሥርዓተ ማህበር አዋላጅ የነበረው የቡርዣ አብዮት የእኩልነትን ጥያቄ ባነሳበት ጊዜ ፤ ያነሳው እድገቱን አፍኖ ይዞበት የነበረውን የፊውዳል የገዥ መደብ የበላይነት በመፃረር ነበር ። ካፒታሊስቱ የፊውዳሉን መደብ የፖለቲካ ሥልጣን ገልብጦ የራሱን የኢኮኖሚና የፖለቲካ የበላይነቱን ባሰፈነበት ወቀት ፤ ግን ፤ ህግ የመደብ ጥቅም ማስከበሪያ መሆኑን በመሸፋፈን ፤ ሰዎች ሁሉ ፤ በመደብ የተከፋፈሉ ቢሆንም ፤ በህግ ፊት እኩል እንደሆኑ አድርጎ መስበክ ጀመረ ። እግዚአብሔርን በህግ የታካው የቡርዣ እኩልነት የቡርዧውን መደብ የእኩልነት ዓለም በመመሥረት ብዝበዛና ጭቀናን ዘላለማዊና ተፈጥሯዊ እንዲሆኑ አድርጎ በማቅረብ ሃሳባዊ ርዕዮተዓለሙን አስፋፍቷል ።

ለወዝአደሩ መደብ ግን እኩልነት እውን የሚሆነው ብዝበዛና ጭቀና ሲያከትምና መደቦች ሲጠፉ ፤ በሳይንስና ቴክኖሎጅ መስፋፋት የምርት ኃይሎች ከፍተኛ እድገት አግኝተው ምርት በብዛትና በዓይነት ለሁሉና ለእያንዳንዱ በበቂ ሁኔታ ሊዳረስ ሲችል ነው ። የወዝአደሩ ርእዮተዓለም የሰዎችን እኩልነት በሚመለከት ጥያቄውን በዚህ መልክ ያቀርበዋል ፤ ተግባራዊ ምላሽ የሚያገኘውም የወዝአደሩ መደብ በማሌ ፓርቲው መሪነት ፣ ሠርቶ አደሮችንና ጭቁን የህብረተሰብ ክፍሎችን አስተባብሮ ለመደቦች መጥፋት በሚያደርገው ትግል ፤ በትግሉም በሚቀዳጀው ድል መሆኑን ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ተንትኖ ያቀርባል ። የነፃነት ፤ የዲሞክራሲ የፍትህ ወዘተ . . . ፅንሰ ሃሳቦችም ከላይ በተመለከተው ሁኔታ በየሥርዓተ ማህበሩ የተነሱ ቢሆንም ይዘታቸው ግን የተለያየ ነው ።

የርእዮተዓለም እድገት በየሥርዓተ ማህበሩ ውስጥ በምርት ሀይሎች እድገትና ቀደም ካለ ጊዜ ጀምሮ በተጠራቀመ አጠቃላይ የእውቀት ክምችት የሚወሰን ሲሆን ሳይንሳዊነቱ ከህብረተሰብ የቁሳዊ ሕይወት እድገት ጋር የተቀራኘ ነው ፤ በዚህም ነው ከዚህ ሁኔታ መሟላት በፊት ሳይንሳዊ የሆነው የወዝአደሩ ርእዮተዓለም ሊከሰት ያልቻለው ። የሶሺያሊስት ርእዮተዓለም መከሰት ከሳይንሳና ቴክኖሎጅ ከምርት ኃይሎች እድገትና ከወዝአደሩ መደብ መጠናከርና ከትግሉ መፋፋም ጋር የተያያዘ ነው ።

የሰው ልጅ በረዥም ዘመን ታሪኩ ስለተፈጥሮም ሆነ ስለህብረተሰብ ያደረጋቸው ሳይንሳዊ ምርምሮች ፤ በካፒታሊስቱ ሥርዓት ዋዜማ በኢኮኖሚ ፤ በፍልስፍናና በተለያዩ የሳይንስ መስኮች የተደረጉ ጥናቶችና ምርምሮች ያስገኙት ከፍተኛ እድገት ፤ በካፒታሊስቱ የምርት ግንኙነት ውስጥ የወዛደሩ መደብ የያዘው የተበዝባዥነት ቦታ ፣ በዚሁም ምክንያት ይኸው መደብ ሊያካሂድ ከተገደደው የመደብ ትግል ጋር ተዳምሮ ለሳይንሳዊው የሶሻሊስት ርእዮተዓለም መከሰት አመቺ ሁኔታን ፈጠረ ።

ማርክስ ፤ ኢንግልስና ሌኒን እንዳመለከቱት የሶሻሊስት ርእዮተዓለም የወዛደሩ መደብ ትግሉን የሚያካሂድበትንና ብሎም ነፃ የሚወጣበትን መንገድ የሚገልፅ ፤ የትግሉንም ዓለምአቀፋዊ ይዘት የሚያሳይ መነፅሩ ነው ። ለሠራተኛው መደብ የማሌ ርእዮተዓለም በፓርቲው መሪነት የንድፈሃሳብ ትጥቁን የሚያጠናክርበት ፤ የመደብ ንቃቱን በማዳበር ከግብታዊ ትግል የሚላቀቀበት ፤ በረዥምና መራራ ትግሉ ታሪካዊ ተልእኮውን የሚያከናውንበት ብቸኛ የተግባር መመሪያው ነው ።

ርዕዮተዓለም እንዴት ይሠራጫል ? እንዴትና በምን መንገድ በሰፊው ሠርቶአደር ሕዝብ ሕሊና ውስጥ ይሰረፃል ? በመሠረቱ የርእዮተዓለም የስርጭት ባህርይ ከራሱ ከርእዮተዓለም ምንነትና ባህርይ ጋር የተያያዘና ከሱም የሚመነጭ ነው ። በላዕላይ መዋቅር የተለያዩ ዘርፎች ወይም ክፍሎች ላይ ከፍተኛ ተፅእኖ ያለው እንደመሆኑ በእነ ዚህ ላይ የበለጠ ያንፀባርቃል ፤ የበለጠ ጎልቶ ይታያል ።

አንደኛው የርዕዮተዓለም ባህርይ በብዙ መንገድ ወይም አቀጣጫ መንፀባረቅ መቻሉ ፤ ሲሆን ፤ በሊላ በኩል ደግሞ የንቃተ ህሊና ልዩ ልዩ ዘርፎች ከመደብ አንፃር የሚ ገዙበትንና የሚመሩበትን ህግጋት የሚመረምር ምንነታቸውንና ባህርያቸውን የሚተነትንና የ እንቅስቃሴያቸውን አቀጣጫ የሚያመለክት ነው። በመጀመሪያው ባህርዩ በየትም ቦታ የምናገኘውና ግንዛቤውም ቀላል ሲሆን በሁለተኛው ባህርዩ የንቃተ ሕሊና ፈርጆች ሕግጋት ጥናት ደግሞ የጥልቀቱና የረቂቅነቱን ገፅታ የሚያመለክት ሲሆን በደንብ ለማወቅና ለመገንዘብ ከፍተኛ ጥረት የሚጠይቅ መሆኑን ያሳየናል ።

ርዕዮተዓለም በላዕላይ መዋቅር ዘርፎች ፤ ፍልስፍና ፤ ሀይማኖት ፤ ስነልቡና ፤ ህግ ስነ መንግሥት ፤ ኪነት ወዘተ . . . ላይ ተፅእኖ ያደርጋል ፤ በእነዚህ ውስጥ ይንፀባረቃል ስንል በእነዚህ በኩል ይተላለፋል ፤ በእነዚህ አማካይነት ይከሰታል ፤ በእነዚህ ተሸካሚነት ይሠራጫል ወዘተ . . . ማለታችን ነው ። ቃልና ድምፅ ልዩ ልዩ ምልክቶች ፤ ቅርጾችና ቁሳቁ ሶች ሀሳቦችንና መልዕክቶችን ለማስተላለፍ የሚያገለግሉትን ያህል ርዕዮተዓለምንም ለማ ሠራጨት ይውላሉ ። በመሠረቱ ሰው ኃሳብን ለማስተላለፍ የሚጠቀምባቸው መንገዶችና ዘዴዎች ሁሉ ለርዕዮተዓለምም ያገለግላሉ ማለት ነው ።

ተወራራሽና የተያያዙ ቢሆኑም የርዕዮተዓለምን ስርጭት ከሶስት አቀጣጫዎች ለመመልከት ይቻላል ። ርዕዮተዓለም በስፋት የሚሠራጭበት መንገድ ወይም ዘዴ ማስሚ ዲያ ድምፅን ቀርፅንና እትምን የሚያጠቃልል ከመሆኑም በላይ በብዙ ሚሊዮን የሚቆ ጠርን ሕዝብ ባንዴ ለማዳረስ የሚችል በመሆኑ «ፕሮፓጋንዳ» በሚል ስያሜ ዛሬ ዓይነተ ኛው የርዕዮተዓለም ማሠራጫ ዘዴ ነው ። በወቅታችን በኢምፔሪያሊዝምና በሶሻሊዝም መካከል የሚካሄደው የርዕዮተዓለም ትግል የተጧጧፈውም በዚህ መልክ ነው ።

ርዕዮተዓለም የሚሠራጭበትና የሚስፋፋበት ሌላው አቀጣጫ ወይም መስክ ትምህርት ሲሆን ከሥር ማለትም ከመዋዕለ ሕፃናት ጀምሮ እስከ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ድረስ ርዕዮተዓለም በራሱና ከሌሎች ትምህርቶች ጋር ተዳብሎ ወይም ከእነዚህ ጋር ተዋህዶ ይሰጣል ። የረቀቀና ጥልቀት ያለው ርዕዮተዓለም የሚስፋፋውና የሚሰራ ጨው በዚህ መስክ ሆኖ እናገኘዋለን ።

ሌላው አቢይ የርዕዮተዓለም መስረጊያና መስፋፊያ አቀጣጫ ባሕል ነው ፤ ባሕል ሰፊና ሁሉን አቀፍ እንደመሆኑ ለርዕዮተዓለም ማስተላለፊያና ማሠራጫ አመቺ መስክ እንደሆነ ይገመታል ። ስነ ጽሑፍ ቲያትር ፣ ኪነት ወዘተ . . . ከባህል ዘርፎች ውስጥ እንደ ዋናዎቹ የርዕዮተዓለም ማሠራጫና ማስፋፊያ ሊቆጠሩ ይችላሉ ።

በአጠቃላይ ፤ እስከ አሁን ለሶሻሊስም ከተደረጉት ትግሎች ታሪክ ፤ ከአንጋፋዎቹ የሶሻሊስት አገሮች ልምድ የምንማረውና የምንገነዘበው ነገር ቢኖር የማሌ ርዕዮተዓለም በወዝአደሩ አብዮትና በአዲሱ መደብ አልባ ሕብረተሰብ ግንባታ ሂደት ውስጥ የወሳኝነት ሚና ያለው መሆኑን ነው ። አሮጌውን ስርዓት የማፈራረሱንና አባጣ ጉርባጣውን የማስ ተካከሉን የተፋፋመ ግብግብ በአሸናፊነት ተወጥቶ ፤ ወደ መደብ አልባው የኮሚኒስት ሕብረተሰብ የሚያደርሰውን በአያሌ ውጣ ውረድ የተሞላውን ውስብስብና ረዥም የግን ባታ ጉዞ አልፎ ከመጨረሻው ግብ ለመድረስ ጠንካራ የማሌ ትጥቅ አማራጭ የለውም ። ይሄንን ሳይንሳዊ ሐቅ በሙጤን ነው ኢሠፓአኮ ያልተከለሰና ያልተበረዘ የማሌ ሳይንስን ለሰ ፊው ሰርቶ አደር ሕዝብ ማሰራጨት ከሁለቱ ዓበይት ዓላማዎቹ ውስጥ እንደ አንዱ አድ ርጐ የወሰደው ።

አብዮታችን ፈር ይዞና ዓላማውን ቀይሶ መራመድ ከጀመረበት ከመስከረም 2 ቀን 1967 ወዲህ የፊውዶ ቡርዣውን መንግሥት ቁንጮ ከሥልጣን በማስወገድ ሕዝባዊ ፖለ ቲካን ለማስፈንና ይህን ሕዝባዊ ፖለቲካም በአዲስ ኢኮኖሚያዊ መሠረት ላይ ለማቆም

የተደረገው እያንዳንዱ ትግል ፤ በዚህ ትግል አንፃር የተጨበጠውም እያንዳንዱ ድል ማርክሳዊውን ሳይንስ ለሕዝባዊው እንቅስቃሴና ለአብዮታዊው ሒደት ብማስጨበጥ ረገድ ከፍተኛ ሚናን የተጫወተ ነው ።

በየጊዜውና በየወቅቱ በተከናወኑት ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ሥራዎች ምክንያት የማርክሲዝም ሥርጭት ሥፋትና ጥልቀትን እያገኘ መጥቶ ዛሬ ሰባተኛውን የአብዮት በአላችንን በምናከብርበት ወቅት የማሌ ግንዛቤ በጥቂት ግለሰቦች ዙርያ ከመወሰን አልፎ ጠቅላላውን ሰፊ ሕዝብ ያቀፈና ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ እየዳበረ በመሄድ ላይ ነው ። ከመራራና ውስብስብ ትግል በኋላ ዛሬ ከደረስንበት የኢሠፓአኮ ሕልውናና በአንድ ማዕከል ያልተከለሰና ያልተበረዘ የማሌን ሳይንስ በሰፊው ሠርቶ አደር ሕዝብ መሀል የማሠራጨቱን ፤ የማሌን ርዕዮተዓለም ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ለማገናዘብና ተግባራዊ ለማድረግ የተደረገው ጥረት ወደፊት በስፋትና በጥልቀት መቀጠል ያለበት መሆኑ ግልጥ ቢሆንም ፤ እስካሁንም የተገኘው ውጤት የማይናቅ መሆኑን ለመገንዘብ እንችላለን ።

ኢሠፓአኮ ሕልውና አግኝቶ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ከጀመረ ገና አንድ ዓመት ያህል ቢሆነውም ፤ በዚህ ጊዜ ውስጥ ለሠርቶ አደሩ ፓርቲ ምስረታ ፤ ለሶሻሊስት ኢኮኖሚ ግንባታና ለጠንካራ ሕዝባዊ የመከላከያ ኃይል መቋቋም ቅድመ ሁኔታና አስፈላጊ የሆነውን የማሌ ርዕዮተዓለም የሚያሰራጭባቸውን ዘዴዎችና መንገዶች እያስፋፋ መጥቷል ።

«የመስከረም» መፅሔት ኢሠፓአኮ የማሌን ሳይንስ ከሚያሰራጭባቸው መድረኮች መካከል አንዱ እንደመሆኑ መጠን ፤ የመጀመሪያው እትሙ ከወጣበት ከመስከረም 1973 ጀምሮ ፤ ርዕዮተዓለሙን ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ በማገናዘብ ለማቅረብ ጥረት አድርጓል ። በመስከረም ወር 1974 «መስከረም» የርዕዮተዓለም መፅሔት እትመት የጀመረበትን አንደኛ ዓመት ያከብራል ። በአንድ ዓመት እድሜውም መፅሔቱ (ይህን እትም ማለትም ቅፅ 2 ቁጥር ስድስትን ሳይጨምር) አራት ቋሚ በየሶስት ወሩ የሚወጡና አንድ ልዩ እትም በአጠቃላይ 5 እትሞችን አውጥቷል ። እነዚህም አምስት እትሞች ፤ የእንግሊዝኛ ትርጉማቸውን ጨምሮ በአጠቃላይ ከ230,000 ሺህ ቅጅዎች በላይ ተባዝተው ተሰራጭተዋል ።

የመስከረም መፅሔት በ1973 ባወጣቸው ተከታታይ እትሞቹ ውስጥ በተለያዩ ርእሶች ላይ ጥናታዊ የሆኑ ጽሑፎችን ማቅረቡ ይታወሳል ። ለወደፊትም ቢሆን ዝግጅቱን በይበልጥ በማጠናከር የማሌን ንድፈ ሀሳብ ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማዋሀድ ፤ የሚወጡ ፅሑፎች ከማሌ ርእዮተዓለም ጋር በይበልጥ የተገናዘቡና መደባዊ አመለካከታቸው የጐለበተ እንዲሆኑ ለማድረግ ጥረት ያደርጋል ።

መስከረም

የማርክሲስት ሌኒኒስት ርዕዮተዓለም መጽሔት

ቅጽ 2 ቁጥር 6
መስከረም 1974

መስከረም

ቅጽ 2 ቁጥር 6
መስከረም 1974

የማርክሲስት ሌኒኒስት ርዕዮተ ዓለም መጽሔት

ማ ው ጫ

ገጽ

● የዝግጅት ገፅ - 3

● የጊዜው የፀረ ኮምኒዝም ዋንኛው ገፅታ - - - - - - - - - - - 7
— ዳንኤል ገ/ኪዳን

● የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም በቀድመ አብዮት
ኢትዮጵያ (ክፍል 2) - - - - - - - - - - - - - - - 28
— ዶ/ር ለገሠ ለማ

● ምሁርና አብዮታዊ ሚናው (ክፍል 2)
የኢትዮጵያ ምሁር መደባዊ ጠባይና ሚናው - - - - - - - - - 53
— ተስፋዬ ለማ

● የኢትዮጵያ አንድነት ታሪክ ፣ በኤርትራ ክፍለ ሃገር የመገንጠል
እንቅስቃሴ አነሳስና የደረሰበት ደረጃ (ክፍል 2) - - - - - 68
— ግርማዬ ገ/የሱስ

— የመስከረም መፅሂት ስድስተኛ እትም ሽፋን
ዲዛይን ትርጉም - - - - - - - - - - - - - - - - - 96

በኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ

ርዕዮተ ዓለም መምሪያ እየተዘጋጀ በየሦስት ወር የሚወጣ ።

አድራሻ

የፖስታ ሣጥን ቁጥር — 80001
የስልክ ቁጥር — 113000

የጊዜው የፀረ ኰምኒዝም ዋንኛው ገፅታ

ዳንኤል ገ/ኪዳን

በአሁኑ ዘመን በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚካሄደው የመደብ ትግል ከፍተኛውን ደረጃ ይዞ የሚገኘው በኢምፔሪያሊዝምና በሶሻሊዝም መካከል ነው ። ትግሉም የሚከሰተው በወታደራዊና በኢኮኖሚ እንደዚሁም የዚህ ጽሑፍ ይዘት በሆነው በርዕዮተዓለም መስክ ነው ። ሶሺያሊስት ሀገሮችና በሶሺያሊዝም ጐዳና በመራመድ ላይ ያሉ ሁሉ ሳይንሳዊ የሆነውን የማሌ ርዕዮተ ዓለም ለማስፋፋት ይታገላሉ ። በአንጻሩ ደግሞ ኢምፔሪያሊዝምና ቡችሎቹ የሚያካሂዱት የርዕዮተዓለም ትግል ያተኮረው በየቦታው እየተስፋፋ የመጣውን የሶሺያሊዝምን ድል ለመቋቋም በመሞከር በሚያካሂዱት የፀረ-ኮሚዩኒዝም ዘመቻ ነው ።

በወዝአደሩ እንቅስቃሴ ውስጥ ሳይንሳዊ ሶሺያሊዝም የቡርዧውን ርዕዮተዓለም ክስረት በማጋለጥ የበላይነቱን ወይም የአጥቂነቱን ቦታ ከተቀዳጀበት ከ19ኛው ክፍለ ዘመን ሁለተኛው አጋማሽ ጀምሮ የቡርዧው ርዕዮተዓለም ይዘት ፀረ-ኮሚዩኒዝም ሆኖአል ። የቡርዧው ርዕዮተዓለም የፀረ ኮሚዩኒዝም ዘመቻውን በተለያየ መልክ ቢያቀርበውም ዓላማው ዞሮ ዞሮ አንድ ነው ። ይኸውም በዓለም አቀፍ ደረጃ ለሶሺያሊዝም የሚካሄደውን ትግል ለማፈንና የዓለም ሕዝቦችን በማወናበድ በፀረ-ሶሻያሊዝም ሰንደቅ ሥር ለማሰለፍ ነው ።

ከታላቁ የጥቅምት ሶሺያሊስት አብዮት በኋላ ደግሞ ቀደም ካለ ጊዜ ጀምሮ የቡርዧው ርዕዮተዓለም ዓይነተኛ መግለጫ የነበረውን ፀረ-ኮሚዩኒዝም ፡ ይዘቱን ሳይሆን ቅርጹን ብቻ በመቀየር ፡ የፀረ-ሶቪዬት ሰንደቅ ይዞ ተነሳ ። በወቅቱም በሶቪዬት ኅብረት መሠረቱን ጥሎ የነበረውን ሶሺያሊዝም ከሥሩ ለመፈንቀል የመላ ዓለም አድሀሮትንና በሶቪዬት ኅብረት ውስጥ የነበሩ ፀረ-አብዮተኞችን በማስተባበር ኢምፔሪያሊዝም የሞት ሽረት ፀረ-አብዮት ትግል አካሄደ ። ዳግመኛም በሁለተኛው ዓለም ጦርነት ወቅት ይኸው ሁኔታ ተደገመ ፤ ሶቪዬት ኅብረት ይዛው በተነሳችው ቀይ የኰሚዩኒስት ሰንደቅ ሥር እስከ መጨረሻው በጽኑነት በመቆምና ይህ ነው የማይባል መስዋዕትነት በመክፈል በአሸና ፊነት ወጣች ። የሶቪዬት ኅብረት ኮሚዩኒስቶችና ሕዝብ ባደረጉት መራራ ትግል በዛ ያሉ የዓለም የሶሺያሊስት ማኅበረሰብ አባል አገሮች ሕልውና ማግኘት እውን ከመሆኑም በላይ ፡ በአሁኑ ጊዜ ሌሎች በዛ ያሉ አገሮች በሶሺያሊዝም የእድገት ጐዳና እንዲጓዙ አመቺ ሁኔታ ፈጥሮላቸዋል ።

ይህ ሁኔታ የኢምፔሪያሊዝምን የተጽእኖ ክልል (Sphere of Influence) በጣም እያጠበበው በመምጣቱ ኢምፔሪያሊዝምን ክፉኛ አስደንግጦታል ፤ የሚይዘውንና የሚጨብጠውን እያጣ እንዲመጣ አድርጎታል ። በአሁኑ ጊዜ የዓለም ሶሺያሊስት ማኅበረሰብ በወታደራዊም ሆነ በኢኮኖሚ ሀይሉ በጣም የተጠናከረና የኢምፔሪያሊዝምን ጥቃት በሁሉም መስክ በሚገባ ለመከላከል የሚችል መሆኑን እራሱ ኢምፔሪያሊዝም በደንብ ተገንዝቦአል ። በመሆኑም የፀረ-ኮሚዩኒዝም ዘመቻውን ፤ የቁጭቱና የንዴቱ ግለት ማሳረፊያ ቦታ ያደረጋቸው ሶሺያሊዝምን ለመገንባት ጥረት የሚያደርጉትን አገሮች ነው ። በነዚህም አገሮች የውስጥ አድሀሪ ኃይሎችን በመርዳትና የወረራ ጦርነቶች በመቀስቀስ ከዚያም አልፎ ባንዳንዶቹ ላይ በቀጥታ የጣልቃ ገብ ጦርነቶችን በመክፈት የአብዮት ቅልበሳ ሙከራውን አካሂዶአል ፤ ለማካሄድም በመዘጋጀት ላይ ይገኛል ።

"Canadian Tribune", Canada

የመርፌውን ዶዝ በዛ አድርገን ብንሰጣትና በይበልጥ ተባባሪ እንድትሆን ብናደርጋትስ

ኢምፔሪያሊዝም ይህ ስልቱ ብዙ ጊዜ የከሸፈበት ቢሆንም ፤ በተለይ በአሁኑ ጊዜ የወታደራዊ ጀብደኝነቱን ይበልጥ ከማባባሱም በተጨማሪ የፕሮፓጋንዳ አውታሮችን በስፋት በመዘርጋት ላይ ይገኛል ። በነዚህ አውታሮቹም አማካይነት በተለይ የሶሻሊስቱን የዕድገት ፈለግ በሚከተሉ አገሮች ውስጥ የፀረ-ኮሚዩኒዝም ቅስቀሳ በማካሄድና የብሔረተኝነት ስሜት እንዲጠናከርባቸው በማድረግ ፤ እነዚህ አገሮች ከሶሺያሊስቱ ማኅበረሰብ በተለይም ደግሞ ከሶቪዬት ኅብረት ጋር ሊኖራቸው የሚገባውን ጠንካራ አንድነት ቀስ በቀስ በማኮላሸት አዳክሞ የሚያካሂዱትን አብዮት ለቅልበሳ ለማመቻቸት የረቀቀ ትግል በማካሄድ ላይ ይገኛል ።

ይህ ጽሑፍ «የጊዜው ፀረ-ኮሚዩኒዝም ዋንኛ ገጽታ» የሆነውን የፀረ-ሶቪዬት አቋም ይዘት ለማጋለጥ ፤ ሶሺያሊዝምን ለመገንባት የሚደረገው ጥረት ከሶሺያሊስት ማኅበረሰብ በተለይም ከሶቪዬት ኅብረት ጋር ጠንካራ የሆነ አንድነትና ግንኙነት ከመፍጠር ጋር ተነጥሎ ሊታይ እንደማይችል ለማሳየት ጥረት ያደርጋል ። በተጨማሪም ይህ ጽሑፍ በተለይ የሶሻሊስቱን የዕድገት ፈለግ በመከተል ላይ ባሉ አገሮች ውስጥ አብዮቱን እንደግፋለን ተራማጅ ወይም ሶሺያሊስቶች ነን የሚሉ ኃይሎች ፀረ-ሶቪዬት አቋም ከያዙ ፀረ ኮሚዩኒስት መሆንና አብዮትን ለቅልበሳ ማመቻቸት መሆኑን ለማሳየት ይሞክራል ። የጊዜው የፀረ ኮሚዩኒዝም ዓይነተኛ መልክ የሆነውን የፀረ ሶቪዬት አቋም ይዘት ከመመርመር በፊት ግን ታሪካዊ አመጣጡን ጠቅለል ባለ መልክ ለማየት መሞከሩ ተገቢ ይሆናል ።

የፀረ ኮሚዩኒዝም ታሪካዊ አመጣጥ በአጭሩ

በአሥራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን የመጀመሪያ አጋማሽ በአውሮፓ የወዝአደሩ ፀረ-ካፒታል ትግል ተፋፍሞ የገዥ መደቦችን (ፊውዳሎችንና ካፒታሊስቶችን) አደናግጦና ግራ አጋብቶ በነበረበት ወቅት በተለይም በ1830ዎቹና 1840ዎቹ ቡርዧዎች ኮሙኒዝምን እንደጭራቅ ፤ እንደጣረሞት ፤ እንደ ፀረ-ሰው ልጅ ወዘተ...... አድርገው የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ ያካሂዱ ጠላቶቻቸውን ይወነጅሉ እንደነበር ካርል ማርክስና ፍሬደሪክ ኤንግልስ በዝነኛው ኮሚዩኒስት ማኒፌስቶ የመጀመሪያው ገጽ ላይ ግልጽ አድርገው አስቀምጠውት ነበር ።

«አንድ መናፍስ ፤ የኮሚዩኒዝም መናፍስ በአውሮፓ ላይ እያንዣበበ ነው ። የአሮጌዋ አውሮፓ ኃያላን ፤ ፓፓውና ዛሩ ሚተርኒክና ጊዞ ፤ የፈረንሳይ ስርነቀሎችና የጀርመን ነጭ ለባሾች ይህንን መናፍስ ለማውደም ተማምለዋል ። . . . የተኛው ተቃዋሚ ፓርቲ ነው ሥልጣን በጨበጡት ተቀናቃኞቹ ኮሚዩኒስት ተብሎ ያልተከሰሰው ? የተኛውስ ተቃዋሚ ፓርቲ ነው በተራው ኮሚዩኒስት የሚለውን ስም ማጥፊያ በቀኝ ወይም በግራ ተቀናቃኞቹ ላይ መልሶ ያልወረወረ?»[1]

የሳይንሳዊው ሶሻሊዝም መሥራቾች የገዥ መደቦች ኮሚዩኒዝምን እንቋሸው አጨልመው ሰይጣናዊ አድርገው እንደ ሚያቀርቡትና እንደሚያጥላሉት በኮሚዩኒስት ማኒፌስቶ መግቢያ ላይ ካስቀመጡ በኋላ በኮሚዩኒስቶች ላይ የሚሰነዝሩትን ክስ ፣ ወንጀል ፣ ወቀሳ አሉባልታ ይጠቁማሉ ።

«ኮሙኒስቶች የግል ሀብትን ለማጥፋት ይፈልጋሉ ፣ ኮሙኒስቶች ቤተሰብን ለማፍረስ ነው የተነሱት ፣ ኮሙኒስቶች እናት ሀገር እና ዘግነት የሚሉትን አስተሳሰቦች ለማስቀረት ይሻሉ ወዘተ . . .»[2] ተብለው በቡርዣዎችና በአፈቀላጤዎቻቸው ይወነጀሉ ነበር ።

ማርክስና ኢንግልስን እንደዚሁም ሌሎት ኮሚዩኒስቶችን በጊዜው የነበሩት የገዥ መደቦች ከአገር አገር ያሳድዷቸው ፣ ያስሩአቸው ፣ ያሰቃዩአቸው ነበር ። የሳይንሳዊ ሶሻሊዝም አስተሳሰባቸው እንዳይስፋፋ ባላቸው ኃይል ሁሉ ተጠቅመው ለማፈን ክፉኛ ተፍጨርጭረዋል ።

እ. ኤ. አ. በ1848 ተቀጣጥሎ እስከ 1850 ድረስ አብዛኞቹን የአውሮፓ አገሮች አጥለቅልቋቸው በነበረው የቡርዧ ዲሞክራሲያዊ አብዮት የወዝአደሩና የኮሚዩኒስቶች ተሳትፎና ሚና ከፍተኛና ግንባር ቀደም ነበር ። ሳይንሳዊ ሶሻሊዝም ተቀነባብሮ ብቅ ያለበትና የልዩ ልዩ አገሮችን ታጋይ ኮሚዩኒስቶች ባንድ ድርጅታዊ መዋቅር ሥር ያሰባሰበው የመጀመሪያው የወዝአደሩ ዓለም አቀፋዊ ድርጅት ማለትም የኮሚዩኒስት ሊግ ለአብዮታዊው እንቅስቃሴ ማዕከላዊ አመራር በመስጠቱ ወዝአደሩ ግንባር ቀደም ሚና በመጫወቱ ቡርዧው ደንግጦና ደንብሮ ስለነበር ከፊውዳሉ ቀሪታ ጋር በመተባበር ኮሚዩኒስቶችን ማሳደድና ወህኒ ቤት ውስጥ ማሰር ጀመረ ። በጀርመን አገር ቍጥራቸው በርከት ያለ የኮሚዩኒስት ሊግ አባሎች በነጭ ለባሽ ፖሊሶች ታድነው ለይስሙላ ለፍርድ ከቀረቡ በኋላ የረዥም ዓመታት የእሥራት ቅጣት ሲወሰንባቸው ማርክስና ኢንግልስ እንደዚሁም ሌሎቹ ኮሚዩኒስቶች ከአገር አገር እንዲሰደዱና እንዲባረሩ ተደርገዋል ።

እነ ሉዊ ናፖሊዮን እነ ቢስማርክ እነ ቲዬር የአሥራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን ሁለተኛ አጋማሽ ቀንደኛ ፀረ-ኮሚዩኒስቶች ነበሩ ። በታሪክ ውስጥ የመጀመሪያው የወዝአደሩ የበላይ ገዥነት የተከሰተበት የፓሪስ ኮሚዩን ከሰባ ሁለት ቀናት በኋላ በአድሀሪያን ርኩስ ኅብረት ሲደመሰስ የቡርዧ ገዥ መደቦች ከ35 ሺህ በላይ ወዝአደሮችንና ሠርቶ አደሮችን እንደ አራሙቻ ጨፈጨፉ ፣ ከዚህ እጥፍ የሚሆኑት ታጋዙ ፣ ታሰሩ ፣ ተሰቀሉ ። አንደኛው ኢንተርናሽናል በመባል ይታወቅ በነበረው ዓለም አቀፍ የሠራተኞች ማኅበር ላይ ጦርነት አወጁ፣ አባላቱንና መሪዎቹን ማሳደድ ፣ ማሰር መግደል ወይም ማስገደል እንደዋና ተግባራቸው አደረጉ ።

የወዝአደሩን የትግል እንቅስቃሴ ለማፈንና በኃይል ለመደምሰስ የተደረገው ሙከራ ሁሉ ሳይሳካ ቀርቶ በኢፀፋው የትግሉ እንቅስቃሴ እየተስፋፋና እየተጠናከረ በመሄዱ የበዝባዥ ገዥ መደቦች ፀረ-ኮሚዩኒዝም በሰርጎ ገቦችና በከሓዎች መከሰት ጀመረ ። በየአገሩና በየቦታው ብቅ ብቅ ማለት በጀመሩት የሶሻል ዲሞክራሲ ፓርቲዎች ውስጥ ወላዋይ ንዑስ ከበርቴዎች ፣ አናርኪስቶች ፣ ጀብደኞቹ ከየአቅጣጫው በመግባት የወዝአደሩን ትግል ማቀዝቀዝና ማዳከም ጀመሩ ። እንደ ነበር ንሽታይን ፣ ሚለራን ፣ ካውስትስኪ ፣ ቫይደማን ፣ ሂልፈርዲንግ ወዘተ...... ያሉት «በፓርላማ ምርጫ ሥልጣን እንጨብጣለን ፣ ወዝአደሩ ለኢኮኖሚው ሁኔታ መሻሻል ብቻ መታገል አለበት» ወዘተ...... በማለት የቡርዧውን ፀረ ኮሚዩኒዝም ተግባራዊ ለማድረግ ሞከሩ ።

እነ ሌኒን የእውነተኛውንና የአብዮታዊውን የማርክሲዝምን ባንዲራ ይዘው በታሪክ መድረክ ላይ ብቅ ያሉት እነዚህን በሁለተኛው ኢንተርናሽናል ውስጥ ሰርገው ገብተው የቡርዧው ፀረ-ኮሚዩኒዝም መሣሪያ የሆኑትን ለመቋቋም ፣ የወዝአደሩን ትግል ለማጠናከርና ወደድል ለመምራት ነበር ። በሩስያ የቦልሼቪክ ፓርቲ መከሰትና መጠናከር ከሌሎቹም በወቅቱ በሶሻል ዲሞክራሲ ፓርቲዎች ሥር ተጠቃልለው የነበሩት አብዮተኛ ኮሚዩኒስቶች ከከሓዎችና በራዦች አመራር መላቀቅና የራሳቸውን ኮሚዩኒስት ፓርቲዎች መመሥረት ከሁሉም በላይ ደግሞ ታላቁ የጥቅምት ሶሻሊስት አብዮት በሩስያ በ1917 መከናወን የቡርዧውን ፀረ-ኮሚዩኒዝም እንቅስቃሴ ግንባሩን መትቶ ወደኋላ መልሶታል ።

ወዝአደሩ ለሶሻሊዝም ብሎም ለኮሚዩኒዝም በሚያደርገው ያላሰለሰና ያላቋረጠ ትግል ድልን እየተቀዳጀ ወደፊት በተራመደና በገፋ ቁጥር የቡርዧው ፀረ-ኮሚዩኒዝም

ጩኸት ይበልጥ አደንቋሪ እየሆነ እንደሚሄድ ከታሪክ መዛግብት ለመገንዘብ ይቻላል ። የፓሪስ ኮሚዩን የወዝአደሩን የበላይ ገዥነት በተጨባጭ ድርጊት ያስመሰከረ ፣ በኮሚዩኒዝም ታሪክ ውስጥ ከፍተኛ ስፍራ የያዘ እንደመሆኑ የቡርዧ መንግሥታትን የሀፍረት ማቅ ያለበስ ነበር ። የቡርዧ ገዥ መደቦች ኮሚዩኑን እንደጭራቅ እንደ ዲያብሎሳዊ ድርጅት አድርገው ለመሳልና ለማቅረብ ሞክረዋል ። ኮሚዩኑ ከወደቀ በኋላ የፀረ-ኮሚዩኒዝም መግለጫቸው አድርገውታል ። እንደዚሁም በሌኒን መሪነት በቦልሼቪክ ፓርቲ ግንባር ቀደምትነት የተመሠረተችውን ሶቪዬት ኅብረትንም የቡርዧ መንግሥታት በጦር ኃይል ለመደምሰስ ያደረጉት ሙከራ ከተመታና የኢኮኖሚ ማዕቀቡም ከከሰረ በኋላ ፣ ሶቪዬት ኅብረትና የተቀሩት ሶሺያሊስት አገሮች በዓለም አቀፍ የትግል መድረክ ላይ የሚጫወቱትን ወሳኝ ሚና ለማቀዝቀዝ ፣ ኢምፔሪያሊዝም ኮሚዩኒዝምን በአጠቃላይ ሶቪዬት ኅብረትን በተለይ የማጥላላት ፣ የማንቋሸሽና አጨልሞ የማቅረብ ዘመቻውን በሰፊው ተያይዘው ።

የሶሻሊዝም ወሳኝ ሚና

ከታላቁ የጥቅምት ሶሺያሊስት አብዮት ውጤቶች መካከል ዋንኛው የዓለም በሁለት ተጻራሪ ጎራዎች መከፋፈል ነው ። ባንድ በኩል አድሀሪውን የምርት ግንኙነት ለማቆየት የሚጥረው የካፒታሊስት ጎራ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ተራማጅ ኅብረተሰብን የሚወክለው የሶሻሊስት ጎራ በታሪክ መድረክ ላይ ብቅ ማለት ነው ። በካፒታልና በሥራ ኃይል መካከል ያለው የካፒታሊዝም ቅራኔ በሶሻሊዝምና በኢምፔሪያሊዝም መካከል የሚካሄደው ትግል መሠረት ነው ። ኢምፔሪያሊዝም በአሁኑ ወቅት ያረጀውና ያበቃለትን የምርት ግንኙነት ለማቆየት በየቦታው የሚገኙትን አድኃሪ ኃይሎች በማቀፍ የሶሻሊዝምን ግፊት ለመቋቋም ጥረት የሚያደርግበት ጊዜ ነው ። ሶሻሊዝም ተራማጅ የኅብረተሰብ እድገትን የሚወክል በመሆኑ ከታላቁ የጥቅምት ሶሻያሊስት አብዮት በኋላ የዘመኑ ዋንኛ ገጽታ በመሆን ላይ ነው ። አዲሱ የታሪክ ወቅት ታላቁ ሌኒን በትክክል እንደአስቀመጠው ወደ ከፍተኛውና የመጨረሻው የእድገት ደረጃ ላይ የደረሰው ካፒታሊዝም አሽቆልቁሎ ወደ ውድቀት የሚሄድበትና በሶሻሊዝም የሚተካበት ወቅት ነው ።

ይህን የዘመኑን ባሕርይ ተግባራዊ ለማድረግ ፀረ-ኢምፔሪያሊስት ትግል የሚያካሂዱ ኃይሎች ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ ። በዚሁም ሶሻሊዝምን የገነቡና ከኢምፔሪያሊዝም ጋር በዓለም አቀፍ ደረጃ በየመስኩ ተፋጠው የሚገኙ ጠንካራ ፀረ-ኢምፔሪያሊስት አቋም ያላቸው ፣ በመሠረቱት ጠንካራ ኢኮኖሚና የወታደራዊ ኃይል ኢምፔሪያሊዝም እንደ ቀድሞው እንደፈለገው እንዳይፏልል እንቅፋት የሆኑትና በምሣሌነታቸው የዓለምን ሕዝብ አብዮታዊ ስሜት በመቀስቀስ ላይ የሚገኙት የሶሻሊስት አገሮች ፣ በአሁኑ ዘመን ካሉት አብዮታዊ ኃይሎች መካከል ዋንኞቹ ናቸው ።

ኢምፔሪያሊዝምን በገዛ «ቤቱ» በማዳከምና ለሰላም ፣ ለዲሞክራሲና ለሕዝቦች ነፃነት የሚታገሉትና የሚዋጉት የኢምፔሪያሊስት አገሮች የሠራተኛና ዲሞክራሲያዊ እንቅስቃሴዎችም ሌላው የዓለም አብዮታዊ ኃይሎች አካል ናቸው ። እነዚህ ኃይሎች ኢምፔሪያሊዝምን አፍንጫው ሥር ሆነው ሰፊ ተቃውሞ በማድረግ ሊወስዳቸው ከሚችል ብዙ እርምጃዎች እንዲታገድ ያደርጉታል ። ለምሳሌ በአሜሪካና በሌሎች የአውሮፓ አገሮች ለፀረ-ቬትናም ጦርነት ፣ ለፀረ-ኒዩትሮን ቦንብ ለዓለም ሰላም በመደረግ ላይ ያሉት ሰልፎችና እንቅስቃሴዎች የዚሁ የዓለም አቀፍ ፀረ-ኢምፔሪያሊስት ትግል አካል ናቸው ። በካፒታሊስት አገሮች የሚገኘው የሠራተኛው እንቅስቃሴ የሚካሄደው ፀረ ሞኖፖሊ ትግል ኢምፔሪያሊዝምን በማዳከም በዚሁ በፀረ-ኢምፔሪያሊስት ትግል ውስጥ ሰፊ ሥፍራ ይዞ ይገኛል ።

ኢምፔሪያሊዝም ቀደም ሲል በቀጥተኛ ቅኝ አገዛዝ ቀጥሎም በእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ አብዛኞቹን ኋላቀር አገሮች በመበዝበዝና በመጨቆን ላይ ይገኛል ። ኢምፔሪያሊዝም ኋላቀር አገሮችን በራሱ ተጽእኖ ሥር አስገብቶ ለራሱ ጥቅም ተገዥ እንዲሆኑ በማድረግ ለዕድገታቸው እንቅፋት ሆኗል ። ለዕድገታቸው የሚያደርጉትን ትግል ያፍናል ። ኢምፔሪያሊዝም ታዛዦቹን በሥልጣን ላይ በማስቀመጥ የታዳጊ አገሮች ሕዝቦች ካለባቸው ባሕላዊና ማቴሪያላዊ ኋላቀርነት በአፋጣኝ ለመላቀቅ የሚችሉት የሶሻሊስት አገሮችን ምሳሌነት በመከተል ካፒታሊስታዊ ባልሆነ የዕድገት ጎዳና አማካይነት ሶሺያሊዝምን ሲገነቡ መሆኑን በመረዳት ላይ ናቸው።ይህ ግንዛቤአቸውም ጠንካራ ፀረ-ኢምፔሪያሊስት አቋም ይዘው ከዓለም አብዮታዊ ኃይሎች ጎን በመሰለፍ የዚሁ እንቅስቃሴ አንድ አካል እንዲሆኑ እያደረጋቸው ነው ።

በ«መስከረም» መጽሔት ቅጽ 1 ቍጥር 1 ላይ እንደተገለጸው «በዚህ ፀረ-ኢምፔሪያሊስት ትግል ውስጥ አብረው የተሰለፉት ኃይሎች የሚፈጥሩት ትብብርና ኅብረት በጣም አስፈላጊ ነው ። እነዚህ ኃይሎች በመደብ ንቃታቸው ፣ በድርጅት ጥንካሬያቸውና በትግል ልምዳቸው የተለያዩ ቢሆንም በሚያደርጉት ፀረ-አድኅሮትና ፀረ-ኢምፔሪያሊስት ትግል ከተለያዩ ማኅበራዊና ብሔራዊ ጭቆናዎች ለመላቀቅ በሚያደርጉት እንቅስቃሴ በአንድነት የተሳሰሩና የጋራ ጥቅም ያላቸው ናቸው ። እርስ በራሱ በተያያዘ ሁኔታ ዓለምን በሙሉ አብዮታዊ በሆነ መንገድ ለመለወጥና ለሰው ልጅ ዕድገት ለማስገኘት የየበኩላቸውን አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ። ይህ ሁኔታ የበለጠ እንዲደራጁና ጥብቅ ግንኙነት እንዲፈጥሩ ያደርጋቸዋል ።»[3]

በአጠቃላይ በአሁኑ ወቅት በዓለም አቀፍ የኮሚዩኒስት እንቅስቃሴ ውስጥ የሚሳተፉት አብዮታዊ ኃይሎች ማለትም የሶሻሊስት አገሮች ፣ በካፒታሊስት አገሮች የሚገኙ የኮሚዩኒስትና የሠራተኞች እንቅስቃሴና በኋላቀር አገሮች ለብሔራዊ አርነትና ለሶሺያሊዝም ትግል የሚደረጉ ኃይሎች ናቸው ። በመካከላቸውም የመተባበርና የመረዳዳት ግዴታ እንዳለባቸው ግልጽ ቢሆንም በዚሁ ትግል ውስጥ ዋንኛው ኃይል የዓለም ሶሻሊስት ሥርዓት ነው ።

ቀደም ብለን እንደተመለከትነው ከ 1917 ታላቁ የጥቅምት ሶሻሊስት አብዮት በፊት የነበረው ትግል በሁለት ርዕዮተ ዓለሞች መካከል የሚደረግ ትግል ነበር ። ይህም በዓለም ካፒታሊስት ሥርዓት ጠንካራ ኃይል የሚደገፈው የቡርዧ ርዕዮተ ዓለምና የኅብረተሰብ ዕድገትን ለማሳየት የሚችል ሳይንሳዊ ቲዮሪ በነበረው ነገር ግን በሥልጣን ላይ የወጣ የሶሻሊስት መንግሥት ድጋፍ ያልነበረው ኮሚዩኒዝም ወይም የወዛደሩ ርዕዮተዓለም ትግሉ በካፒታሊዝምና በሶሻሊዝም መካከል ያለው ትግል አካል ሆነ ። ከዚሁ ጊዜ በኋላ ማርክሲዝም ሌኒኒዝም ድጋፍና ጥንካሬ የሚያገኝበት በተጨባጭ ያለሶሻሊስት ሥርዓት አገኘ ።»[4]

የመጀመሪያዋ የሶሻሊስት አገር የሆነችው የሶቪዬት ኅብረት ምንም እንኳን ከአብዮቱ በኋላ ብዙ የኢምፔሪያሊዝም ጣልቃ ገብ ወረራዎችና የፀረ-አብዮት እንቅስቃሴዎች ቢያጋጥማትም ፣ ማንም ሌላ ሥርዓት ሊቋቋመው በማይችል መንገድ ፈተናውን ተወጣዋለች ። በሁለተኛው ዓለም ጦርነት ወቅት የሶቪዬት ኅብረት በፋሺስት ጀርመን ላይ ያገኘችው ድል ወታደራዊ ብቻ ሳይሆን ርዕዮተዓለማዊም ድል ነበር ። በአገር ውስጥ በተደረገው ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ለውጥም ውስብስብና ከባድ የሆኑ የኅብረተሰቡን ችግሮች በመፍታት ሶሻሊዝም በካፒታሊዝም ላይ ያለውን ታሪካዊ የበላይነት አስመስክሮአዋል ።

ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በኋላ በርከት ያሉ አገሮች በሶሻሊስት ጎራ ውስጥ በመታቀፋቸው የሶሻሊስቱ ሰፈር ጠንካራ ኃይል ሆነ ። ይህ ሁኔታና የዓለም ምዝብሮችና ጭቁኖች ለነፃነትና ለእኩልነት የሚያደርጉት ትግል ሶሻሊዝም የሰው ልጅ በሞላ የሚከተለው የዕድገት ጎዳና መሆኑን በተግባር ከማሳየታቸውም በላይ ማርክሲዝም ሌኒኒዝም መጭውን የኅብረተሰብ እድገት በትክክል ለማየት የሚያስችል ሳይንስ መሆኑን አረጋገጡ ። ይህ ከታላቁ የጥቅምት ሶሺያሊስት አብዮት በኋላና በተለይም ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በኋላ የተገኘው ድል በሁሉም መስኮች ሶሻሊዝም በካፒታሊዝም ላይ ያለውን የበላይነት እያረጋገጠ መጣ ።

የሶሻሊስት ሥርዓት ለመጀመሪያ ጊዜ ከኢኮኖሚ ቀውሶች ነፃ የሆነ ፣ ኢኮኖሚው በየጊዜው እያደገ የሚሄድ ፣ ዕውነተኛ ነፃነት ያለበትና ለመጭው ጊዜ ብሩህ ተስፋ የሚታይበት መሆኑን ለማረጋገጥ ተቻለ ። የሶሻሊስት አገሮች ማኅበራዊ ምርት ፈጣን ዕድገት እያሳየ በሜሄድ ላይ ከመሆኑም በላይ የኅብረተሰቡ ባሕላዊና ማቴሪያላዊ የኑሮ ደረጃ በየጊዜው ዕድገት እያሳየ ነው ። እነዚህ አገሮች በሕዝቦቻቸው መካከል በወንድማማችነትና በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ጠንካራ አንድነት መሥርተዋል ። አዲሱን ሶሺያሊስታዊ ሰው በመፍጠርም የኅብረተሰቡን የመፍጠር ችሎታ አሳድገዋል ።

በሶሻሊዝም የሰዎች ቦታ የሚወሰነው በማኅበራዊ ተሳትፎአቸው በሥራቸው ፣ በግል ችሎታቸውና በሕዝባዊ ብቃታቸው እንጂ በሀብታቸው አለመሆኑ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሰዎች ማኅበራዊ አስተዋጽኦቻቸውንና ችሎታቸውን የሚያሳዩበትና የሚጠቀሙበትን ሁኔታ ይፈጥራሉ ። ካፒታሊዝም ለሰው ልጅ የሞራል ውድቀትን የሚያንናጽፍ ፣ መጭውን ሕይወቱን በጥርጣሬ ላይ የሚጥል ሲሆን ፣ ሶሻሊዝም ግን የሰው ልጅ ስለመጭው ጊዜ ግልጽና ብሩህ ተስፋ

እንዲኖረው የሚያደርግና ለእድገቱ ሰፊ
ዕድል የሚሰጥ ፣ ጤናማ የሆነ ሥነ ምግባር
እንዲኖረው በማድረግም ግለኝነትንና ስግ
ብግብነትን የሚያጠፋ ነው ። በጣም አነስ
ተኛ ከሆኑት የጨቋኝና የበዝባዥ መደቦች
አባላት ሥልጣኑን ነጥቆ ለሰፊው ሕዝብ
በማድረግ ፣ የኢኮኖሚ ተቋሞች የሀብት
ምንጮችን ለሰፊው ሕዝብ ንብረትነት በማ
ዛወር የአገሪቱን ሀብት የሕዝብ ሀብት
ያደርገዋል ። መደቦችን በማጥፋትና የሰ
ዎችን እኩልነት በማረጋገጥ ለሰው ልጅ
መሠረታዊ መብትና ነፃነት ዋስትና ይሰ
ጣል ፣ የብሔሮችን እኩልነትም ያረጋግ
ጣል ። ሕዝባዊና መንግሥታዊ አስተዳደ
ሮችን መምራት የተወሰኑ በዝባዥ መደቦች
አባላት መብት ሳይሆን የሰፊው ሕዝብ መ
ብት መሆኑን በማረጋገጥ ሰፊው ሕዝብ በሕ
ዝባዊ ድርጅቶቹ አማካይነት ራሱን በራሱ
እንዲያስተዳድር ሰፊ መድረክ ይከፍትለ
ታል ። በተጨማሪም አንድ ሕዝብ ካለበት
ኢኮኖሚያዊና ባሕላዊ ኋላቀርነት በአፋ
ጣኝ ሊላቀቅና፣የተደላደለና የተሟላ እድገት
ሊቀዳጅ የሚችለውና የኅብረተሰቡ ማኅበ
ራዊና ፖለቲካዊ ችግሮችም ሊፈቱ የሚች
ሉት በሶሻሊዝም አማካይነት ብቻ መሆኑን
የሶሻሊስት አገሮች በተግባር አስመስክረ
ዋል ። የገበሬው የመሬት ጥያቄ ፣ የሴቶች
እኩልነት ፣ እኩልነትና ዲሞክራሲ የሚረ
ጋገጠውም በሶሻሊዝም ብቻ መሆኑ በገ
ሀድ ታይቷል ።

የሶሻሊስት ሥርዓት ባገኛቸው ድሎችና
በየጊዜው በሚያሳየው እድገት ለዓለም
ሕዝብ አብዮታዊ ምሣሌ ሆኗል ። ይህ በብዙ
መስዋእትነት በሶሻሊዝም የተገኙት ታላ
ላቅ ድሎች ሕዝቦች ለመብታቸውና ለነፃ
ነታቸው እንዲታገሉ እየገፋፉቸው ነው ።
የሶሻሊስት ሥርዓት በኢኮኖሚው ግንባታ
ሂደት ውስጥ ያጋጠሙትን ችግሮች በየጊ
ዜው በመፍታት በአሁኑ ጊዜ የሶሻሊስት
ግንባታ ለሚያካሂዱ አገሮችና ሕዝቦች ት
ልቅ ልምድና ትምህርት በመስጠት ላይ
ነው ። ይህ ልምዱና ትምህርቱም በአሁኑ
ጊዜ ተመሳሳይ ስህተቶች እንዳይፈጸሙ ፣
የሶሺያሊዝምን መፍትሔነት የተቀበሉ አገ
ሮች ከሶሺያሊስት አገሮች የትግል ልምድ
ተምረው ግንባታቸውን እንዲያጠናክሩ አ
መቺ መንገድ ከፍቷል ።

ኢምፔሪያሊዝም ሶሻሊዝምን ለመደ
ምሰስና ለማጥፋት ባለመቻሉ የሶሺያሊስ
ትን ሥርዓት ለማጥላላት ከፍተኛ የፕሮፓ
ጋንዳ ጦርነት ካወጀ ውሎ አድሮአል ።

በአሁኑ ጊዜ ሶሻሊዝም በየቦታው በአሸና
ፊነት በመውጣቱም ሆነ የሶቪዬት ኅብረትና
ሌሎች ሶሻሊስት አገሮች በደረሱበት ከፍ
ተኛ የኢኮኖሚ እድገትና ወታደራዊ ኃይል
የተነሣ ኢምፔሪያሊዝም ዛሬ እንዳሻው በተ
ለያዩ አገሮች የውስጥ ጉዳይ ግልጽ ጣልቃ
ገብነት ከመፈጸም እንዲቆጠብ ተደርጓል ።
በዓለም አቀፍ ደረጃ የኃይል ሚዛኑ ለሶሻሊ
ዝም እያደላ በመሄድ ላይ በመሆኑ ኢምፔ
ሪያሊዝም ዓላማውን ለማሟላት እንቅፋት
ስላጋጠመው በአሁኑ ጊዜ ከመናኛ የፕሮፓ
ጋንዳ ጦርነትም በተጨማሪ አዲስ የዓለም
ጦርነት ለማስነሳት ጠብ በመጫር ላይ
ይገኛል ። የሶሺያሊስት አገሮችን አብዮ
ታዊ ምሳሌነት ለመቀነስ በጦር መሣሪያ
እሽቅድምድምና የጦርነት አዝማሚያዎችን
በማሳደግ የኢኮኖሚ እድገታቸውን ለመኀ
ተት ጥረት እያደረገ ነው ። ኢምፔሪያሊዝም
በአሁኑ ጊዜ የሶሻሊስት ሥርዓትን ከአዳ
ከመ የበላይነቱ ሙሉ በሙሉ እንደሚረጋ
ገጥ ፣ ዓለም አቀፍ ብዝበዛውን ያለምንም
ተቃውሞ ለማራመድ እንደሚችል ስለሚገነ
ዘብ የፀረ-ሶሺያሊዝም ትግሉ ዋና ትኩረቱ
በሶሻሊስት አገሮች ላይ አርፎአል ። ለዚህም
ነው በአሁኑ ጊዜ ያለው ቅራኔ ግልጽ በሆነ
መንገድ በሶሻሊዝምና በኢምፔሪያሊዝም
መካከል እየሆነ የመጣው ።

የሶሻሊስት አገሮች ኢምፔሪያሊዝምን
መቋቋም መቻላቸው ብቻ ሳይሆን ለቀሩት
አብዮታዊ ኃይሎች የሞራል ፣ ዲፕሎማቲክ ፣
ወታደራዊና ኢኮኖሚያዊ እርዳታ በመስ
ጠትም ትልቅ ሚና ይጫወታሉ ። የሶሻ
ሊስት አገሮች በገነቡት ጠንካራ ኢኮኖሚ
ያዊና ወታደራዊ ኃይል አማካይነት ኢምፔ
ሪያሊዝም ፀረ-አብዮት ድርጊቱን በየቦታው
እንዳሰኘው እንዳያስፋፋ ለመቋቋም በመቻ
ላቸው ፣ ዛሬ በዓለም አቀፍ ደረጃ ፀረ
ኢምፔሪያሊስት ኃይሎች ለትግላቸው አ
መቺ ሁኔታዎች እንዲፈጠርላቸው አድር
ገዋል ። ኢምፔሪያሊዝም በሰላም አብሮ
የመኖርን ፖሊሲና ዴታንትን ለመቀበል
የተገደደውም በሶሻሊስት አገሮች ጥንካ
ሬና በሰላም ወዳድ ሕዝቦች ትግል ነው ።
የሶሻሊስት አገሮች መኖር ኢምፔሪያሊዝም
በፈለገው መንገድ ፍላጎቱን በተጽእኖ መ
ልክ በፈለገው ቦታና ጊዜ ሊፈጽም የማይ
ችልበት ደረጃ ላይ ስላደረሰው የፀረ-ኢምፔ
ሪያሊስት ትግል ለሚያካሂዱ ኋላቀር አገ
ሮችና በካፒታሊስት አገሮች ለሚገኙ ሠራ
ተኞች ከፍተኛ እርዳታ ነው ።

የሶሻሊስት አገሮች ማርክሳዊ ሌኒናዊ
ለሆነው የወዛደሩ ዓለምአቀፋዊነት መ

ርህ ታማኝ በመሆን ለአብዮታዊ ኃይሎች ብዙ የማቴሪያል እርዳታ በመስጠት ላይ ናቸው ። ሶቪዬት ኅብረትና ሌሎች ሶሻሊስት አገሮች በአብዮታዊ እንቅስቃሴ ውስጥ የሚገኙትንና የሶሻሊስት የእድገት ፈለግ ለሚከተሉ ሕዝቦች አብዮታዊ ድሎቻቸውን ለመጠበቅና ለማጠናከር እንዲችሉ መከላከያ ኃይላቸውንና ኢኮኖሚያቸውን የሚያጠናክሩበት እርዳታ ይሰጣሉ ። ለብሔራዊ ነፃነታቸው መገኘት ከቅኝ ገዥዎች ጋር ባደረጉት መራራ ትግል ኮርያ ፣ አልጀሪያ ፣ ቪዬትናም ፣ አንጎላ ፣ ሞዛምቢክና ፣ ሌሎች አገሮችም ድል ለመቀዳጀት የቻሉት የሶሻሊስት አገሮች በሰጧቸው የተለያየ እርዳታ አማካይነት ነው ። አብዮታቸው በፀረ-አብዮት ኃይሎችና በውጭ ጣልቃ ገቦች የተጠቃና የቅልበሳ አደጋ የደረሰባቸው አገሮች ፣ ለምሳሌ አንጎላ ፣ ኢትዮጵያ ፣ ኩባና ቪዬትናም የውጭ ወራሪ ኃይሎችን ለመቋቋም የቻሉት አሁንም ሶቪዬት ኅብረትና ሌሎች ሶሻሊስት አገሮች በሰጧቸው ወታደራዊ ዕርዳታ ነው ። ይህ ወታደራዊ ዕርዳታ አብዮት በማካሄድ ላይ ላሉ አገሮች አብዮታቸው ራሱን ለመከላከል እንዲችል በማድረግ ኢምፔሪያሊዝም በነዚህ ሀገሮች በመካሄድ ላይ የሚገኙ አብዮቶችን ለመቀልበስ የማይችልበት ሁኔታ እንዲፈጠር አድርጓል ። በአጠቃላይ በአሁኑ ጊዜ የሶሺያሊስት ሥርዓትን የመሠረቱ የምሥራቅ አውሮፓ አገሮች ፣ የኩባ ፣ የኮሪያና የቪዬትናም ወዘተ...... አብዮቶች በአሸናፊነት ሊወጡ የቻሉት የሶቪዬት ኅብረትን ድጋፍ በማግኘታቸው ነው ። የቻይናም ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት በ1949 በአሸናፊነት ሊወጣ የቻለው የሶቪዬት ኅብረት ዕርዳታ ስለነበረው መሆኑ አይካድም ። በአጠቃላይ ቀደም ሲል ሶሻሊዝምን የገነባና በአሁኑ ጊዜም ለመገንባት የሚታገል ማናቸውም አገር አለ ሶቪዬት ኅብረት ዕርዳታ ዓላማውን ተጨባጭ ለማድረግ የማይችል መሆኑ ታሪክ እራሱ ምስክር ከመሆኑም በላይ አሁኑም በተጨባጭ እየታየ ነው ።

የሶሻሊስት አገሮች በአብዮታዊ ሂደት ውስጥ ለሚገኙት ኋላቀር አገሮች በሚሰጧቸው የኢኮኖሚ ዕርዳታ አማካይነት ከኢምፔሪያሊዝም ተጽእኖ ለመላቀቅና የኢኮኖሚ ነፃነት እንዲቀዳጁ እየረዳቸው ነው ። ሶቪዬት ኅብረትና ሌሎቹ ሶሺያሊስት አገሮች በሚሰጡት ሰፊ ዕርዳታ እየተጠቀሙ ኋላቀር አገሮች ብሔራዊ ኢኮኖሚያቸውን በመገንባት ላይ ይገኛሉ ። የሶሺያሊስት አገሮች በሚሰጡት እርዳታና ከእነርሱ ጋር በሚፈጠረው የኢኮኖሚ ግንኙነት አማካይነት የኢምፔሪያሊዝም የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ እየተዳከመ ነው ። ከሶሻሊስት አገሮች ጋር የሚፈጠረው የንግድና ኢኮኖሚያዊ ልውውጥ ለረዥም ጊዜ ፣ ቋሚና ለሁለቱም ወገኖች በሚጠቅም መንገድ የሚከናወን ነው ። ኋላቀር አገሮች በዚሁ ትብብር አማካይነት የሚገኘው ምርትና ሀብት ሙሉ ተጠቃሚ ይሆናሉ ። የሶሺያሊስት አገሮች አብዛኛው የኢኮኖሚ ዕርዳታው ኋላቀር አገሮች መሠረታዊ የሆኑ ዘመናዊ ኢንዱስትሪዎች አቋቁመው የምርቱና የትርፉ ብቸኛ ተጠቃሚ እንዲሆኑ እንጂ እነሱ የተለየ ጥቅም የሚያገኙበት ስላልሆነ ለኋላቀር አገሮች እድገት አስተዋጽኦ ያደርጋል ። ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በኋላ የተከሰቱ ሶሺያሊስት አገሮች በአሁኑ ጊዜ የደረሱበት ከፍተኛ የኢኮኖሚ የእድገት ደረጃ ለዚህ ቋሚ ምስክር ነው ።

ለኢኮኖሚ ግንባታው የሰለጠነ የሰው ኃይል ትልቅ ሚና የሚጫወት መሆኑ አይካድም ። ሶቪዬት ኅብረትና ሌሎች ሶሻሊስት አገሮች በአብዮታዊ ሂደት ውስጥ ለሚገኙት አገሮች ብዙ ምሁራንን በማሠልጠን የሚሰጡት ዕርዳታ በቀላሉ የሚታይ አይደለም ። በተለይ ኋላቀር አገሮች ተፈላጊ የሰው ኃይል እጥረት በየሥራ መስኩ የሚታይባቸው በመሆኑ ለወጣቶቻቸው ነፃ የትምህርት ዕድል በመስጠት በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ምሁራን አሰልጥኖ በመላክ የሰው ሀይል እጥረት እንዲቃለል የሶሻሊስት አገሮች ብዙ ዕርዳታ ይሰጣሉ ። በሌሊ አንጻር ኢምፔሪያሊስቶች ከኋላቀር ሀገሮች የሰለጠነ የሰው ኃይል በመዝረፍ ምን ያህል ጥቅም እንደሚያገኙ ማመዛዘኑ ጠቃሚ ይሆናል ።

በተጨማሪ በአሁኑ ዘመን ለሕዝባዊ አብዮቶች ድል መምታት የሕሊናዊ ሁኔታዎች መሟላት ሊታለፍ የማይችል ነገር ነው ። የሶቪዬት ኅብረት ኮሚዩኒስት ፓርቲና ሌሎች የሶሻሊስት አገሮች ፓርቲዎች ለፀረ-ኢምፔሪያሊስት ኃይሎች ተፈላጊ አብዮታዊ ካድሬዎች በማሠልጠን ለአብዮታዊ እንቅስቃሴው መጠናከር የሚሰጡት ዕርዳታ ትልቅ ግምት የሚሰጠው ነው ። ኋላቀር አገሮች የፓርቲ አሠራር ልምድ ስለሚጎድላቸው በእንደነዚህ ያለ ኅብረተሰብ ውስጥ የሰፊው ሕዝብ ርዕዮተዓለማዊ ንቃት ዝቅተኛ በመሆኑ ፣ በፓርቲዎቻቸው ውስጥ በበቂ መጠን የነቁና ቆራጥነት ያላቸው አባላት ቊጥር አነስተኛ በመሆኑ ፣ የሶሻሊስት አገር ፓርቲዎች ይህንን ድክመት

ለማስወገድ ትልቅ እርዳታ ይሰጣሉ ። የእነ
ዚህ አገር አብዮታዊያን ወደ ሶሻሊስት
አገሮች በመሄድ በተግባር ሶሻሊዝም በምን
ደረጃ ላይ እንዳለ እንዲያዩ ፤ የፓርቲዎቹን
ታሪክ እንዲያጠኑ በማድረግ ከትምህርታዊ
ልውውጥ ልምድ እንዲያገኙና የማርክሲ
ዝም ሌኒኒዝም ንድፈሀሣብን በደንብ ተም
ረው በየአገሮቻቸው ተመልሰው ትክክለኛ
ሳይንሳዊ አመራር ለመስጠት ብቁ እንዲ
ሆኑ ያስለጥናቸዋል ። ለአብዮቱ ድል የግድ
አስፈላጊ የሆነውን የሕሊናዊ ሁኔታ ለማ
ሟላት ጥራት ያላቸውና በበቂ መጠን የሚ
ገኙ ካድሬዎች መገኘት አስፈላጊ በመ
ሆኑ ፤ በዚህ አንጻር የሶሻሊስት አገሮች ከፍ
ተኛ አስተዋጽኦ በማበርከት ላይ ይገኛሉ ።

ስለዚህም የሶሻሊስት አገሮች በአብዮ
ታዊ ምሳሌነታቸው ፤ በሁሉም መስክ በተ
ቀዳጁት ጥንካሬና ድል አማካይነት ኢምፔ
ሪያሊዝምን መቋቋም መቻላቸው ፤ ለዓለም
አብዮታዊ ኃይሎች በሚሰጡት የተለያየ ዕር
ዳታ ፤ ፊት ለፊት ኢምፔሪያሊዝምን በመ
ጋፈጥ ለዓለም አብዮታዊ ኃይሎች መከታና
ለአብዮታቸው ድል መምታት ዋስትና በመ
ሆን በአሁኑ ጊዜ የፀረ-ኢምፔሪያሊስት
ትግሉ መሪ ኃይልና ወሳኝ ሚና የሚጫ
ወቱ ሆነዋል ። ለዚህም ነው እ. ኤ. አ.
በ1969 በሞስኮ የተደረገው የኮሚዩኒስትና
የሠራተኛ ፓርቲዎች ስብሰባ ፤ «የዓለም
ሶሺያሊስት ሥርዓት የፀረ-ኢምፔሪያሊስት
ትግሉ ወሳኝ ኃይል ነው ፤» በማለት በአ
ወጣው መግለጫ ላይ በግልጽ የአስቀ
መጠው ።

የፀረ ኮሚዩኒዝም የትግል መልኮች

ፀረ-ኮሚዩኒዝም በአሁኑ ጊዜ የካፒታ
ሊስት ሥርዓትን ዕድሜ ለማራዘምና የዓለም
ሕዝቦችን አብዮታዊ እንቅስቃሴን ለመግ
ታት ቡርዧው የሚጠቀምበት መሣሪያ ነው።
ፀረ-ኮሚዩኒዝም አስፈላጊነቱና ታዳጊነቱ
ያበቃለትን የቡርዧ መደብ የበላይ ገዥነት
ለማቆየት ኢምፔሪያሊዝምና አድህሮት የሚ
ጠቀሙበት የቡርዧ ርዕዮተዓለም ነው ።
የቡርዧ ርዕዮተዓለም የካፒታሊስቱ ኅብረተ
ሰብም ሆነ የሰው ልጅ ያጋጠሙትን ችግሮች
ለመፍታት ከማይችልበት ደረጃ ላይ ደር
ሷል ። በመሆኑም የቡርዧ ርዕዮተዓለም
ተራማጅና ሳይንሳዊ የሆነውን የወዝአደሩን
ርዕዮተዓለም ለመቋቋምና ለመወዳደር የማ
ይችል መሆኑ በግልጽ እየታየ ነው ። ከዚ
ህም የተነሣ የቡርዧ ርዕዮተዓለም ቢአፍ
ራሽነትና በመከላከል ደረጃ ላይ ይገኛል ።
የቡርዧ ርዕዮተዓለም የሰው ልጅ ላሉበት
ችግሮች ገንቢ የሆኑ መፍትሔዎች ለመስ
ጠት ባለመቻሉ አፍራሽ በሆነ መንገድ
የማርክሲስት ሌኒኒስት ፓርቲዎችንና የሶሻ
ሊስት ሥርዓትን (ማለትም የሰው ልጅ ያሉ
ትን ችግሮች ለመፍታት የሚችሉትና በመ
ፍታት ላይም ያሉትን ኃይሎች) በማንቋ
ሸሽ ፤ በማጥላላትና መሠረተቢስ አሉባልታ
ዎች ላይ ብቻ እንዲያተኩር ተገዷል ።
ይህ ሁኔታ ባንድ በኩል የቡርዧ ርዕዮተ
ዓለምን ዝቅጠትና ውድቀት የሚያሳይ
ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የወዝአደሩን ርዕ
ዮተዓለም ኃያልነትና ታሪካዊ የበላይነቱን
ከቡርዧው ርዕዮተዓለም የተረከበ መሆኑን
ያመለክታል ።[5]

ፀረ-ኮሚዩኒዝም የአብዮታዊ ኃይሎችን
እድገት ለመግታት ፤ የሶሻሊዝምን ግንባታ
ለመገደብ ዋና መሣሪያ ሆኖ በመቅረቡ ፤
በአሁኑ ጊዜ ማንኛውም የአድኅሮት ኃይል
የፀረ-ኮሚዩኒዝም ባሕርይ ይዞ በመውጣት
ላይ ይገኛል ። የወቅቱ ፀረ-ኮሚዩኒዝም
ሦስት የተያያዙ ግቦች እንዳሉት ለመገን
ዘብ ይቻላል ። 1. በዓለም አብዮታዊ ሂደት
ውስጥ በግንባር ቀደምትነት በመጓዝ ላይ
ያሉትን የሶሻሊስት አብዮት ድል ያደረገባ
ቸውን የሶሻሊስት አገሮች ለመከፋፈልና
ለማዳከም ፤ 2. በካፒታሊስት አገሮች ውስጥ
ለዲሞክራሲና ለሶሻሊዝም የሚደረገውን
የትግል እንቅስቃሴ ማፈንና 3. ኋላቀር
አገሮች የኢምፔሪያሊዝምን የብዝበዛና የጭ
ቆና ቀንበር በመስባበር የሶሺያሊስቱን የእ
ድገት ፈለግ ተከተለው ሶሻሊዝምን እንዳ
ይገነቡ መቋቋምና መዋጋት ናቸው ።[6]

ኢምፔሪያሊዝም ይህን የፀረ-ኮሚዩኒ
ዝም ትግሉን በሁለት መንገዶች ያካሂዳል ።
አንደኛው ግልጽ የሆነ ጣልቃ ገብ ወረራና
ጦርነት ማካሄድ ነው ። ለዚህም ምሳሌ
ቀደም ብለን የጠቀስነው ሶቬዬት ኅብረት
እንደተመሠረተች በጦር ኃይል ለመደም
ሰስና አድህሪውን ስርዓት መልሶ ለማቋቋም
የተደረገው ሙከራ ነው ። ሌላው መንገድ
ደግሞ የኤኮኖሚና የፕሮፓጋንዳ ጦርነት
ነው ። ለምሳሌ ያህል በሶቬዬት ኅብረትና
በሌሎች ሶሻሊስት አገሮች ላይ ተጥሎ የነ
በረው የኢኮኖሚ ማዕቀብ ፤ ቀዝቃዛው ጦር
ነት ፤ በሶሻሊስት አገሮች የውስጥ ጉዳይ
ጣልቃ መግባት እነ ሲ. አይ. ኤን በመሳ
ሰሉት ፀረ-ሕዝብ ድርጅቶች የሚቀነባበሩ
የውስጥ ቡርቦራዎች «የአሜሪካን ድምጽ» ፤
«የነፃነት ሬዲዮ» ፤ «የነፃይቱ አውሮፓ
ሬዲዮ ፤ ወዘተ..... በተሰኙ ሬዲዮ ጣቢያዎች

ፀረ-ኮሚዩኒስት የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ ማካሄድ ይገኙበታል ።

በጦር መሣሪያ በመጠቀም የኮሚዩኒዝምን መስፋፋት ለመዋጋት ኢ.ምፔሪያሊዝም በቬይትናም ፣ በላኦስና በካምፑቺያ ሕዝቦች ላይ ያካሄደው ግልጽ ወረራ የዚህ የፀረ ኮሚዩኒዝም ትግል አካል ነው ። የቺሊን ሕዝብ አብዮታዊ እንቅስቃሴ ለማፈን በ ቺሊ ውስጥ ጣልቃ በመግባት እ. ኤ. አ. በ1973 በኢ.ምፔሪያሊዝም የተቀነባበረው ወታደራዊ መፈንቅለ መንግሥት ፣ በጽዮናዊት እሥራኤል አማካይነት በዓረብ አገሮች ላይ የሚካሄደው ወረራ ፣ በታዳጊ አገሮች ውስጥ ተራማጅ መንግሥታትን ለመገልበጥ ከውስጥ አድኃሪ ኃይሎች ጋር በመመሳጠር ኢ.ምፔሪያሊዝም የሚያካሂዳቸውን ብዙ መፈንቅለ መንግሥቶችም የዚሁ የፀረ-ኮሚዩኒዝም ትግል ገጽታ ናቸው ። በተጨማሪ የኢትዮጵያን አብዮት ለመቀልበስ ኢ.ምፔሪያሊዝም የሶማሌን ተስፋፊ ጦርና ተገንጣይ ቡድኖችን በማስታጠቅ የሚያካሂደው ጣልቃ ገብነት ፣ የኩባን አብዮት ለመቀልበስ እ. ኤ. አ. በ1961 በተሞከረው ወረራ ፣ በአንጎላ ለፀረ-አብዮት ቡድኖች የሚደረገው ድጋፍ ፣ በደቡብ አፍሪካ መንግሥት አማካይነት በሞዛምቢክና በአንጎላ ላይ የሚካሄዱት ወረራዎች ፣ የናሚቢያን ሕዝብ ነፃነት ለመግታት ከደቡብ አፍሪካ ጋር በመተባበር የሚፈጽመው ደባ ወዘተ...... ፀረ-ኮሚዩኒዝም ትግልን ተግባራዊ ማድረጊያ ናቸው ።

እንደዚህ ዓይነቱን ግልጽ የሆነ ወረራና በውስጥ ጉዳይ ጣልቃ እየገባ ፕሮፓጋንዳውን የሚያናፍሰው ኢ.ምፔሪያሊዝም በተለይ የሶሻሊዝም መጠናከርና የአድኃሪያን መዳከም በሚታይበት ጊዜ በመሆኑ በአሁኑ ጊዜ የሞኖፖሊ ካፒታል ጥቅም አስጠባቂ የሆነው የፕሬዚዳንት ሮናልድ ሬጋን ኑመራርም ይህንኑ ቀጥተኛ የሆነ ፀረ-ኮሚዩኒዝም አቋም በማስተጋባትና በማፋፋም ላይ ይገኛል ። የሬጋን አመራር ዓለምን እንደገና ወደ ቀዝቃዛ ጦርነት ለመመለስ ፣ በዓለም ላይ የኑክሌር ጦርነት አደጋ ስጋት እንዲፈጠር ለማድረግ የውጭ ፖሊሲውን በተለመደውና በቀድሞው «ኮሚዩኒዝም እንዳይስፋፋ» በሚለው መፈክር ላይ እንዲገነባ አድርጓል ። በዚህ አቋሙም የአሜሪካ ፈጣን ጣልቃ ገብ ጦር ኃይል በየቦታው በማቋቋም አብዮት በማካሄድ ላይ በሚገኙ አገሮች ውስጥ ጣልቃ ለመግባት ሁኔታዎችን እያመቻቸ ነው ። የጦር መሣሪያ ቅንሳ ስምምነቶች እንዳይፈረሙ በማድረግ የጦርመሣሪያ እሽቅድምድምን ያበረታታል። የውጭ ፖሊሲው በየቦታው ኮሚዩኒዝምን ለመዋጋት የተቀየሰ በመሆኑ ለአድኃሪና ፀረ-አብዮት ኃይሎች ከፍተኛ ዕርዳታ በመስጠት ላይ ይገኛል ። በቅርቡ በአንጎላ ውስጥ የሚገኙትን ፀረ-አብዮት ኃይሎች ለመርዳት ያሳለፈው ውሣኔ የዚሁ ግልጽ የሆነ ጣልቃ ገብነትና ፀረ-ኮሚዩኒዝም አቋሙን የሚያሳይ ነው ። የሶሻሊስትን ሥርዓት ለማዳከምና በሶሺያሊስት አገሮች መካከል ያለውን አንድነት ለማናጋትም በፖላንድ ውስጥ ላሉት ፀረ-ሶሻሊስት ኃይሎች የሚሰጠው የፕሮፓጋንዳና የማቴሪያል ድጋፍም ከዚሁ ጋር የተያያዘ ነው ። በአፍጋኒስታን በመካሄድ ላይ ያለውን አብዮት ለመቀልበስ በአሁኑ ጊዜ ለፀረ-አብዮት ኃይሎች በኢ.ምፔሪያሊዝም የሚሰጠው የተለያየ ዕርዳታ የዚሁ ፖሊሲ አካል ነው ።

ይህ የኢ.ምፔሪያሊዝም ጣልቃ ገብነትና ጠብ አጫሪነትአደገኛ ሁኔታን እየፈጠረ ቢሆንም አብዮታዊ ኃይሎች በቆራጥነት እየተቋቋሙትና በብዙ ቦታዎች እያከሸፉት ነው ። ኢ.ምፔሪያሊዝም በቀጥታ ጣልቃ ገብ ወረራ ብቻ ሣይሆን በሁለተኛውም መንገድ ማለትም በፕሮፓጋንዳውም እየተጠቀመ ነው ። በአሁኑ ጊዜ ኮሚዩኒዝምን ለመዋጋት የሚጠቀምበት ዋነኛው ዘዴ ግልጽ ጣልቃ ገብነት ብቻ ሳይሆን ይልቁንም ተዘዋዋሪና ተለዋዋጭ በሆነ መንገድ ሰፊ የፕሮፓጋንዳ ውዥንብር እያናፈሰ ነው ። በሶሻሊስት አገሮችና የሶሻሊዝምን የእድገት ፈለግ በሚከተሉ አገሮች የአብዮት ቡርቦራና ቅልበሳ ሴራ እያካሄደ ሲሆን ፣ አብዮታዊ እንቅስቃሴዎችን ለመግታትና ለማዳከም ደግሞ በሰርጎ ገቦችና በከፋፋዮች ይጠቀማል ።

በዚህም የፀረ-ኮሚዩኒስት የትግል ስልቱ አማካይነት ሶሻሊዝምንና የኮሚዩኒስት ፓርቲዎችን በማንቋሸሽ ፣ ማርክሲዝም ሌኒኒዝም የሶሺያሊስት ሥርዓትን ባልገነቡ አገሮች እንዲጠላ ሙከራ ያደርጋል ። የግንባር ቀደም ፓርቲዎቹን ርዕዮት ዓለማዊና ድርጅታዊ አንድነት ለማናጋት ለከላሾችና ለበራዥች ድጋፍ በመስጠትና እርምጃውን ከእነርሱ ጋር በማስተባበርም ኮሚዩኒስት ፓርቲዎች በከላሽነት እንዲበከሉ ይጥራል። በአጠቃላይም በተዘዋዋሪ መንገድ ኢ.ምፔሪያሊስቶችና ተባባሪዎቻቸው ተጨባጭ በሆነ መንገድ ለኮሚዩኒዝም አማራጭ የሆነ ነገር ለማቅረብ ባለመቻላቸው የሕዝቡን

ስሜት በሐሰት ፕሮፓጋንዳ በመስለብ በኮ
ሚዩኒዝም ላይ የጥላቻ ስሜት እንዲኖረው
ለማድረግ ይጥራሉ ። በዚህም የሐሰት ዘ
መቻ አማካይነት ኮሚዩኒስቶች ብሔራዊ
ነፃነትን ፣ ዲሞክራሲንና ባሕልን ያጠፋሉ ፣
«ቤተሰብን ያፈራርሳሉ» ፣ «የግለሰብ ሰብ
እናን ይደመስሳሉ» ፣ «የሰው ሞራል ያዋር
ዳሉ» ፣ «ሀይማኖትን ይጻረራሉ» ፣ «በጭ
ፍጨፋ ፣ በኃይልና ሰውን በማስፈራራት
ይገዛሉ» በማለት ሐሰት የተሞላበትና መሠ
ረተ ቢስ የሆነ ቅስቀሳ ያካሂዳሉ ። ስለሶሻ
ሊስት ሀገሮች የተሳሳተ ሥዕል በመሳል
የሰፊውን ሕዝብ አዕምሮ ለመመረዝና አሳ
ስተው ለዓላማቸው ሊጠቀሙበት ይጥራሉ ።

ይህ የፀረ-ኮሚዩኒዝም ዘመቻ ይበል
ጡኑ ያተኮረው ደግሞ የመጀመሪያዋ የሶሻ
ሊስት አገርና የዓለም አብዮታዊ ኃይሎች
መከታ በሆነችው በሶቪዬት ኅብረት ላይ
ነው ። ፀረ-ኮሚዩኒስቶች በሶቪዬት ኅብረት
የሚገኘውን እውነተኛ ገጽታ አሳስተው በ
ማቅረብ ከታላቁ የጥቅምት ሶሺያሊስት
አብዮት በኋላ የሶቪዬት ኅብረት ሕዝብ ያገ
ኘውን ድል ያንቋሽሻሉ ። በሶሻሊስት ግን
ባታ የመጀመሪያ ወቅት የሚያጋጥሙትን
ተጨባጭ ችግሮችና በየጊዜው በመወገድ
ላይ ያሉ የግንባታ ስህተቶችን ከመጠን
በላይ በማጋነን ድክመቱ የማርክሲዝም
ድክመት እንደሆነ አድርገው ለማቅረብ
ይሞክራሉ ። ሶቪዬት ኅብረት ከሌሎች አገ
ሮች ጋር ያላትን ግንኙነትና የውጭ ፖሊ
ሲዋን እያጣመሙ በማቅረብ አብዮታዊ
ኃይሎች ከሶቪዬት ኅብረት ጋር ሊኖራቸው
የሚገባውን አንድነት ለማናጋት ይሞክ
ራሉ ። በ«መስከረም» መጽሔት ቅጽ ፩
1. ቁጥር 1 ላይ በግልጽ እንደተቀመጠው
«ኢምፔሪያሊዝም የሶሻሊዝምን መጥፎነት
ለማሳመን የሚጠቀመው በሶቪዬት ኅብረ
ትና በሌሎች ሶሻሊስት አገሮች ላይ የማጥ
ላላት ፕሮፓጋንዳና ቅስቀሳ በማፋፋም
ነው ።»[7]

ይህን የፀረ-ሶቪዬት መስመር በዝርዝር
ከማየታችን በፊት ኢምፔሪያሊዝም ለምን
የሶሻሊስት አገሮችን የማጥላላት ዘመቻ ሥ
ራዬ ብሎ እንደተያያዘው ማየቱ የግድ አስ
ፈላጊ ስለሆነ ፣ ከዚህ ቀጥሎ የሶሻሊስት
አገሮች በአሁኑ ዓለም አቀፍ አብዮታዊ
እንቅስቃሴ ውስጥ የሚጫወቱትን ወሣኝ
ሚና እንመለከታለን ።

ፀረ-ሶቪዬትነት ፣ የኢምፔሪያሊዝ ምና የአድሀሮት የትግል ፈረስ ፤

ሶሻሊዝም በተሟላ መልኩ ለመጀመ
ሪያ ጊዜ ወደ ተጨባጭ እውነታ የተተረ
ጐመው እ. ኤ. አ. በጥቅምት 1917
በተከናወነው ታላቁ የሩስያ ሶሻሊስት አብ
ዮት ነው ። አንጋፋ የሳይንሳዊ ሶሻሊ
ዝም መሥራቾች የቀመሩት የኅብረተሰብ
የእንቅስቃሴና የዕድገት ንድፈ ሀሳብ ተግ
ባራዊ ሊሆን የቻለው ሌኒንና ቦልሼቪኮች
በግንባር ቀደምትነት በመሩት ትልቁ የጥ
ቅምት አብዮት ሲሆን ፣ የዚህ ውጤት
የሆነችው ሶቪዬት ኅብረት ሶሻሊዝም እን
ዲስፋፋና በዛሬው ጊዜ ከዓለም ሕዝቦች
ከአንድ ሲሶ በላይ የሆነው ከብዝበዛና ከጭ
ቆና ነፃ ሆኖ በዚህ ሥርዓት ውስጥ እንዲ
ተዳደር ግንባር ቀደም ሚና የተጫወተች
መሆንዋን የማያውቅ ወይም የሚክድ አለ
ለማለት አይቻልም ። ጭቁኖችና ምዝብሮች
የኢምፔሪያሊዝምንና የአድኀሮትን ቀንበር
አሽቀንጥረው ለመጣል በዓለም ላይ በማ
ፋፋም ላይ ያሉትን የአብዮታዊ ትግል ቋያ
በግንባር ቀደምነት የምታበረታታና የምት
ደግፍ የመጀመሪያዋ የሶሻሊስት ምድር
የሆነችው ታላቋ ሶቪዬት ኅብረት ናት ።

ከዚህም በላይ ባሉት ክፍሎች እንደ
ተጠቀሰው አድኃሪ የገዥ መደቦች የፀረ
ኮሚዩኒዝም ዋና አላማቸው ያደረጉት ግን
ባር ቀደሞቹን የሶሻሊስት ኃይሎች እንደ
መሆኑ ከታላቁ ጥቅምት ሶሻሊስት አብዮት
ወዲህ ደግሞ ዋና ጠላታቸው በማድረግ የፀረ
ኮሚዩኒዝም ጦራቸውን ያሾሉት በሶቪዬት
ኅብረት ላይ ነው ። የፀረ-ኮሚዩኒዝም ዓይ
ነተኛ መግለጫና መከሰቻ ፀረ-ሶቪዬትነት
ሆኖአል ፣ በዛሬው ወቅት ፀረ-ሶቪዬትነት
ከፀረ-ኮሚዩኒዝም ተነጥሎ ሊታይ አይች
ልም ፣ ፀረ-ሶቪዬትነት ማለት ፀረ-ኮሚዩኒ
ዝም ማለት ሆኖአል ፣ ሁለቱ አንድ ናቸው ።

እንዴት እንደዚህ ይሆናል? ፀረ-ሶቪ
ዬትነት ፀረ-ኮሚዩኒዝም የሚሆንበት ምክ
ንያት ምንድነው? በማለት የሚጠይቁ ይኖሩ
ይሆናል ። ከፍ ብሎ ከቀረበው ሐተታና
ትንተና ነገሩ ግልጽ ቢሆንም ፣ ሁኔታውን
ይበልጥ ማብራራት ይቻላል ። ከፓሪስ ኮሚ
ዩን ወዲህ ብዙሀን ሠርቶአደሮች የወዝ
አደሩ ርዕዮተዓለም አበው ማለትም ማርክ
ስና ኤንግልስ ያቀነባበሩትንና ኅይወታቸ
ውን ሙሉ የታገሉለትን የኅብረተሰብ እድ
ገትና ለውጥ ሳይንስ ማለትም ሳይንሳዊ
ኮሚዩኒዝምን ተግባራዊ ያደረጉበት ምድር
ሶቪዬት ኅብረት ናት ። ይህ ብቻ ሳይሆን
ለስልሳ አራት ዓመታት በተጨባጭ አዲ
ሱን ኅብረተሰብ በመገንባት ትክክለኛነቱን

አረጋግጣለች ። በቢሊዮን የሚቆጠሩ ሠር
ቶአደሮች የጭቆናንና የምዝበራን ቀንበር
አስወግደው በሶሻሊዝም ጥላ ሥር አዲስ
ሕይወት እንዲገነቡ ከፍተኛ አስተዋፅኦ
ያደረገችው የሌኒን አገር ሶቪዬት ኅብረት
እንደ ሆነች የታወቀ ነው ። በኢምፔሪያሊ
ዝምና በአድኅሮት የብዝበዛና የጭቆና ጫማ
ሥር የሚሰቃዩት ምዝብርና ጭቁን ሕዝ
ቦች የሰውን በሰው መበዝበዝ በማስወገድ
ነፃነታቸውንና ሰብእናቸውን ለመጎናፀፍ
በሚያካሂዱት መራራና ውስብስብ ትግል
አይዟችሁ! ከጎናችሁ ቆሚያለሁ ወዝአደ
ራዊ ዓለም አቀፋዊነትን ተግባራዊ አደር
ጋለሁ! በማለት በግንባር ቀደምነት አለኝታ
ነቷን የምታረጋግጠው ታላቋ ሶቪዬት ኅብ
ረት አይደለችምን?

ከታላቁ የጥቅምት ሶሻሊስት አብዮት
በፊት ኢምፔሪያሊዝምና አድኅሮት የብዝ
በዛና የምዝበራ ድንኳናቸውን በመላው
ዓለም ላይ ተክለው ነበር ። ማንም የሚቋ
ቋማቸውና ቀና ብሎ የሚያያቸው አልነበ
ረም ፤ አምባገነንነታቸውን ከአጽናፍ እስከ
አጽናፍ ዘርግተው ነበር ። ብዝበዛውና ምዝ
በራው ገደብና መጠን አልነበረውም ።
ይሁንና ሶሻሊዝም እውን ከሆነና ሶቪዬት
ኅብረት በዓለም መድረክ ላይ ብቅ ካለች
በኋላ ሁኔታው መለወጥ ጀመረ ፤ የምዝ
በራው መስክ እየጠበበ ሄደ ፤ ማርክሲዝም
ሌኒኒዝም በሰፊው ተሠራጨ ፤ በብዙሀን
ኅሊናም ሰረፀ ፤ ምዝብሮችና ጭቁኖች
እምቢኝ አሻፈረን አንበዘበዝም! እንጨ
ቆንም በማለት የትግል አርማቸውን ይዘው
ተነሱ ።

የብዝበዛ መልካቸው ፤ የጥቅም ስልታ
ቸው እየጎደለና እየጠበበ የሄደባቸው ኢም
ፔሪያሊዝምና አድኅሮት ዛሬ የሰውን ልጅ
ከጭቆናና ከብዝበዛ ከኋላቀርነትና ከፍላጎት
ተገዥነት ነፃ ለማውጣትና ሰብእናውን
ለማጎናፀፍ ወደፊት በመገስገስ ላይ ያለ
ውን ኮሚዩኒዝምን ለመቋቋምና ለመገደብ
የፀረ-ሶቪዬትነትን ጥቁር ባንዲራ ከፍ
አድርገው ቢያውለበልቡ የሚገረም ሰው
ይኖር ይሆን? ከዚህ በላይ እንደተመለከ
ተው የኮሚዩኒዝም መከሰት ጥቅማቸውን
የጎነተለባቸው አድኃሪያን ኮሚዩኒስት ታጋ
ዮችንና ድርጅቶቻቸውን «ፀረ-መንግሥት ፤
ፀረ-ሥልጣኔ ፤ ፀረ-ቤተሰብ ፀረ-የግል ንብ
ረት ፤ ከሀዲዎች ዱርዬዎች ፤ ወሮበ
ሎች ፤ ነፍሰገዳዮች ፤ ወንጀለኞች ወዘተ......»
በማለት ውርጅብኝ ያፈሱባቸው ነበር ።
አሁንም ቢሆን ሶሻሊስት አገሮችንና ለዚሁ
ዓላማ የሚታገሉትን በተለይም ደግሞ ቀን
ደኛ ጠላታቸው አድርገው የሚመለከት
ዋትን ሶቪዬት ኅብረትን አርክሰውና አጨ
ልመው የሰይጣን ሰይጣን የጭራቅ ጭራቅ
አድርገው ለማቅረብ ይሞክራሉ ።

ከብዙዎቹ ልፈፋዎችና ውርጅብኞች
ውስጥ ፤ «ዲሞክራሲ የለም ፤ ሰባዊ መብቶ
ችና ነፃነቶች ተሠርዘዋል ፤ የኢኮኖሚው
ይዞታ ሕዝባዊ ወይም ማኅበራዊ ሳይሆን
መንግሥታዊ ካፒታል ነው ፤ የኮሚዩኒስት
ፓርቲ አባሎችና መሪዎቹ የገዥ መደብ
ሆነዋል ፤ የሠርቶአደሩን የድካም ፍሬ የሚ
በዘብዙት ኮሚዩኒስቶች ናቸው ፤ የሰውን
ሁሉ አስተሳሰብ እኩልና አንድ ለማድ
ረግ ይሞክራሉ ፤ ሳይንሳዊ ኮሚዩኒዝም ም
ኞት እንጂ እውነት አይደለም ወዘተ......»
የሚሉት ይገኙባቸዋል ። እነዚህንና የመሳ
ሰሉትን ውንጀላዎች የሚያናፍሱት ወደው
ሳይሆን ጥቅማቸው ስለተነካባቸውና የሥር
ዓታቸው ግብአተ መሬትም መቃረቡን
ስለአዩት ነው ። ሶቪዬት ኅብረትን ለማጥ
ፋትና የሶሻሊዝምን ግሥጋሴ ለማቆም
በጦር መሣሪያ ተጠቅመዋል፤ የኢኮኖሚና
የንግድ ገደብ አድርገው አያሌ ቢሊዮን
ዶላር በማፍሰስ የፕሮፓጋንዳ ወናፍ በዓለም
ላይ አናፍሰዋል ፤ ውጤቱ ግን ሌላ ወይም
የተገላቢጦሽ ነው ።

"Unsere Zeit", FRG

የሶቪዬት ኅብረት «የወታደራዊ ወረራ
ፍራት» ("Soviet threat") ቅጥፈት
ለሚሊተሪዝም የሚሰጥ ምክንያት ነው

የሶቪዬት ኅብረት ከተመሠረተችበት
ጊዜ ጀምሮ የካፒታሊዝም ቅራኔዎች የሚ
ፈቱት በሶሻሊዝም መሆኑን በተግባር ለማ
ሳየት በመቻሏና የዓለም አብዮታዊ ኃይሎች
ዋና ማዕከል በመሆኗ በአሁኑ ጊዜ የፀረ
ኮሚዩኒዝም ትግል ዋና መልክ ፀረ-ሶቭዬ
ትነት እየሆነ መጣ። ኢምፔሪያሊስቶች ኮሚ
ዩኒዝምን ለመዋጋት የመጀመሪያዋን ሶሻ
ሊስት አገር ማንቋሸሽ ፣ ሶሺያሊዝም ዲሞ
ክራሲ የሌለው ሥርዓት እንደሆነ በመስ
በክና ዓለምን ከዚህ «ከኮሚዩኒዝም አደጋ
ለመከላከልና ለማዳን» በሚል ሽፋን በሶቪ
ዬት ኅብረት ላይ ከፍተኛ ዘመቻን ማካ
ሄድ ጀመሩ ። ኢምፔሪያሊዝም በሶቪዬት
ኅብረት የውስጥ አድኃሪያንን በማስታጠ
ቅና የ14 ካፒታሊስት አገሮችን ጦር በማሳ
ባስብና በአዲሲቷ አብዮታዊት አገር አብ
ዮት ላይ ጦርነት በመክፈት በጦር ኃይል
ለመቀልበስ ከፍተኛ ሙከራ ቢያደርግም
ብዙ መስዋዕትነት ከተከፈለ በኋላ ሶቪዬት
ኅብረት ይህንን አደጋ ለመቋቋም ችላለች ።
ከዚህ በኋላ የኢምፔሪያሊዝም ሰላዮችና
ደጋፊዎች ፓርቲውን ለመከፋፈል ሙከራ
ከማድረጋቸውም በላይ የሶሺያሊስት ግንባ
ታውን ለማፈን የኢኮኖሚ አሻጥር ማካሄድ
ጀመሩ ። ለዚሁ ዓላማቸው ዋና ተባባሪያ
ቸው ከነበሩ ፀረ-አብዮተኞች አንዱ ትሮት
ስኪና ተከታዮቹ ነበሩ ።

የሶቪዬት ኅብረት ሕዝብ ጠንካራ ርዕዮ
ተዓለማዊና ድርጅታዊ አንድነት ባለው
ፓርቲው እየተመራ የጠላቶቹን ጥቃት እየ
ተቋቋመ የሶሺያሊስት ግንባታውን በተፋ
ጠነ ሁኔታ ማራመድ ጀመረ ። ይህ ግንባታ
የተካሄደው ፣ ብቸኛና የመጀመሪያ ሶሻ
ሊስት አገር የሆነችው ሶቪዬት ኅብረት
በኢምፔሪያሊስት አገሮች ተከባ የጦርነት
አደጋ በሚያንዣብብበትና የኢኮኖሚ ማዕ
ቀብ ተጥሎባት ከማንም አገር ጋር የንግድ
ልውውጥ እንዳታደርግ በተደረገበት ጊዜ
በመሆኑ ከፍተኛ ድል ነው ። ኢምፔሪያሊ
ዝም በፀረ-ኮሚዩኒስት አቋሙ የመጀመሪያ
ዋን የሶሻሊስት አገር በጦር መሣሪያ ፣
በኢኮኖሚ አሻጥርና በውስጥ ሰርጎ ገቦች
አብዮቱን ለመቀልበስ ያደረገው ሙከራ
ሳይሳካለት ቢቀርም ፣ በሌሎች አገሮች ይህ
ዓይነት አብዮት እንዳይካሄድ ዋና የትግል
መሣሪያ ያደረገው የፀረ-ሶቪዬት ፕሮፓጋ
ንዳና ቅስቀሳን ነው ። ለዚሁ ተግባሩ ቀደም
ሲል የሁለተኛው ኢንተርናሽናል መሪዎች
የነበሩትን እንደ ካርል ካውትስኪ ከአብ
ዮቱ በኋላ በነበራቸው ፀረ-ኮሚዩኒስት አቋም
በስደት የነበሩትን ሜንሼቪኮችና ሌሎች
ፀረ-አብዮት ሩሲያውያንን ተጠቅሞባቸ
ዋል ። ኢምፔሪያሊዝም ለሶሺያሊዝም በ
ዓለም ላይ መስፋፋት ዋንኛውን ሚና የምት
ጫወተው ሶቪዬት ኅብረት መሆኗን ጠን
ቅቆ ስለሚያውቅ በተለያየ መልኩ የፀረ
ሶቪዬት ዘመቻ ከማድረግ ተቆጥቦ አያው
ቅም ፣ ወደፊትም እስከ ግብዓተ መሬቱ
ድረስ አያቋርጥም ። ይህ ሐቅ በሌላ በኩል
ሶቪዬት ኅብረት የምትከተለው ፖሊሲ ትክ
ክለኛ መሆኑን ያረጋግጣል ።

በተለይ የሩስያ ስደተኞች በተለያዩ የአ
ውሮፓ አገሮች በመሆን መለስተኛ የሆኑ
የሶሺያሊስት የኢኮኖሚ ግንባታ ችግሮች
ንና አንዳንድ መጠነኛ ድክመቶችን ከመ
ጠን በላይ በማጋነንና የውሸትና የአሉባልታ
ፕሮፓጋንዳ በማናፈስ የሶቪዬትን መንግ
ሥት ለመቃወም ያካሄዱት የነበረው ዘመቻ
ሶሺያሊዝምን ለመዋጋት ለኢምፔሪያሊዝም
ትልቅ መሣሪያ ሆነው ነበር ።

ማርክሲስቶች ነን ፣ ለኮሚዩኒዝም እን
ታገላለን ፣ ይሉ የነበሩ የውሸት አብዮታው
ያንም በትሮትስኪ ፣ በካርል ካውትስኪና
በመሳሰሉት ከላሾችና በራዦች ግንባር
ቀደምነት እየተመሩ በዚሁ ፀረ-ሶቪዬት
የፕሮፓጋንዳና የፖለቲካ ትግል በመሳተፍ
የኢምፔሪያሊዝም መሣሪያ ሆነው ነበር ፤
አሁንም ናቸው ። በእነዚህ አስመሳዮች አባ
ባል የሩስያ ወዛደር አነስተኛ ስለሆነ ታሪ
ካዊ ተልዕኮውን ሊያከናውን አይችልም ፣
የፓርቲ አባላት እንደ አንድ መደብ ሆነው
የቀረውን የሶቪዬት ሕዝብ እየተጨቆኑ ነው
የሚሉና ሌሎች በሳይንሳዊው ሶሺያሊዝም
ያልተደገፉ የሐሰት ውንጀላዎች በማቅረብ ፣
ሶቪዬት ኅብረትን በመሳደብ ፣ የሕዝቡን
አእምሮ በውሸት በመመረዝ ፣ ኮሚዩኒዝ
ምን በሕዝብ ፊት የማስጠላት ዘመቻቸውን
ተያያዙት ። ይህ ፀረ-ሶቪዬት ዘመቻ በካ
ውትስኪ ፣ በበርንስታይን ፣ በትሮትስኪና
በኋላም በእነ ጂላስ አፈቀላጤነት የተለፈ
ፈው ፣ በአሁኑ ጊዜ ማኦይስቶችና አዲሶቹ
«ግራዎች» (The New Left) ለሚያካ
ሂዱት ፀረ-ሶቪዬት የፖለቲካ ዘመቻ መሠ
ረት ሆኖአል ። አድርባዮች የቀኙም ይሁኑ
የ«ግራ» በአሁኑ ጊዜ አንድ የሚያደርጋ
ቸው ዋና መለያቸው ፀረ-ሶቪዬት አቋማቸው
ነው ። [8] በአሁኑ ጊዜ በየትኛውም አሕጉርና
አገር ውስጥ የኮሚዩኒዝም ጽንሰ ሀሳብ
ሊዋጥላቸው የማይችል አድኃሪያንና ሳይፈ
ልጉት በመዋጥ ሊወጣ እየተናነቃቸው
ያሉ አስመሳዮች ለሶሺያሊዝም ተግባራዊ
ነት የሚደረገውን ትግል ለማኮላሸት ሀብ
ለው የሚጀምሩት በተለያየ ደረጃ የፀረ
ሶቪዬት አቋም በመያዝ ነው ። ከስልሣ

ዓመታት በላይ ሕልውና ያለውን ፥ ከሥር ዓተ ማኅበራት ቆይታ አንጻር ሲታይ እጅግ በጣም አነስተኛ በሆነ ጊዜ ከፍተኛ ዕድገት በማሳየት ወደር የሌለውን የሶሺያሊስት ሥርዓት ተጨባጭ ልምድ በቅን ልቦና ላስ ተዋለና የኢምፔሪያሊዝም የሐሰት ፕሮፓጋ ንዳ ዓይነ ልቦናውን ላልጋረደው ማናቸ ውም ሰው ፤

— ለምሥራቅ አውሮፓ አገሮች ከፋሽዝም ቀንበር መላቀቅና የዳበረ የሶሺያሊስት ሥርዓት መመሥረት ፤

— ለኮሪያ ፥ ለቪዬትናምና ለኩባ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊና ሶሺያሊስት አብዮት ቶች ድል አድራጊነት ፤

— በ1949 ለቻይና ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት መሳካትና ከቅኝ አገዛዝ ቀንበር መላቀቅ ፥

— በዓለም አቀፍ ደረጃ ለቅኝ አገዛዝ ሥርዓት መንኮታኮትና በዛ ያሉ ኋላ ቀር አገሮች ብሔራዊ ነፃነት መጎናጸፍ

— ከእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ለመላቀቅ የሶሺ ያሊስቱን የዕድገት ፈለግ በመከተል ሥር ነቀል የሆነ አብዮት የሚያካሂዱ እንደ ኢትዮጵያ ፥ ሞዛምቢክ አንጎላ ወዘተ......ባሉ አገሮች ውስጥ የሚካሄዱ አብዮቶችን ለመቀልበስ የተካሄዱ ሙ ከራዎች መክሸፍ ፤

— ለአርነትና የነፃ አውጭ ግንባሮች መጠ ናከር ፤

— በመጨረሻም ዓለም አስከፊ ወደሆነው የኑክሌር ጦርነት በኢምፔሪያሊስቶች ጠብ አጫሪነት ምክንያት ለሦስተኛ ጊዜ እንዳይዘፈቅ የዓለምን ሰላም በተ ጠንቀቅ ለመጠበቅ ፥ (ከኢኮኖሚ ግንባ ታውና ከሕዝቡ ብልጽግና በመቀነስ ለሕዝቦች እኩልነት ፥ ለሰላምና ለፍትሕ መስፈን ዋስትናና መከታ የሆነውን የመከላከያ ኃይሉን በመገንባት) በአጠ ቃላይ ለማርክሲዝም ሌኒኒዝም የተቀ ቀደሰ ዓላማ ድልአድራጊነት ፥ የሶቪዬት ኅብረት ሠራተኛ ሕዝብ የከፈለውንና በመክፈል ላይ ያለውን መስዋእትነት ለመገንዘብ አያዳግተውም ።

ሐቁ እንግዲህ ይህ ነው ። የሶሺያሊዝም በዓለም ላይ መስፋፋት ከሶቪዬት ኅብረት ሕልውና ጋር በቅርብ የተቆራኘ ነው ። በመ ሆኑም ሶሺያሊዝምን እንገነባለን ወይም ለመገንባት እንታገላለን የሚሉ ኃይሎች እን ደገና መለስ ብለው ፀረ-ሶቪዬት አቋም ሊይዙ አይችሉም ። ሊይዙ አይችሉም ሲ ባል የሚከለክላቸው ነገር አለ ለማለት ሳይሆን ይህን ዓይነት አቋም ከያዙ ከማርክ ሲዝም ሌኒኒዝም ማፈንገጣቸውን ማወቅ ይኖርባቸዋል ለማለት ነው ። ይህ ደግሞ በቻይና ኮሚዩኒስት ፓርቲ ከሐዲ አመራር አማካይነት በግልጽ የተከሰተ ነው ።

ኢምፔሪያሊዝም የመጀመሪያውን ድል አድራጊ የሶሻሊስት አብዮት ለመቀልበስና በዓለም ሠራተኞች ፊት ሶቪዬት ኅብረትን ለማስጠላት ተደጋጋሚ ሙከራ ቢያደር ግም ዓላማው ያለ መሳካቱን በመገንዘቡ በፋሺዝም አማካይነት ሶቪዬት ኅብረትን ከዓለም ገጽ ለማጥፋት ተነሳሳ ። ፋሺዝም ኢምፔሪያሊዝም ከፋኛ ሲጨነቅ የሚከ ሰት የከረረ ፀረ-ኮሚዩኒስት የፖለቲካ ገጽ ታው እንደመሆኑ መጠን በፋሽዝም አማካ ይነት ሶሺያሊዝምን ከዓለም ገጽ ለማጥ ፋት ከፍተኛ ጦርነት አወጀ ። ናዚ ጀርመን ፥ ፋሺስት ኢጣልያን እና ሚሊታሪስት ጃፓን የተዋዋሉት ፀረ-ኮሚዩንተርን ስምምነትም ይህንኑ ዓላማ ተግባራዊ ለማድረግ ነበር ። በ1941 የጀርመን ጦር ሶቪዬት ኅብረትን ቢወርም የ20,000,000 (ሀያ ሚሊዮን) ውድ ልጆቿን መስዋዕትነት በመክፈል (ፓር ቲውና ኮምሶሞሉ ብቻ ከሦስት ሚሊዮን በላይ አባሎቻቸውን በመስዋዕትነት ከፍለ ዋል) ወረራውን ድባቅ ለመምታት ችላለች። ሶቪዬት ኅብረት ራሷን ከፋሺስት ወረራ ነፃ በማውጣት ብቻ ሳትቆጠብ የምሥራቅ አውሮፓ አገሮችንም ጭምር ከፋሺስት ወራሪ ኃይል ነፃ ወጥተው የሶሺያሊስት ሥርዓት እንዲመሠርቱ መንገድ ከፍታላቸ ዋለች ። በዚሁ ግልጽ ወረራ ኢምፔሪያ ያሊዝም የመጀመሪያዋን የሶሻሊስት አገር ለመደምሰስ ቢሞክርም ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በኋላ ብቸኛ የነበረችው የሶሻሊስት አገር ሌሎች ተጨማሪ ሶሻሊስት አገሮች እንዲከሰቱ በማድረግ ጠንካራ የሶሻሊስት ሥርዓት እንዲመሠረት አድርጋለች ።

ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በኋላ ጠን ካራ ኢምፔሪያሊስት አገር ሆና የወጣችው የአሜሪካ መንግሥት ለጊዜው ብቸኛ የአ ቶሚክ ቦንብ ባለቤት ስለነበረች በዚህ ይዞታዋ በመጠቀም የሶሻሊስቱን ሥርዓት ለማስፈራራትና ለማዳከም ግልጽ የሆነ ዛቻና የከበባ እርምጃዎች መውሰድ ጀመ ረች ። ነገር ግን አሁንም የሶሻሊስት ሥር ዓት መከታ የሆነችው የሶቪዬት ኅብረት እ. ኤ. አ. በ1947 የአቶሚክ ቦንብ ባለቤት ነትዋን በማረጋገጥ ኢምፔሪያሊዝም የዓ ለም ጦርነት ለመቀስቀስ እንዳይችል ለማ ቀብ በቅታለች ። በመሆኑም ከጠቅላላ ጦር

ነት በመለስ በማያቋርጥ አኳኋን የጦርነት አደጋ እንዲያንዣብብ በማድረግ ፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ አስጊ ሁኔታ ለመፍጠርና በዚሁም አማካይነት ሶሻሊዝምን ለማዳከም ኢምፔሪያሊዝም በቀዝቃዛ ጦርነቱ አማካይነት የፀረ ኮሚዩኒዝም ዘመቻውን ለመግፋት ተገደደ ። የሶሻሊስቱ ሥርዓት በሶቪዬት ኅብረት መሪነት በተከተለው የሰላም ፖሊሲና ባገኘውም ኢኮኖሚያዊና ወታደራዊ ጥንካሬ በኃይል ሊደመሰስ የማይችል ጠንካራ ኃይል እንደሆነ በማሳየቱ የግዴታ ኢምፔሪያሊዝም ሌኒናዊውን በሰላም አብሮ የመኖር ፖሊሲን እንዲቀበል ተገደደ ። በሰላም አብሮ መኖር በሚባልበት ጊዜ ግን በሁለቱም ወገን የርዕዮተ ዓለም ትግሉ ይቀራል ማለት ስላልሆነ አሁንም ኢምፔሪያሊዝም የፀረ-ኮሚዩኒዝም ትግሉን በተለይም ፀረ-ሶቪዬት ቅስቀሳውን በረቀቀ መንገድ እያስፋፋ መሄዱን እንመለከታለን ። ቀጠል አድርገን እንደምንመለከተው ይህ የወቅቱ የኢምፔሪያሊዝም ታክቲክ በሚካሄደው ፀረ-ኢምፔሪያሊስት ትግል ውስጥ ባለው የኮሚዩኒስትና የሠራተኛው እንቅስቃሴ እንዲሁም የብሔራዊ አርነት ትግል በማካሄድና የሶሺያሊስቱን የዕድገት ፈለግ በመከተል ላይ ባሉ አገሮችና ኃይሎች መካከል የተገነባውን አንድነት እና ግቶ በማዳከም የኢምፔሪያሊዝምን የበላይነት ለመጠበቅ የሚደረግ ሙከራ ነው ።

ባለፉት ገጾች ለማሳየት እንደተሞከረው ኢምፔሪያሊዝም የኮሚዩኒዝምን አስተሳሰብ ለመዋጋት ፣ ጭቁን ሕዝቦች አድኃሪ ሥርዓትን ገርስሰው የሶሺያሊስት ስርዓት ማኅበር እንዳይመሠርቱ ለመከላከል ፣ በአብዮታዊ ኃይሎች መካከል ያለውን አንድነት ለማናጋትና ያለውን የሶሺያሊስት ሥርዓት በተለይም ሶቪዬት ኅብረትን የማጥላላት ዘመቻ ያራምዳሉ ። እስካሁን እንደተመለከትነው የሶሻሊስት ማንባታ ሊሳካ የሚችለው በብሔራዊ ጥቅምና በዓለም አቀፋዊነት መካከል ያለው ጥብቅ ግንኙነት ያልተናጋ እንደሆነ ነው ። ኢምፔሪያሊስቶች ይህን ጉዳይ ጠንቅቀው ስለሚያውቁ ብሔረተኝነትን በመቀስቀስ አብዮትን ለማኮላሸት ከፍተኛ ጥረት ያደርጋሉ ።

በአሁኑ ጊዜ ፀረ-ሶቪዬት አቋምና አድርባይነት ልዩነት የላቸውም ፣ ሁለቱም የበዝባዥ መደቦችን ጥቅም የሚጠብቁ ፣ የአድኃሪያን ዋና የትግል መሣሪያዎች ናቸው። ኢምፔሪያሊዝምና ደጋፊዎቹ የዓለም የሶሻሊስት ሥርዓትን ፣ በካፒታሊስት አገሮች ውስጥ የሚካሄደውን የሠራተኛ እንቅስቃሴና በኋላቀር አገሮች የሚካሄደውን አብዮታዊ እንቅስቃሴ ለማዳከም የሚጠቀሙባቸው መሣሪያዎች ናቸው ። ሌኒን በግልጽ እንዳስቀመጠው ከታላቁ የጥቅምት የሶሺያሊስት አብዮት በኋላ «የቡርዧ መደቦችን ቦልሼቪዝም ፍርሀት አሳድሮባቸዋል ፣ ብስጭታቸው እስከ እብደት ደረጃ እየደረሰ ነው ፣ በዚሁ ምክንያትም ትኩረቱ በሞላ ቦልሼቪዝምን በኃይል በማጥፋት ላይ ሆኗል ፣»[9] ብሎ ነበር ።

ፀረ-ሶቪዬት አቋም የቡርዧውን መደብ ጥቅም ለማስጠበቅ የቆመ የፀረ-ኮሚዩኒስቶች ፖሊሲ የሆነበት ምክንያት ሶቪዬት ኅብረት የዓለም አብዮታዊ እንቅስቃሴዎች መከታ በመሆን ፣ በሁሉም አንፃር የኢምፔሪያሊዝምን ግፊት ለመቋቋም የቻለች አገርና የፀረ-ኢምፔሪያሊስት ትግሉ መሪ ኃይል በመሆኗ ነው ። ሶቪዬት ኅብረት በታላቁ ሌኒን የተመራች የመጀመሪያ የሶሻሊስት አገር እንደመሆኗ በአለፉት 64 ዓመታት በማኅበራዊ ዕድገት አንፃር መንገድ ቀያሽና ምሣሌ ሆና ቆይታለች ። በነዚህ ዓመታትም ሶቪዬት ኅብረት ለሶሻሊዝምና ለኮሚዩኒዝም መከታ በመሆን የሂትለርን ፋሽዝም በመደምሰስ ፣ የሶሻሊስት ግንባታ በማካሄድ ላይ ላሉ አገሮች ዕርዳታ በመስጠት ፣ የሶሺያሊዝም ግንባታ ሂደት እንዲጠናከር በማድረግና ለሰላም የሚደረገውን ትግል በመምራት ለዓለም አብዮታዊ ኃይሎች ትግል አመቺ ሁኔታ የፈጠረችና በመፍጠርም ላይ የምትገኝ አገር ናት ።

የሌኒን አገር በሆነችው የሶቪዬት ኅብረት ለመጀመሪያ ጊዜ የዳበረ የሶሻሊስት ሥርዓት ተገንብቷል ። በሶቪዬት ኅብረት የግል ሀብት ሙሉ በሙሉ ጠፍቶ ሠርቶ አደሩ ሕዝብ የአብዮቱ ድሎቹ ተጠቃሚ ሆኗል ። በአገሪቱ ጠንካራ የምርት ኃይሎች ፣ በጣም ያደገ ሳይንስና ባሕል ፣ የሕዝቡ የኑሮ ሁኔታ በየጊዜው በማደግ ላይ የሚገኝበትና ለግለሰብ ዕድገትም በጣም አመቺ ሁኔታዎች የተፈጠሩባት አገር ነች ። ሠራተኛ መደቦች በተገኘው ከፍተኛ የምርት ኃይሎች ዕድገት አማካይነት ይበልጥ እየተቀራረቡ የመጡበት ፣ በሕግና በተግባርም የብሔሮችና ብሔረሰቦች እኩልነት የተረጋገጡባት አገር ነች ። ሶቪዬት ኅብረት ነፃ ሕክምና ፣ ነፃ ትምህርት ፣ በጣም ዝቅተኛ የሆነ የቤት ኪራይ ዋጋና ሌሎች ማኅበራዊ አገልግሎቶች ለሰፊው ሕዝብ ሙሉ በሙሉ ለማዳረስ የቻለች አገር ናት ። በፖለቲካውም አንፃር 17 ሚሊዮን አባላት ባለው ግንባር ቀደም

ፓርቲው ኢማካይነት ሕዝቡ በመንግሥታዊ አስተዳደር በምርት ተግባርና በማከፋፈሉ ላይ ሙሉ በሙሉ ተሳታፊ እንዲሆን ተደርጓል ። በፓርቲው መሪነት ጠንካራ የሆኑ ሕዝባዊ ድርጅቶች በኮሚዩኒስት ግንባታ ላይ ንቁ ተሳትፎ በማድረግ ሠራተኛው ሕዝብ በአገሩ የፖለቲካና የኢኮኖሚያዊ ሕይወት ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ እንዲሳተፍ የተደረገባት አገር ናት ።

የሶቪዩት ኅብረት የውጭ ፖሊሲ መደባዊ ይዘት ያለው የሶሻሊስት ፖሊሲ ነው ። ይህ ፖሊሲ ፀረ-ኢምፔሪያሊስት ፣ ፀረ-ጭቆናና ብዝበዛ ነው ። በመሆንም ሶቪዩት ኅብረት ከሌሎች አገሮች ጋር የምትመሠርተው ግንኙነት ለመበዝበዝ ወይም ለመጨቆን ሳይሆን በነዚህ አገሮች ለዕድገት አመች የሆነ ሁኔታ እንዲፈጠር ለማድረግ ነው ።

ሶቪዩት ኅብረት ከኋላቀር አገሮች ጋር የምትመሰርተው የኢኮኖሚ ግንኙነት እንደ ኢምፔሪያሊስት አገሮች በተዘዋዋሪና በቀጥታ የእነዚህን አገሮች የተፈጥሮ ሀብት ለመበዝበዝ ፣ ከሰጠው ዕርዳታ የበለጠ በተለያየ መንገድ በትርፍ መልክ ለመውሰድና በሌላ መንገድ ለመጠቀም ሳይሆን እነዚህ አገሮች ከሶቪዩት ኅብረት ጋር በሚያደርጉት የኢኮኖሚ መተባበር አማካይነት ከኢምፔሪያሊዝም ብዝበዛ ነፃ እንዲሆኑ ለማስቻል ነው ። የሶቪዩት ዕርዳታ ተቀባይ አገሮቹ የከባድ እንዱስትሪዎች ባለቤት እንዲሆኑና ከኢምፔሪያሊዝም ጥገኝነት እንዲላቀቁ ለማድረግ ፣ ነፃ የሆነ ብሔራዊ ኢኮኖሚ እንዲገነቡ ይረዳል ። ከሶቪዩት ኅብረት የሚያገኙትም ወታደራዊ ዕርዳታ እነዚህ አገሮች ብሔራዊ ነፃነታቸውንና አብዮታቸውን ከኢምፔሪያሊዝምና ፀረ-አብዮት ሰራዎች ለመከልከል የሚያስችል ዕርዳታ ነው ።

በአፍሪካ ፣ በእስያና በላቲን አሜሪካ የሚገኙ አገሮች ካለባቸው የኢኮኖሚ ኋላቀርነት ለመላቀቅ ያላቸው ብቸኛ መንገድ ሶሻሊዝም ብቻ ነው ። በ«መስከረም» ቅጽ 1 ቁጥር 1 ላይ «ኋላቀርነትና መፍትሔው ፣ በኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ግንባታ ግንዛቤ» በሚል አርዕስት ሥር ከኋላቀርነት ለመላቀቅ በፀረ-ኢምፔሪያሊስት ትግል አማካይነት የሶሻሊስት ግንባታ ማካሄድ እንዳለባቸው በዝርዝር የተቀመጠ ስለሆነ እዚህ ላይ መድገሙ አስፈላጊ አይደለም ።

ኢምፔሪያሊዝም የሶሽያሊስቱን የዕድገት ፈለግ በሚከተሉ አገሮች የተቀጣጠለውን አብዮት ለመቀልበስ ሙከራ የሚያደርግ ፣ እንደገና በብዝበዛ መረቡ ሊያስገባቸው የሚጥር ኃይል ሲሆን የሶሻሊስት ሥርዓት ግን ኋላቀር አገሮች ከኢምፔሪያሊስት ብዝበዛ ነፃ ወጥተው ነጻ ኢኮኖሚ እንዲገነቡ የሚረዳ ፣ አብዮታቸውን ለማጠናከር በወዳጅነትና በዓላማ አንድነት ላይ የተመሠረተ ዕርዳታ የሚሰጥ ኃይል ነው ። ከኋላቀርነት ለመላቀቅ ከሶሻሊስት አገሮች ጋር ጠንካራ ግንኙነት መፍጠር አማራጭ የማይገኝለት ግዴታ ነው ።

የሶሺያሊስትን የዕድገት ፈለግ የመረጡ አገሮች ከሶሽያሊስት አገሮች ጋር መፍጠር ያለባቸውን የጠበቀ የኢኮኖሚክ ግንኙነት ለማኮላሸት በኢምፔሪያሊስቶችና በነዚህ አገሮች ውስጥ ባሉ ፀረ-ሶሽያሊስት ኃይሎች ከፍተኛ ቅስቀሳ ያካሂዳል ። «የሶሻሊስት ሀገሮች ቴክኒዎሎጂ ከምእራቡ ዓለም ያነሰ ነው ፣ ለኛ ኑ ይስማማንም ፣ የለመድነው ቴክኒዎሎጅ ከምእራቡ የመጣ ስለሆነ አሁን አዲስ ብንቀይር ለዚህ ዓይነት ቴክኒዎሎጂ አስፈላጊውን ሰው ለማሠልጠን ከፍተኛ ወጭን ይጠይቃል "ከሶሽያሊስት አገሮች የማመጠው የልማትም ሆነ የፍጆታ ዕቃ አይረባም" ወዘተ...... የሚሉ የተለመዱና አንድም ዕውነትነት የሌላቸውን ሀረጐችን በማወናጨፍ ፀረ-አብዮት ኃይሎች የሶሽያሊስቱን የዕድገት ፈለግ በመረጡ ሀገሮችና በሶሽያሊስት ሀገሮች መካከል መኖር የሚገባውን የኢኮኖሚ ትብብር ለማናጋት ያሰራሉ ። ለመሆኑ ከሶሽያሊስት ሀገሮች የሚመጣው የማምረቻም ሆነ የፍጆታ ዕቃ «የማይረባ» ሆኖ ከተገኘ ፣ የሶሽያሊስት ሀገሮች በዚህ ዓይነት ሁኔታ አሁን የደረሱበት ከፍተኛ የኢኮኖሚ የዕድገት ደረጃ ላይ እንዴት ሊደርሱ ቻሉ? ፀረ ሶሽያሊስት ኃይሎች ለዚህ አጥጋቢ መልስ መስጠት አይችሉም ።

የኋላቀር ሀገሮች ፣ የሶሽያሊስቱን የዕድገት ፈለግ በመከተል ላይ ያሉትም ቢሆኑ ፣ በአብዛኛው ኢኮኖሚያቸው በተለይም የውጭው ንግዳቸው አጠቃላይ አቅጣጫ ከዓለም አቀፍ የካፒታሊስት ገበያ ጋር ገና ጠርሶ ያልተላቀቀ በመሆኑ ፣ በዚህ ግንኙነት ወይንም ከኢምፔሪያሊስቱ ዓለም ጋር ያለውን የኢኮኖሚ ግንኙነት በማጥበቅ በተለያየ መንገድ የግል ጥቅም የሚያገኙ ክፍሎች ከሶሽያሊስት አገሮች ጋር መኖር የሚገባውን የተጠናከረ የኢኮኖሚ ትብብር በሚመለከት ክፉኛ ተቃውሞ ያነሳሉ ። ተቃውሞአቸውም የሶሽያሊስት ሀገሮችን ቴክኒዎሎጂና ዕቃ ማንቋሸሽ ፣ ከሶሽያሊስት

ሀገሮች ጋር ሊደረግ የታሰበውን የኢኮኖሚ
ትብብር በየደረጃው መሰናክል እንዲፈጠ
ርበት በማድረግ ማኮላሸት ፣ አልፎ ተርፍም
ፀረ-ሶቪዬት የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ ማካሄድ
የመሳሰሉትን ያጠቃልላል ።

እዚህ ላይ ዋናው ነጥብ የሶሺያሊስት
የዕድገት ፈለግ የሚከተሉ አገሮች ከኢም
ፔሪያሊስት አገሮች ጋር ምንም የንግድ
ግንኙነት አይኑራቸው ወይንም ከካፒታሊ
ስቱ የዓለም አቀፍ ገበያ ላይ ካላቸው ጥገ
ኝነት በአንድ ጊዜ ለመላቀቅ ይችላሉ ለማ
ለት ሳይሆን ፣ የውጭ ንግዳቸው ይዘት አጠ
ቃላይ አቅጣጫ፣(ለመገንባት የሚታገሉት
የሶሺያሊስት ኢኮኖሚ ስለሆነ) ደረጃ በደ
ረጃ ከሶሺያሊስት የዓለም አቀፍ ገበያ ጋር
ያላቸውን ግንኙነት የሚያጠናክር መሆን
አለበት ማለት ነው ። ይህ ሳይሆን ቀርቶ
ከዓለም አቀፍ የካፒታሊስት ገበያ ጋር
ያለው የንግድ ግንኙነት አጠቃላይ አቅጣጫ
እየተጠናከረ ከሄደ የሶሺያሊስት ክፍለ ኢኮ
ኖሚ ሊቦረቦር ይችላል ።

በታሪክ እንደታየው የሶሻሊስት ግንባታ
ማካሄድ የጀመሩ አገሮች ፀረ-ሶቪዬት መስ
መር ማራመድ ሲጀምሩ በቀጥታ ከኢምፔ
ሪያሊዝም ጋር ለመሰለፍ ይገደዳሉ ። ለዚ
ህም ግልጽ ምሣሌ የሚሆነን አድኀሪው
የቻይና ኮሚዩኒስት ፓርቲ አመራር ነው ።
የቻይና ኮሚዩኒስት ፓርቲ በቻይና ውስጥ
አንደኛው የአምስት ዓመት ፕላን እ. አ. አ.
በ1958 እስከተከናወነ ድረስ ከሶቪዬት ኅብ
ረትና ከሌሎች የሶሻሊስት አገሮች ጋር ጠን
ካራ አንድነት በመመሥረት ሣይንሣዊ በሆነ
መንገድ የሶሻሊስት ግንባታውን ያካሂድ
ነበር ። ከ1958 በኋላ በፓርቲው አመራር የብ
ሔረተኝነት አዝማሚያ እየተጠናከረ ሄዶ
ግልጽ የሆነ ፀረ-ሶቪዬት አቋም መከሰት
እንደጀመረ ግን በአገር ውስጥም ሆነ
በውጭ ፖሊሲው ፀረ-ማርክሲስት ሌኒኒስት
አቋሞችን በመውሰድ አድኀሪ መስመር
ማራመዱን ጀመረ ። አማራጩ ከኢምፔሪ
ያሊዝም ጋር መሰለፍ ስለሆነ የቻይና አድ
ሀሪ አመራር በአሁኑ ጊዜ በግልጽ እንደሚታ
የው ከኢምፔሪያሊዝም ጐን በመሰለፍ
አድኀሪ መስመር በማራመድ ላይ ይገኛል ።
በዚሁ አቋሙም የዓለም አብዮታዊ ኀይሎ
ችን ለማዳከምና ለመከፋፈል ሲጣጣር ይ
ታያል ።

ፀረ-ሶቪዬት ፕሮፓጋንዳ ኢምፔሪያሊ
ስቶችና መላ አድኀሪያን አብዮታዊ ኀይሎ
ችን ለመዋጋት የሚጠቀሙበት ዋነኛ መሣ
ሪያቸው ከመሆኑም በላይ ኮሚዩኒዝምን
ለማጥላላት የሚጠቀሙበት ዘዴ ነው ። ኢ
ምፔሪያሊስቶችና ቡችሎቻቸው የፀረ-ሶቪ
ዬት የፕሮፓጋንዳ ዘመቻቸውን የተያያዙት
ከታላቁ የጥቅምት ሶሺያሊስት አብዮት መ
ባቻ ጀምሮ ቢሆንም እንደነሱ ፍላጐት
ሳይሆን ፣ የሶሺያሊዝም ተቀባይነት በየጊ
ዜው እየጨመረና ፀረ-ኢምፔሪያሊስት ትግ
ሉም ሰፋትና ጥልቀት እያገኘ በመሄድ ላይ
ነው ። ይህም ሊሆን የቻለው አብዮታውያን
ኀይሎች የፀ-ረኮሚዩኒዝም አቋም የሚከሰ
ትበትን ፀረ-ሶቪዬት ፕሮፓጋንዳ ያለማ
ቋረጥ በመታገል ፀረ-አብዮት ይዘቱን ለማ
ጋለጥ በመቻላቸው ነው ።

በ1956 እና በ1968 የሀንጋሪና ቼኮዝ
ሎቫኪያ የአብዮት ቅልበሳ ሙከራዎች
የተቃጡት ይህንኑ የፀረ-ሶቪዬት አቋም
በመመርኮዝ ነበር ። በግብጽ ተጀምሮ
የነበረው ተራማጅ እንቅስቃሴ ሂደትም
ቢሆን የሳዳት መንግሥት ፀረ-ሶቪዬት አቋም
ከወሰደ በኋላ ቀስ በቀስ አሁን ወደአለበት
የኢምፔሪያሊዝም ዋና ተገዥና መሣሪያ
ወደመሆን ደርሷል ።

እዚህ ላይ ማስታወስ የሚያስፈልገው
ከ1917 የጥቅምት ሶሻያሊስት አብዮት
ጀምሮ ይህን የፀረ-ሶቪዬት ፕሮፓጋንዳ በማ
ሠራጨት ረገድ ከፍተኛ ሚና በመጫወት
ላይ የሚገኙ በየአገሮቻቸው በሚካሄዱ አብ
ዮታዊ እንቅስቃሴዎች የበረገጉ ፣ ወይም
እንቅስቃሴው ለሥልጣን አላበቃ ብሎ
አቸው የፈረጠጡና አብዮቱን ለማዳከም
ጥረት የሚያደርጉ ፀረ-አብዮት ስደተኞች
(አሚግረስ) እንደሆኑ ነው ። እነዚህ ኃይ
ሎች መጀመሪያውኑም በስደት ወደ ውጭ
አገር የሄዱት በየአገሮቻቸው የሚካሄደውን
አብዮት በመጥላትና የሶሻሊስት ግንባታውን
ለመቀልበስ ሳይችሉ በመቅረታቸው በመ
ሆኑ በውጭ አገር አብዮቱን ለማጥላላት
እንደ ትልቅ መሣሪያ አድርገው የሚጠቀ
ሙበት የብሔረተኝነት ስሜት በመቀስቀ
ስና ፀረ-ሶቪዬት ፕሮፓጋንዳ በማናፈስ ነው።
እነዚህ ፀረ-አብዮተኛ ስደተኞች የሀገርን ጥቅ
ም ለግል ጥቅም የሸጡ ከመሆናቸውም በላይ
ለኢምፔሪያሊዝም ያላቸውን ታማኝነት የ
ሚያረጋግጡበት ዋንኛው ዘዴያቸው ሶቪ
ዬት ኅብረትን ክፉኛ እንደሚጠሉ ለማሳ
የት ከኢምፔሪያሊስት የዜና ማሠራጫ
ዎች የሚለቅሙትን «እድልዎ የሌለበት»
ዜና በመለቃቀም በብሔራዊ ጥቅም ሽፋን
ሽፋፍኖ በማቅረብ ነው ። በመሆኑም ፀረ
ሶቪዬት ቅስቀሳ በአሁኑ ጊዜ በተለያየ
መልኩ የቀኝና የ«ግራ» ሽፋን ይዘው
ለሚመጻደቁ አድኀሪያን ለአብዮት ያላቸ

ውን ጥላቻ የሚገልጹበት መግሪያ ሆኖ አል ።

ለማጠቃለል ያህል ሶቪዬት ኅብረት በዓለም አቀፍ ኮሚዩኒስት ንቅናቄ ውስጥ ያላትን ከፍተኛ ሚና በማስመልከት ጓድ ፊደል ካስትሮ ሩዝ በ26ኛው የሶቪዬት ኅብረት ኮሚዩኒስት ፓርቲ ስብሰባ ላይ ያደረጉትን ንግግር መጥቀሱ በቂ ይሆናል ። «ይህ አርጌው የቅኝ አገዛዝ የተደመሰሰበት ፤ ሶሻሊዝም በየጊዜው እየተጠናከረና እየ ተስፋፋ የሄደበት ዘመን ቀደም ሲል በነበረው ታሪክ ጨርሶ ያልታወቀ ብሩህ የነፃነትና የብሔራዊ አርነት ዘመን የተከፈተበት ዓለም እውን ሊሆን የቻለው ለማርክሲዝም ሌኒኒዝም ፍጹም ታማኝ በሆነችውና ጠንካራ ዓለም-አቀፋዊ ፖሊሲ በምታራምደው በሶቪዬት ኅብረት ሶሻሊስት ሪፑብሊክ መኖር ሲሆን ፤ በመጨረሻም ይህ ዓለም እውን ሊሆን የቻለው ኢምፔሪያሊዝም በግድ እንዲወስደው በተገደደው የማይበገር ጥንካሬዋ አማካይነት ነው ።»[10]

በመጠኑም ቢሆን የሶቪዬት ኅብረት የውስጥና የውጭ ፖሊሲ በተግባር እንደታየው የተጠቀሰውን ሲመስል ፤ ኢምፔሪያሊዝምና ቡችሎቹ ግን እውነቱን አጣመው በማቅረብ ሶቪዬት ኅብረትን የሁሉም መጥፎ ነገሮች ምንጭ እንደሆነች አድርገው ሊያቀርቡ ይሞክራሉ ። በሶቪዬት ኅብረት ይህ አሁን የተደረሰበት የዳበረ የሶሻሊስት የዕድገት ደረጃ ላይ ለመድረስ ብዙ ከባድ ችግሮች መታለፍ ነበረባቸው ። የአገሪቱ ኢኮኖሚ በአብዮቱ ጊዜ አንፃራዊ በሆነ መንገድ ሲታይ ኋላቀር የነበረና በሁለት ጣልቃ ገብ ጦርነቶች የበለጠ የተዳከመ ነበር ። የመጀመሪያ ሶሻሊስት አገር በመሆንዋ የተነሳም ምንም ረዳት አልነበራትም ። ለሶሻሊስት ግንባታ ምሳሌ ሊሆናት የሚችል የሶሻሊስት ግንባታ ልምድ ባልነበረበት ጊዜ በመሆኑና በካፒታሊስት አገሮች ተከባ አስቸጋሪ ዓለም አቀፍ ሁኔታ የነበረበት ስለሆነ ግንባታው በጣም አስቸጋሪ ነበር ። በዚሁ ሁኔታ የተካሄደው የሶሻሊስት ግንባታ አስቸጋሪ ብቻ ሳይሆን አልፎ አልፎም ስህተቶች የታዩበትም ጊዜ ነበር ። እነዚህ ጊዜያዊ ድክመቶች ግን ወዲያው እየታረሙና እየተስተካከሉ በመሄዳቸው አሁን የተደረሰበት ከፍተኛ የዕድገት ደረጃ ላይ ለማድረስ ተችሏል ። በሶሻሊስት ግንባታ ወቅት አንዳንድ ድክመቶች መከሰታቸው ሶሻሊዝም መጥፎ ነው ወደሚለው መደምደሚያ ከተሊያደርስ እንደማይችል ግልጽ ነው ። እንደዚህ ባይሆንማ ኖሮ ከተከሰተ ገና የስልሳ ዓመታት ዕድሜ ያለው የሶሻሊስት ሥርዓት በኢኮኖሚ በማኅበራዊ ኑሮ በሳይንስና በቴክኖሎጂ ዕድገት ወዘተ...... መስኮች ከሦስት መቶ ዓመት በላይ ዕድሜ ያለውን የካፒታሊስት ስርዓት ከፍተኛ ውጥረት ላይ ሊጥለው ባልቻለም ነበር ።

የተራማጅና ሶሻሊስት ኃይሎች አንድነት

ዘመኑ ከካፒታሊዝም ወደ ሶሻሊዝም የመሸጋገሪያ ዘመን ነው ። ይህ ሽግግርም የሚከናወነው በአዲሱ የሶሻሊስት ሥርዓትና ፤ በአረጀውና በአድኃሪው የካፒታሊስት ሥርዓት መካከል በሚደረገው ትግል አማካይነት ነው ። የካፒታሊስትን ሥርዓት ለማቆየት ጥረት የሚያደርገው ኢምፔሪያሊዝም በመሆኑ ይህ ሽግግር ሊከናወን የሚችለው አብዮታዊ ኃይሎች በሚፈጥሩት ጠንካራ ፀረ-ኢምፔሪያሊስት አንድነት ነው ። በአሁኑ ጊዜ በፀረ-ኢምፔሪያሊስቱ የትግል ግንባር የተሰለፉት ኃይሎች የሶሻሊስት አገሮች ፤ በኋላቀር አገሮች የሚካሄደው የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮትና በካፒታሊስት አገሮች ያለው የሠራተኛው ዲሞክራቲክ እንቅስቃሴ ናቸው ።

አብዮታዊ ኃይሎች ግባቸውና ዓላማቸው ተመሳሳይ የሆነ የሶሻሊስት ግንባታ ነው ። ጠላታቸውም ኢምፔሪያሊዝም በመሆኑ ሁሉም አንድ ጠላት አላቸው ። የትግል ስልታቸው በማርክሲዝም ሌኒኒዝም የሚመራና ተመሳሳይ በመሆኑ ፤ በበለጠ መረዳዳት ፤ ልምዳቸውን በማሰባሰብ የሀሳብ ልውውጥ ማድረግ ይኖርባቸዋል ። እነዚህ የዓለም አብዮታዊ ኃይሎች ነፃ ሆነው የኮሚዩኒስት ግንባታ ለማካሄድ የሚችሉት በዓለም አቀፍ ደረጃ ሶሻሊዝም ሲገነባ ነው ። ኢምፔሪያሊዝምን ከዓለም ገጽ ለማጥፋት የግድ አብዮታዊ ኃይሎች መሰባሰብ ፤ ትግላቸውን ማቀነባበርና አንድነታቸውን ማጠናከር ይኖርባቸዋል ። ይህ ሊፈጸም የሚችለው ማርክሳዊ ሌኒናዊ በሆነው በወዛደራዊ ዓለም አቀፋዊነት መርኅ በመመራት ነው ። ሌኒንም እንዳለው «የካፒታሊዝም አገዛዝ ዓለም አቀፋዊ ነው ፤ በመሆኑም በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚደረገው የሠራተኛ ትግል አሸናፊ ሊሆን የሚችለው ሠራተኞች ዓለም አቀፍ ካፒታልን ለማጥፋት ተባብረው ሲዋጉ ነው ።»[11]

ከታላቁ የጥቅምት ሶሺያሊስት አብዮትና ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላም የሶሻሊስት ሥርዓት መመሥረት የወዛደራዊ ዓለም አቀፋዊነትን መርኅ እያደገና ተግባራዊነቱ እየጎላ እንዲመጣ አድርጎታል ።

ማንኛውም የዓለም አብዮታዊ ኃይሎች ብሔራዊ አካል ዓለም አቀፋዊ ግዴታውን በመጀመሪያ የሚወጣው በአገሩ ውስጥ የኢምፔሪያሊዝምን የእጅ አዙር አገዛዝና ብዝበዛ በመደምሰስ የሶሻሊስት ግንባታዋን ሲያከናውን ነው ። የሶቪዬትኅብረት በመጀመሪያ ዓለም አቀፋዊ ግዴታውን የተወጣችው የታላቁን የጥቅምት ሶሺያሊስት አብዮት ፀማካሄድ ለዓለም አብዮታዊ ኃይሎች መከታ የሆነ የሶሽያሊስት ሥርዓት በመገንባት ነው ። ሆኖም የአንድ አብዮታዊ ብሔራዊ እንቅስቃሴ ድል ሊረጋገጥ የሚችለው በዓለም አቀፍ ደረጃ በሶሻሊዝምና በኢምፔሪያሊዝም መካከል በሚደረገው ትግል በሚገኘው ውጤትና ሌሎች አብዮታዊ ኃይሎች በሚያገኙት ድልና ውጤት ነው ። በሌላ አነጋገር የማንም አገር አብዮታዊ እንቅስቃሴ ድል ዋስትና የሚያገኘው ኢምፔሪያሊዝም ሲዳከምና በመጨረሻም ከዓለም ገጽ ሲጠፋ በመሆኑ ለሶሻሊዝም የሚታገሉ ኃይሎች መጠናከር ፣ እያደጉ እንዲሄዱ መርዳትና በመካከላቸው ጠንካራ አንድነት መመሥረት ካላቸው የጋራ ብሔራዊ ጥቅምና የዓለም አቀፉ የሠራተኛው እንቅስቃሴ የጋራ ዓላማ ጋር የተቆራኘ ነው ።

ሆኖም ፀረ-ኮሚዩኒስቶች ይህን የሶሻሊዝም ጥንካሬ የሆነውን አንድነት ለማናጋትና አብዮታዊ ኃይሎች ተከፋፍለው ለአንድ የጋራ ዓላማ እንዳይዋጉ በማድረግ ሊያዳክሟቸውና ለኢምፔሪያሊዝም ጣልቃ ገብነት ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር ብዙ ጥረት ያደርጋሉ ። ጥረታቸው በብዛት ያተኮረው ደግሞ በሶሻሊስትና የሶሻሊስት ግንባታ ሂደት በተያያዙ አገሮች ውስጥ የብሔረተኝነት ስሜት ለመቀስቀስ ሙከራ በማድረግ ነው ። ይህ ጉዳይ በ«መስከረም» ቅጽ 1 ቊጥር 1 ላይ «ወዝአደራዊ ዓለም አቀፋዊነት በሚል አርዕስት ሥር በሰፊው የተብራራ ቢሆንም በመጠኑ ከጽሑፉ ለመጥቀስ «ለማርክሲስቶች ወዛደራዊ ዓለም አቀፋዊነት የአገሮችን ብሔራዊ ነፃነት ፣ እኩልነትና ብሔራዊ ልዕልናን የሚያጠቃልል ጽንሰ ሀሳብ ነው ። ይህም አንድነት በጋራ ዓላማና በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ያደርገዋል ። ሆኖም የእኩልነትና የነፃነት ጥያቄዎች በራሳቸው እንደ ዓላማ ተደርገው የሚወሰዱ አይደሉም ። ለሚካሄደው ዓለም አቀፍ የመደብ ትግል ጥቅም ሲባል ተገዥ መሆን አለባቸው ፤»[12] በማለት አስፍሮታል ።

በዚህ «መስከረም» ጽሑፍ ላይ በተጨማሪ እንደተጠቀሰው ፣ «በአንድ አገር ክልል ውስጥ የሚደረገው ትግል ብዝበዛን ለማጥፋት የኢምፔሪያሊዝምን ተጽእኖ ለመደምሰስ የሚደረግ የሶሻሊስት ግንባታ በይዘቱ ዓለም አቀፋዊ ነው ። ዓለም አቀፋዊነት የዓለም ሠራተኞች ሙሉ ጥቅም የሚገለጽበት የመጨረሻ የተጠቃለለ መግለጫ እንደመሆኑ ከእውነተኛ ብሔራዊ ጥቅም ጋር አይጋጭም ።»[13] የሶሻሊስት አገሮች ልምድ በተጨባጭ የሚያሳየው አሁን የደረሱበት ከፍተኛ የዕድገት ደረጃ ላይ ሊደርሱ የቻሉት በወዝአደራዊ ዓለም አቀፋዊነት መርኅና በብሔራዊ ጥቅም መካከል ያለውን ዲያሌክቲካዊ አንድነት በመጠበቅ የሶሽያሊስት ግንባታቸውን ለማካሄድ በመቻላቸው ነው ። የሶሽያሊስት ሥርዓትን ለሚገነቡ አገሮች በወዝአደራዊ ዓለም አቀፋዊነትና በብሔራዊ ጥቅም መካከል ያለውን ዲያሌክቲካዊ አንድነት ማናጋት ማለት ወደ ብሔረተኝነት መዘፈቅና የሶሽያሊስት ግንባታን ማሰናከል ማለት ነው ። ለዚህ ጉልህ ማስረጃ የሚሆነው በቻይና ውስጥ አሁን ያለው ሁኔታ ነው ።

የሶሻሊስት አገሮች እስከአሁን ድረስ በተግባራቸው እንዳረጋገጡት በመካከላቸው የተፈጠረው ወንድማዊ አንድነትና መተባበር የእያንዳንዱን አገር ብሔራዊ ጥቅም የሚንከባከብ ነው ። ለሶሽያሊስት አገሮች ፣ ብሔራዊ ጥቅም ሲባል ሌላ የተለየ ነገር ሳይሆን በአብዮቱ የተገኙ ድሎችን መጠበቅና ማጠናከር ፣ የሶሻሊስት ግንባታን ሂደት በተሳካ መንገድ በአፋጣኝ ማከናወን ማለት ነው ። ይህ ብሔራዊ ጥቅም ሊሳካ የሚችለው ፣ በተግባርም እንደታየው ፣ የሶሻሊስት አገሮች በሚፈጥሩት የጋራ መተባበርና ዓለም አቀፋዊ አንድነት አንፃር ብቻ ነው ። የሶሻሊስት አገሮች ብሔራዊ ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ የቻሉትና የሚችሉት ሕዝቦቻቸው የሶሻሊስት ሥርዓትን ለማጠናከርና ለማሳደግ በአደረጉት ዓለም አቀፋዊ ትግል አማካይነት ነው ። የሶሻሊስት አገሮች ልምድ በተጨባጭ እንዳሰየን ብሔራዊ ጥቅምና ዓለም አቀፋዊነት ተጻራሪ አይደሉም ። ስለ ብሔራዊ ጥቅም ሲወሳ መደባዊ አቀራረብ ሊሰጠው ይገባል ። ብሔራዊ ጥቅም በሚል ሽፋን የቡርዧ መደብ አፈቀላጤዎች የመደብ ትግልን ለማከላሽ

ትና በኮሚዩኒስቶች መካከል መኖር የሚገባውን አንድነትና ትብብር ለማናጋት ይጥራሉ ። በማርክሲዝም ሌኒኒዝም ጽኑ እምነት ላላቸው ኮሚዩኒስቶች ግን ሐቀኛ ብሔራዊ ጥቅምና ዓለም አቀፋዊነት በጥብቅ የተቆራኙና ተደጋጋፊዎች ናቸው ።

ከወዳጅ ሶሻሊስት አገሮች ጋር የሚፈጠረው አንድነት አንድን አገር ማቴሪያልና ባሕላዊ ዕድገት የሚያመቻችና ከኢምፔሪያሊዝም ጥቃት አገሪቱን ለመከላከልም ዋናው ዋስትና ነው ። ይህንን መተሳሰር ማላላት በአገሪቱ የሚካሄደውን የሶሻሊስት ግንባታና ሶሻሊስታዊ ድሎች አደጋ ላይ መጣል ብቻ ሳይሆን ብሔራዊ ነፃነትንም አደጋ ላይ መጣል ይሆናል ። የሶሻያሊስቱን የዕድገት ፈለግ በመከተል ላይ ባሉ አገሮች የብሔራዊ ነፃነት መደፈር አደጋ ሊፈጥር የሚችለው ከሶሻሊስት አገሮች ጋር የተፈጠረው ጠንካራ አንድነት ሲናጋና ሲላላ ብቻ ነው ።

ከዓለም አቀፋዊነት አቋም ማፈንገጥ ማለት ብሔረተኝነትን በመቀስቀስ የመደብ እርቅ ማድረግ ማለት ነው ። በታሪክ ተደጋግሞ እንደታየው ቡርዧው በብሔራዊ ጥቅም ሽፋን የመደብ ጥቅሙን ሲያስከብር ቆይቶአል ። የማናቸውም ሐቀኛ አብዮት ድል ሊረጋገጥ የሚችለው ይኸው አብዮት በሚያካሄደው የማያሰልስ ፀረ-ኢምፔሪያሊስት ትግል ነው ። ይህ ደግሞ የኮሚኒስቶችን ጠንካራ ሶሻሊስታዊ ወንድማማችነትና አንድነትን ይጠይቃል ። እውነተኛውና ከፍተኛው ብሔራዊ ጥቅም ከአብዮቱና ከሶሻሊዝም ግቦች ጋር የተያያዙ ናቸው ። የሶሽያሊዝም ግቦች ተግባራዊነት ደግሞ ከዓለም አቀፋዊነት ጋር የተቆራኘ ነው ። ብሔረተኝነትን አጠናክሮ ዓለም አቀፋዊነትን ማዳከም የኋላቀር አገሮችን ኢኮኖሚ ለካፒታሊስቱ ዓለም ጥገኛ እንዲሆን ያደርጋል ። በፖለቲካ አንፃርም አድኃሪና አደገኛ ነው ፥ ምክንያቱም የተባበረ የኢምፔሪያሊዝምን ኃይል ለመቋቋም ሕዝቦችን እንደማስተባበር ፋንታ ይከፋፍላቸዋል ፥ በአገሪቱ የቡርዧ ብሔረተኝነት አዝማሚያ ያስፋፋል ፥ በመጨረሻም የተገኙትን አብዮታዊ ድሎች አደጋ ላይ ይጥላል ።»[14]

በመስከረም ቅጽ 1 ቁጥር 1 ላይ ይህን ጉዳይ በሚመለከት «በኮሚዩኒስት ንቅናቄ ውስጥ ብሔረተኝነት ከአድርባይነት ተነጥሎ የሚታይ አይደለም ። ሁለቱም አንድ ምንጭ አላቸው ። ብሔረተኝነት የሚን ፀባረቀው ብሔራዊ ጥቅምን ጠባብ በሆነ መንገድ በመመልከትና በመተርጎም ብሔራዊ ጥቅምን ከዓለም አቀፋዊነት በላይ ቅድሚያ ሰጥቶ የሠራተኞች የጋራ ዓላማና ፀረ-ኢምፔሪያሊስት ትግሉ ወደ ጎን ሲተው ነው ። ብሔረተኝነት የወዛደራዊ ዓለም አቀፋዊነትን መርኅ እንደ ዋናው የመደብ ትግልና የሶሻሊስት አብዮት መጣሪያ መሆኑን መዘንጋትን ያመለክታል ።...... በአጠቃላይ የጊዜውን ማኅበራዊ ክስተቶች መደባዊ ባልሆነ መንገድ መመልከትና ከዓለም አብዮታዊ ኃይሎች ጋር ለጋራ ዓላማ በአንድነት ተባብሮ ለመታገል ያለመፈለግን ያሳያል ።»[15] የሚል አስተያየት ሰፍሮ ይገኛል ።

ለማርክሲስቶች በአብዮታዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ብሔራዊና ዓለም አቀፋዊ ጥቅሞች የሚቃረኑ ሳይሆኑ በይዘታቸው አንድ ናቸው ። ማርክሲስቶች እውነተኛ አገር ወዳዶች ፥ የሕዝቡን ብሔራዊ ባሕሎች የሚጠብቁና የሚያሳድጉ ፥ ለዕድገት በሚጠቅምና የሕዝቡን አመለካከት አብዮታዊ በሆነ መንገድ ለመለወጥ በሚያምኑ መንገድ ብሔራዊ ታሪካቸውን በኩራት የሚመለከቱ ናቸው ። ሶሻሊዝምንም ሲገነቡ የአገራቸውን ልዩ ባሕሪ በማጥናት ነው ። የአገራቸውን ልዩ ባሕሪ ያጠናሉ ሲባልም የሶሺያሊስት ማኅበረሰብና ከዓለም የኮሚዩኒስትና የሠራተኛ እንቅስቃሴ ትምህርት አይወስዱም ማለት አይደለም ።

በአጠቃላይ ማናቸውም በአንድ አገር ክልል ውስጥ የሚካሄድ አብዮታዊ እንቅስቃሴ ዓለም አቀፋዊ ግዴታውን የሚያሟላው ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው በመጀመሪያ በአገሩ ክልል ውስጥ የካፒታልን አገዛዝ ሲገረስስ ፥ የሠርቶ አደሩን ሕዝብ የፖለቲካ ሥልጣን ሲመሠርትና የሶሽያሊስት ሥርዓትን ሲገነባ ነው ። ነገር ግን የአንድ ብሔራዊ አንቅስቃሴ ድል ሊረጋገጥ የሚችለው በዓለም አቀፍ ደረጃ በሶሽያሊዝምና በካፒታሊዝም መካከል በሚደረገው ትግል የሚገኘው ውጤትና ሌሎች አብዮታዊ ኃይሎች በሚያገኙት ድልና ውጤት አኳያ ነው ። ስለዚህም ነው እያንዳንዱ ብሔራዊ እንቅስቃሴ የራሱን ቀጥተኛ ፍላጎት እያሟላ በተጨማሪ ደግሞ በዓለም ላይ የሚገኙትን ለሶሺያሊዝም የሚታገሉ ኃይሎችን ባለው አቅም መርዳትና በአብዮታዊ ኃይሎች መካከል አንድነት እንዲኖር ጥረት ማድረግ ያለበት ።

ለማርክሲስቶች ወዝአደራዊ ዓለም አቀፋዊነት ፥ የአገሮች ነፃነትና ልዕልና የማይ

ገሰስ መሆኑን ፣ አንድ አገር ከሌላው አገር ጋር የሚፈጥረው ማናቸውም ግንኙነት በእኩልነትና በጋራ ጥቅም ላይ መመሥረት ያለበት መሆኑን የሚያጠቃልል ጽንሰ ሀሳብ ነው ። ይህ ጽንሰ ሀሳብ የመንግሥታትን ብቻ ሳይሆን የፓርቲዎችንም ግንኙነት ያጠቃልላል ። ይሁንና ለማርክሲስቶች የእኩልነት የነፃነት ወዘተ...... ጥያቄዎች ፍጹም እንደሆኑ ነገሮች የሚወሰዱ አይደሉም ። በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚካሄደውን የመደብ ትግል ለማፋፋም ፣ በአብዮታዊ ኃይሎች መካከል መኖር ለሚገባው የትግል አንድነት በሁሉም መስክ የመተባበርና የመረዳዳት ዓለም አቀፋዊ ግዴታ ተገዥ መሆን ይኖርባቸዋል ። በዓለም አቀፋዊውና በብሔራዊው ጥቅም መካከል ያለው ዲያሌክቲካዊ ግንኙነት በሚናጋበት ጊዜ ለብሔረተኝነት ማንሠራራት አመቺ ሁኔታ ይፈጠራል ።

በሀንጋሪ እ. ኤ. አ. በ1956 ፀረ-ሶሺያሊስት ኃይሎች «ብሔራዊ ጥቅምን» ለማስጠበቅ በሚል ሽፋን ተነሳሱ ። በኋላም ሶሻሊዝምን «ለማሻሻል» የሚል ፈሊጥ ይዘው የሶሻሊስት አገሮችን በማጥላላትና በተለይም ፀረ-ሶቪዬት አቋም በመያዝ ብዙ የሀንጋሪ ኮሚዩኒስቶች የተሰውለትን አብዮት ለመቀልበስ ሞክረው እንደነበር ይታወሳል ። በቸኮዝሎቫኪያም እ. ኤ. አ. በ1968 ሶሺያሊዝምን «ዲሞክራሲያዊ» ለማድረግ በሚል ሽፋን የቀኝ አድርባይ ኃይሎች የቼኮዝሎቫኪያን ሶሺያሊስታዊ ግስጋሴ ለማስናከልና የፓርቲውን መስመር ለመበረዝ ሙከራ አድርገው እንደነበር ይታወሳል ። በዚህም ሂደት ውስጥ ብሔረተኝነትን በመቀስቀስ ፀረ-ሶቪዬት ቅስቀሳ ያካሂዱ እንደነበር ይታወሳል ። ብሔረተኝነትና የቀኝ ክንፍ ከላሽነት ለአብዮት ቅልበሳ ሙከራ ዋና መሣሪያ እንደነበሩም የሚረሳ አይደለም ። አሁንም ቢሆን አድኃሪ ኃይሎች የተለመደውን የብሔረተኝነትን አርማ ይዘው በመነሳት የዓለም አብዮታዊ ኃይሎች አንድነት እንዳይኖራቸው ፣ ለኢምፔሪያሊዝም ጣልቃ ገብነትና ለፀረ-አብዮተኞች የቅልበሳ ሴራ የተጋለጡ እንዲሆኑ የመከፋፈልና የማዳከም ጥረታቸውን እያፋፋሙ ነው ። በብሔራዊ ነፃነት ፣ ብሔራዊ ጥቅምና ልዕልና በሚሉ ቃላት እየተጠቀሙ በየቦታው ፀረ-ሶሻሊስት ቅስቀሳቸውን በማካሄድ ላይ ይገኛሉ ።

ማ ጠ ቃ ለ ያ ፤

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ኢምፔሪያሊዝም የሶሺያሊዝምን ግሥጋሴ ለማገታት ፣ በሶሺያሊስት የዕድገት ጎዳና ላይ ያሉ አገሮች የሚያካሂዱትን አብዮት አቅጣጫ ለማዛባት በተለያየ መንገድ ትግል እንደሚያካሂድ ተመልክተናል ። ከሚያካሂደውም ትግልና ከሚያውጠነጥነው ሴራ መካከል ፣ በተለይ በርዕዮተዓለም የትግል ዘርፍ መስክ የሚጠቀምበትን የፀረ-ኮሚዩኒዝምና የሱም ዓይነተኛ መግለጫ የሆነውን የፀረ-ሶቪዬት ዘመቻውን ይዘት ለመገምገም ተሞክሯል ።

ኢትዮጵያም የሶሺያሊስት የዕድገት ፈለግን በመከተል የሶሺያሊስት ሥርዓት ለመገንባት በመታገል ላይ ያለች አገር እንደመሆኗ ፣ ኢምፔሪያሊዝም የኢትዮጵያን አብዮት ለመቀልበስ የተለያዩ የአብዮት ቅልበሳ ሙከራዎች ሰንዝሮባታል ። የውስጥ አድሀሪያንንና የውጭ ተስፋፊ ኃይሎችን በማስተባበር የሀገራችን ዳር ድንበር እንዲደፈርና አብዮታችን እንዲቀለበስ ከፍተኛ የፀረ-አብዮት ዘመቻ አካሂዶብናል ። ይህ ሁሉ ሙከራ አልሳካ ሲለው ደግሞ በአካባቢው ጣልቃ ገብ ጦሩን በማስፈር ከበባውን ከማጠናከሩም በላይ ፣ በኢትዮጵያ ውስጥ አብዮቱ ጥቅማቸውን የነካባቸው መደቦችና ክፍሎች ፣ እንዲሁም አስመሳዮች በኢምፔሪያሊዝም መናኛ የፀረ-ሶቪዬት ፕሮፓጋንዳ በመመራት ለኮሚዩኒዝም ያላቸውን ጥላቻ ለመወጣት ርካሽ አሉባልታ በማናፈስ ላይ ይገኛሉ ።

የኢትዮጵያ አብዮታውያን አድሀሪ ኃይሎች የሚያናፍሱትን የፀረ-ሶቪዬት አሉባልታ የማጋለጥና በሚያካሂዱትም የርዕዮተዓለም ትግል እርቃኑን ማስቀረት ይኖርባቸዋል ። በዚህም ሂደት ውስጥ አብዮቱ የመጣለት ሰፊ ሕዝብ የአብዮቱን የዘለቄታ ግብ እንዲገነዘብ ፣ የወዝአደራዊ ዓለም አቀፋዊነትን ጽንሰሀሳብ በሚገባ እንዲጨብጥና የብሔረተኝነትን አደጋ እንዲከላከል ፣ ፀረ-ኢምፔሪያሊስት ትግል ማለት ምን ማለት እንደሆነና እንዴትስ እስከ መጨረሻው ድረስ ለማራመድ እንደሚቻል ለማስገንዘብ መቻል ይኖርባቸዋል ።

በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ በኢትዮጵያ አብዮትና በሶሺያሊስት ማኅበረሰብ በተለይም በሶቪዬት ኅብረት መካከል ያለውን የትግል አንድነት በማዛባት የፀረ ሶቪዬት አሉባልታ ማናፈስ ማለት ፀረ-ሶሺያሊስት አቋም መያዝና የኢትዮጵያን አብዮት መጻረር ማለት ነው ። አብዮታችን አሁን በደረሰበት የዕድገት ደረጃ ደግሞ ከአድሀሪያን በስተቀር ፣ አብዮቱ ለመጣለት የሰፊው ሕዝብ ወገን ሁሉ እውነተኛ ሀገር ወዳድነት

በኢትዮጵያ ለሶሺያሊዝም ልዕልና የሚደረገውን ትግል ከመደገፍ ተገንጥሎ ሊታይ አይችልም ። ለሶሺያሊዝም የሚደረገው ትግል መደገፍና የፀረ-ሶቪዬት አቋም መያዝ ደግሞ ሊጣጣሙ እንደማይችሉ ቀደም ሲል በሰፊው ለማስረዳት ተሞክሯል ።

የኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ ካስተላለፋቸው ውሳኔዎች መካከል ፡«የኢትዮጵያ አብዮት ዛሬ የደረሰበት የዕድገት ደረጃ ላይ ሊደርስ የቻለው በሰፊው ሕዝብ ያልተቆጠበ ተጋድሎና መስዋዕትነት እንደዚሁም የሶሺያሊስት አገሮች እና ተራማጅ ኃይሎች ባደረጉት ትብብር መሆኑን ፡ ዓለም አቀፍ ኢምፔሪያሊዝምና አድሀሪ ኃይላት የሚያውጠነጥኑትን ፀረ እድገት ሤራና የሚሰነዝሩትን ጥቃት መከላከል የሶሺያሊስት ፡ የተራማጅና የሰላም ኃይሎች ሁሉ ዓለም አቀፋዊ ግዴታ ሲሆን ፡ ዋስትናቸውም የትግል አንድነታቸው ጥንካሬ ነው»[16] የሚሉ ይገኙበታል ።

በተለይ ደግሞ «የአብዮቶች ድል በሶሺያሊስት ኃይሎች አንድነት የሚወሰን እንደመሆኑ ፡ የሶሺያሊስት ሥርዓት ፡ የዓለም አቀፍ ኮሚዩኒስትና የሠራተኛ መደብ ንቅናቄ ይበልጥ መጎልበት እጅግ አስፈላጊ መሆኑን በማመን ፡ የመላው ሶሺያሊስት ካምፕና የአርነት ንቅናቄዎች መከታ ከሆነው ከሶቪዬት ኅብረት ፡ ማለትም ከሶቪዬት ኅብረት ኮሚዩኒስት ፓርቲ ፡ መንግሥትና ሕዝብ ጋር ፡ ከጎናችን ከቆሙት ወዳጅ ሶሺያሊስት አገሮችና ግንባር ቀደም ፓርቲዎቻቸው ጋር ፡ እንዲሁም ከሌሎች ለእውነተኛ ነፃነትና ለአርነት ከሚታገሉ ኃይሎች ጋር ያለን የትግል አንድነት ይበልጥ እንዲጠናከርና እንዲዳብር ማድረግ ፡»[17] (ስርዝ የተጨመረ) የሚለው የኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔ ፡ ኢሠፓአኮ በሶቪዬት ኅብረትና በኢትዮጵያ አብዮት መካከል ላለው የትግል አንድነት ይበልጥ መጠናከርና መዳበር ከፍተኛ ትኩረት የሰጠው መሆኑን ያመለክታል ።

በመሆኑም በኢትዮጵያ አብዮትና በሶቪዬት ኅብረት መካከል ያለውን የትግል አንድነትና ትብብር እንዲጠናከር መታገል የኢሠፓአኮን ተልዕኮ የማሳካቱ ተግባር አንድ አካል ነው ። በአንፃሩ ፡ የፀረ-ኮሚኒስት ዓይነተኛ መግለጫ በሆነው በፀረ ሶቪዬት ፕሮፓጋንዳ በመነዳት በሶቪዬት ኅብረት ላይ የአሉባልታ ዘመቻ ማካሄድ የኢሠፓአኮን ውሳኔ መጣስና የኢትዮጵያን አብዮት ሂደት መጻረር መሆኑን ግልጽ ማድረግ ያስፈልጋል ።

የግርጌ ማስታወሻ

1. Karl Marx and Frederic Engies, Communist Manifesto, p. 8.
2. *Ibid*, pp. 25-28
3. መስከረም መጽሔት ፤ ቅጽ 1 ፤ ቁጥር 1 ፤ ገጽ 52-53 «ወዝአደራዊ ዓለምአቀፋዊነት» ፤
4. *Right Wing Revisionism Today*, Moscow, Progress. Pub., 1976, p. 404.
5. Panomarev Boris, Lenin and the World Revolutionary Process, Progress Publishers, Moscow, 1980, pp. 155-156.
6. *Contemporary Anti-Communism: Policy and Ideology*, Progress Publishers, Moscow, 1976, pp. 32-33
7. መስከረም መጽሔት ፤ ቅጽ 1 ፤ ቁጥር 1 ፤ ገጽ 55 «ወዝአደራዊ ዓለምአቀፋዊነት» ፤
8. *Right Wing Revisionism Today*, Moscow, Progress Publishers, 1976, P. 405.
9. Lenin, Collected Works, Vol. 31, P. 100.
10. Moscow News, No. 10, March 8, 1971 P. 7
11. Lenin, Collected Works, Vol. 11, P. 109.
12. መስከረም መጽሔት ፤ ቅጽ 1 ቁጥር 1 ፤ ገጽ 54 «ወዝአደራዊ ዓለምአቀፋዊነት» ፤
13. ከዚሁ መጽሔት ፤ ገጽ 54 ፤
14. The Road to Communism, Moscow, P. 466.
15. መስከረም መጽሔት ፤ ቅጽ 1 ፤ ቁጥር 1 ፤ ገጽ 54 «ወዝአደራዊ ዓለምአቀፋዊነት» ፤
16. የኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች ፤ ገጽ 65፥
17. *Ibid*.

መስከረም

የማርክሲስት ሌኒኒስት ርዕዮተ ዓለም መጽሔት

ቅጽ 2 ቁጥር 6
መስከረም 1974

መስከረም

ቅጽ 2 ቁጥር 6
መስከረም 1974

የማርክሲስት ሌኒኒስት ርዕዮተዓለም መጽሔት

ማ ው ጫ

ገጽ

- የዝግጅት ገፅ - - - - - - - - - - - - - - - - - - 3

- የጊዜው የፀረ ኮምኒዝም ዋንኛው ገፅታ - - - - - - - - - - - - 7
  — ዳንኤል ገ/ኪዳን

- የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም በቀድመ አብዮት
  ኢትዮጵያ (ክፍል 2) - - - - - - - - - - - - - - - - 28
  — ዶ/ር ለገሠ ለማ

- ምሁርና አብዮታዊ ሚናው (ክፍል 2)
  የኢትዮጵያ ምሁር መደባዊ ጠባይና ሚናው - - - - - - - - - 53
  — ተስፋዬ ለማ

- የኢትዮጵያ አንድነት ታሪክ ፤ በኤርትራ ክፍለ ሃገር የመገንጠል
  እንቅስቃሴ አነሳስና የደረሰበት ደረጃ (ክፍል 2) - - - - - - 68
  — ግርማየ ገ/የሱስ

— የመስከረም መፅሄት ስድስተኛ አትም ሽፋን
  ዲዛይን ትርጉም - - - - - - - - - - - - - - - - - 96

በኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ

ርዕዮተዓለም መምሪያ እየተዘጋጀ በየሦስት ወር የሚወጣ ።

አድራሻ

የፖስታ ሣጥን ቁጥር — 80001
የስልክ ቁጥር — 113000

የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም በቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ

(ክፍል 2 እ.ኤ.አ. ከ1950ዎቹ የመጀመሪያ ዓመታት እስከ 1974)

ለገሠ ለማ

የዚህ ጽሑፍ የመጀመሪያ ክፍል በዚሁ መጽሔት ቅጽ 1 ቍጥር 3 ላይ መውጣቱና ትኩረቱም እ. ኤ. አ. ከ1900 እስከ 1950ዎቹ የመጀመሪያ ዓመታት ያለው ጊዜ መሆኑ ይታወሳል ። በጽሑፉ የመጀመሪያ ክፍል መደምደሚያ ላይ እንደተገለጸው ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ በማያወላውል አኳኋን የካፒታሊስቱን ዓለም መሪነቱን ከእንግሊዝ የተረከበችው ዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ በኢትዮጵያ ቀንደኛ ኢምፔሪያሊስትነቱንም እንደዚሁ ከእንግሊዝ በ1950ዎቹ የመጀመሪያ ዓመታት ልትረከብ ቻለች ።

ይህ ሁለተኛው የጽሑፉ ክፍል የሚያተኩረው በተለይ በአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝምና በኃይለ ሥላሴ መንግሥት መካከል ከ1950ዎቹ መጀመሪያ ዓመታት እስከ አብዮታችን ፍንዳታ ድረስ ተጠናክሮ የነበረው ሽርክና ላይና ከዚህም የሰፊውን ሕዝብ ጥቅም አሳልፎ በመስጠት ከዳበረው ሽርክና የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝምና የኃይለ ሥላሴ መንግሥት ያገኙት ጥቅም ላይ ይሆናል ። እንደ ዲፕሎማሲ ፤ ሚሊተሪ ፤ ኢኮኖሚ ፤ ባሕልና ትምህርት ያሉ የግንኙነት መስኮች በጽሑፉ ውስጥ ይዳሰሳሉ ። ከአብዮቱ ፍንዳታ ቀደም ብለው ባሉት ጥቂት ዓመታት ውስጥ ታይተው የነበሩ የሁለቱን አገሮች ግንኙነቶች የሚመለከቱና ከአብዮቱ ፍንዳታ ጋር ቀረብ ያለ ዝምድና ያላቸውን አንዳንድ ጉዳዮችም ለማብራራት ሙከራ ይደረጋል ።

ሀ. የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም አምባገነንነት በኢትዮጵያ

«ሚስተር ፖል ። ለኢትዮጵያ የምንሰጠው ዕርዳታ እኛ ከአገሪቱ ከምናገኘው ጥቅም ይበልጣል ብለህ ታምናለህ ?

ሚስተር ቤደር ። የለም ፤ አላምንም ።''

ከዚህ በላይ የተገለጸው ውይይት የተካሄደው እ. ኤ. አ. በ1970 በንድ የአሜሪካ ምክር ቤት የውጭ ግንኙነት ኮሚቴ ባልደረባና የአሜሪካ የመከላከያ ሚኒስቴር ባልደረባ በሆነው በጆርጅ ቤደር መካከል ነበር ። በእነዚህ ቃላቶች በመጀመር የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝምና

የኃይለ ሥላሴ መንግሥት ከግንኙነታቸው ምን ምን እንዳገኙ ይዘረዝራል ። የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም ከሽርክናው ያገኘው ጥቅም በርካታ ነው ። ቀደም ሲል በኤርትራ አቋቁሞት የነበረውን የሚሊተሪ መገናኛ ጣቢያ ሊያስፋፋና ለፀረ ኮምዩኒዝምና ለፀረ ሕዝብ ዓላማው ሊገለገልበት ችሏል ። የኢትዮጵያን ወታደሮች በዓለም አቀፍ ለሚያካሂዳቸው ጦርነቶች ከጎኑ ያሰለፈበት ጊዜም ነበር ። የመካከለኛው ምሥራቅንና አፍሪካን በሚመለከት ለሚከተለው ፖሊሲ ኢትዮጵያን ተገልግሎባታል ። ኢትዮጵያ በሯን ለኢምፔሪያሊዝም በተለይም ለአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም የኢኮኖሚ ብዝበዛና የባሕል ተጽዕኖ ወለል አድርጋ እንድትከፍት መገደዷም በአገሪቱ የኢኮኖሚና የባሕል የውጭ ግንኙነት ላይ የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም የበላይነቱን እንዲይዝ አድርጎታል ። በአንፃሩ የኃይለ ሥላሴ መንግሥት በብዝበዛና በጭቆና ላይ ተመሥርቶ የነበረውን የአገዛዙን ዕድሜ ለማራዘም ያገለገለው የሚሊተሪና የኢኮኖሚ ዕርዳታ አግኝቷል ።

የቃኘው ሚሊተሪ መገናኛ ጣቢያ

የአሜሪካ ኢምፔሪያሊስቶች በኢትዮጵያ ውስጥ ካገኙዋቸው ጥቅሞች ምናልባትም የአንደኛውን ደረጃ ሊይዝ የሚችለው አሥመራ አጠገብ አቋቁመው ሲገለገሉበት የቆዩትና ኋላም ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት እንዲዘጋ ያደረገው የቃኘው ሚሊተሪ መገናኛ ጣቢያ ነው ። አሜሪካ ይህን ጣቢያ ያቋቋመችው እ. ኤ. አ. በ1940ዎቹ የመጀመሪያ ዓመታት ኤርትራ በእንግሊዝ ኢምፔሪያሊዝም አስተዳደር ሥር እንደወደቀች ነበር ። በዚህ ጽሑፍ የመጀመሪያ ክፍል እንደተገለጸው እ. ኤ. አ. በ1953 ፤ ማለት ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር በተዋሀደች በዓመቱ ፤ በኢትዮጵያና በአሜሪካ መካከል በተደረገ የመከላከያ ስምምነት መሠረት ጣቢያውን የማስፋፋትና እ. ኤ. አ. እስከ 1978 ድረስ በጣቢያው የመገልገል መብት ለአሜሪካ ተሰጠ ።

የቃኘው ጣቢያ ተልዕኮ ምን ነበር ? ጣቢያው መረጃዎችን በማስተላለፍ ላይ ያተኮረ ወታደራዊ ተቋም ነበር ። እ. ኤ. አ. በ1970 በተጻፈ ሪፖርት መሠረት ጣቢያው «አሜሪካ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያስፋፋቻቸው የስለላና የግንኙነት ጣቢያዎች አካል» ነበር ። «ለአሜሪካና ለተቀረው የካፒታሊስቱ ዓለም መከላከያ አስፈላጊ የሆኑ ፈጣን ወታደራዊ ነክ የሬዲዮ መልዕክቶችን ለመጥለፍና መረጃዎችን ለማግኘ» አገልግሏል። በአፍሪካ አካባቢ ለሚገኙ የአሜሪካ ዲፕሎማቲክ ጽሕፈት ቤቶችና ወታደራዊ ተቋሞች የሬዲዮ ግንኙነት አገልግሎት መስጠትና መልዕክቶችን ከአሜሪካና ከአውሮፓ ተቀብሎ ወደ ሕንድ ውቅያኖስ አካባቢና ከዚያም አልፎ ወደ ሩቅ ምሥራቅ ማስተላለፍ የጣቢያው ተቀዳሚ ተግባር ነበር ። ከጣቢያው ተጨማሪ ተግባሮች መካከል «ስለተፈጥሮ የኤሌክትሮኒክ ክስተቶች ቁጥጥርና ምርምር ማድረግ» ይገኛል ።[2] ሌተና ጄኔራል ኤች ኤም ፊሽ የተባለ አንድ የአሜሪካ የመከላከያ ሚኒስቴር ከፍተኛ ባለሥልጣን ባቀረበው ሪፖርት መሠረት በቃኘው ይገኝ የነበረው የአሜሪካ የባሕር ኃይል ጣቢያ ፤ በፋርስ ባሕረ ሰላጤ አካባቢ ለሚገኙ የጦር መርከቦች እንቅስቃሴ ድጋፍ ከመስጠቱና ለአሜሪካ ፕሬዚዳንት የሚላኩ መልእክቶችን ተቀብሎ ከማስተላለፉም በላይ በአፍሪካ ፤ በመካከለኛው ምሥራቅ ፤ በፋርስ ባሕረ ሰላጤና በደቡብ እስያ ሊሰማራ የሚችል ፈጣን ጣልቃ ገብ ጦር ለማስተናገድ የሚያስችል ዝግጅት ነበረው ።[3] አንድ የዓለም ወታደራዊ ጉዳይ ላይ የሚያተኩር መጽሔት ፤ የቃኘው ጣቢያ የሬዲዮ መልዕክቶችን በመቀበልና በማስተላለፍ ችሎታው በዓለም ውስጥ ከሚገኙ ተመሳሳይ ጣቢያዎች መካከል ከፍተኛው መሆኑን እ. ኤ. አ. በ1972 አረጋግጧል ። ይኸው መጽሔት በተጨማሪ ሲያትት ጣቢያው ለአሜሪካ የጠፈር ግንኙነቶች ፤ እንዲሁም የሶቪዬት ኅብረትን የሮኬት ሙከራዎችና ስትራተጂያዊ ግንኙነቶች ለመቆጣጠር አገልግሏል ።[4] አሥመራን ለጣቢያው መመሥረቻ ካስመረጧት ምክንያቶች ውስጥ ከምድር ወገብ አካባቢ መገኘቷ ለሬዲዮ ግንኙነት አመቺ ያደረጋት መሆኗ ፤ ከፍታዋና መልካም የአየር ጠባይዋ ይገኛሉ ።[5] ምንም እንኳ የአሜሪካ መንግሥት የቃኘው ጣቢያ ይሰጥ የነበረው በተለይ የመገናኛ አገልግሎት በቴክኖሎጂ ዕድገት ምክንያት አክትሟል ብሎ በመለፈፍ[6] እ. ኤ. አ. ሐምሌ 1 ቀን 1974 የሚዘጋ መሆኑን አንድ ዓመት ያህል ቀደም ብሎ ቢያስታውቅም በጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ እንዲዘጋ እስኪታዘዝበት እስከ እ. ኤ. አ. ሚያዝያ 1977 ድረስ[7] ጣቢያውን አልዘጋም ነበር ።

የአሜሪካ ኢምፔሪያሊስቶች በቃኘው ጣቢያ አከማችተዋቸው ከነበሩት የስለላ መሣሪያዎች ውስጥ አንዳንዱን በይበልጥ ይተማመኑባቸው ለነበሩት እንደ አስራተ ካሣ ላሉት ተባባሪዎቻቸው ያስጉበኙ ነበር

የኢትዮጵያን ወታደሮች ከኢትዮጵያ ውጭ በማዝመት የአሜሪካን ተልዕኮ እንዲያሟሉ ስለማድረጉ

በአሥመራ ውስጥ ተቋቁሞ የነበረው የቃኘው የጦር ሠፈር ቃኘው ተብሎ የተሰየመው እ. ኤ. አ. በ1950ዎቹ የመጀመሪያ ዓመታት በኮሪያ ጦርነት ተሳትፎ በነበረው በቃኘው ባታሊዮን ጦር ስም መሆኑ የአሜሪካ ኢምፔሪያሊስቶች ከኢትዮጵያ ወደ አገኙት ሌላ መከላከያ ነክ ጥቅም ያሸጋግረናል ። እ. ኤ. አ. በ1950ዎቹ እና በ1960ዎቹ ዓመታት ውስጥ ኢትዮጵያ በሁለት ጦርነቶች ውስጥ ማለትም በኮርያና በኮንጎ (የዛሬይቱ ዛየር) ጦርነቶች ከድንበሯ ክልል ውጭ ተሳትፋለች ። ኢትዮጵያ በእነዚህ ጦርነቶች በተለይም በኮርያው ጦርነት ውስጥ ያደረገችው ተሳትፎ ከኢምፔሪያሊዝም ፤ በተለይም ከአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም ጥቅምና ፍላጐት ጋር የተቆራኘ ነበር ። ለምሳሌ የአሜሪካ ጦር ሠራዊት የውጭ ወታደራዊ ዕርዳታ ዲሬክተር ፤ ጄኔራል ሮበርት ጄ ውድ ለኢትዮጵያ ይሰጥ የነበረው ወታደራዊ ዕርዳታ መቀጠል ያለበት መሆኑን በማስገንዘብ እ. ኤ. አ. በ1966 ከዘረዘራቸው ምክንያቶች መካከል የሚከተለው ይገኛል ፤

«ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ ትኩረት ተጥሎባቸው በነበሩ ጉዳዮች ላይ ለአሜሪካ ከፍተኛ ድጋፍ ስትሰጥ ቆይታለች። በኮርያ ጦርነት ወቀት የምድር ጦሯን ስትልክ ፤ በኮንጎ ደግሞ የምድር ጦሯና የአየር ኃይሏ የተባበሩት መንግሥታትን ጥረት ረድቷል ።»[8]

ለረጂም ጊዜ የኃይለ ሥላሴ አማካሪ በመሆን ሲያገለግል የነበረው አሜሪካዊው ጆን ስፔንሰር ኢትዮጵያ በኮርያ ጦርነት ውስጥ የተሳተፈችበትን ምክንያት አስመልክቶ ሲገልጽ ፤ «ኢትዮጵያ በኮርያ ጦርነት ለመሳተፍ ከኔቶ አባል አገሮች ውጭ ሆነው በአካባቢዋ ከሚገኙት መካከል ብቸኛዋ ለመሆን ችላለች ። በአሜሪካ ወታደራዊ ዕዝ ሥር ለነበረውና ኮርያ ለዘመተው የጦር ኃይል ወታደሮቿን የላከችበት ምክንያት እ. ኤ. አ. በ1950 በተባበሩት መንግሥታት ውስጥ ኤርትራንና ኦጋዴንን በሚመለከት አሜሪካ ለኢትዮጵያ ድጋፍ ስጥታ ስለነበር ወሮታ ለመመለስ ነው»[9] ብሎ ነበር ። ኃይለ ሥላሴም በበኩሉ ወታደሮች ወደኮርያ የላከበት ምክንያት በአጠቃላይ ከካፒታሊስቱ ዓለም ፤ በተለይም ከአሜሪካ ጋር የነበረውን ሕብረት ለማጠናከር መሆኑን እ. ኤ. አ. በ1954 በሚከተሉት ቃላቶች በአሜሪካ ምክር ቤት ውስጥ ገልጿል ።

«ይህ (የኢትዮጵያ) ከምዕራቡ በተለይም ከዩናይትድ ስቴትስ ጋር ማበር (ከኤርትራ ጉዳይ) ሰፋ ያለ ቀርጽ እየያዘ መጥቷል። በመካከላችን የተፈረመው የሚሊተሪ ስምምነት አለ ። ግሪክንና ቱርክን የሰሚን አትላንቲክ የጦር ቃል ኪዳን አባላት አድርገን ብንወስዳቸው ኢትዮጵያ የዩናይትድ ስቴትስን ምሳሌነት ተከትላ ጦሯን ወደኮሪያ ለመላክ ከመካከለኛው ምሥራቀ ሀገሮች ውስጥ ብቸኛ ሆናለች ።[10]

ቍጥራቸው 1,158 የሆነ እግረኛ ወታደሮችን የያዘው ቃኘው ሻለቃ ጦር እ. ኤ. አ. በግንቦት ወር 1951 ደቡብ ኮርያ ደረሰ ። በሚቀጥለው ዓመት በመጋቢት ወር 612 ተጨማሪ ወታደሮች ወደ ኮርያ አመሩ ። እ. ኤ. አ. በታኅሣሥ ወር 1952 በተጠናቀረ ሪፖርት መሠረት ኢትዮጵያ በኮርያው ጦርነት 80 ወታደሮች ሲሞቱባት ፤ 347 ቆስለውባታል ። አንድም ወታደር ግን አልተማረከባትም ። በዚህ አኳኋን ኢትዮጵያ ከደቡብ አፍሪካ ሌላ ብቸኛዋ የአፍሪካ ሀገር በመሆን በኮርያው ጦርነት በቀጥታ ተካፍላለች ።[11]

በኮንጎ ሊዮፖልዲቪልም (የአሁኗ ዛየር) ኢትዮጵያ ተዋጊ ኃይሏን ልካ ነበር ። እዚህ ላይ በመጀመሪያ ማስታወስ የሚገባው የኢትዮጵያ ወታደሮቿን ወደ ኮንጎ መላኳ ሁለት ገጽታዎች ያሉት መሆኑን ነው ። ቦአንድ በኩል የኮንጎ መንግሥት በአገሪቷ ውስጥ ተናግቶ የነበረውን ፀጥታ ለማስከበር የተባበሩት መንግሥታትን ወታደራዊ ዕርዳታ በጠየቀው መሠረት የተከናወነ በመሆኑ ለአፍሪካ ሰላምና ብልጽግና የቆመ ማናቸውም ኃይል ሊደግፈው የሚገባ ነው ። በሌላ በኩል ግን ይህንኑ የሰላም ጥረት ኢምፔሪያሊስቶች በተለይም የአሜሪካ ኢምፔሪያሊስቶች የራሳቸውን ጥቅም በኮንጎ ውስጥ ለማስከበሪያ ሊጠቀሙበት መሯሯጣቸው አልቀረም ። ይህንን ነጥብ ግልጽ ለማድረግ ይቻል ዘንድ እ. ኤ. አ. በ1960ዎቹ የመጀመሪያ ዓመታት ኮንጎን አጋጥሟት የነበረውን ችግር ባጭሩ መቃኘት ያስፈልጋል ። እ. ኤ. አ. በሰኔ 30 ፤ 1960 ኮንጎ ከቤልጅግ ቅኝ አገዛዝ ነፃነቷን እንደተጎናፀፈች በየእርስ በርስ ጦርነት ተጥለቀለቀች ። ወዲያውኑ የቤልጅግ መንግሥት በአዲሲቱ ኮንጎ ሪፐብሊክ ውስጥ ይገኙ የነበሩ የቤልጅግ ዜጎች ደህንነት አደጋ ላይ ወድቋል በሚል ሳቢያ የጦር ኃይሉን ወደ ኮንጎ ላከ ። ሐምሌ 12 ቀን 1960 የሶቪዬት ኅብረት ጠቅላይ ሚኒስትር የነበሩት ክሩቼቭ ቤልጅግ ከሰ

ሜን አትላንቲክ የጦር ቃል ኪዳን ሀገሮች ጋር በማበር ያደረገችውን ጣልቃ ገብነት አውግዘው የተባበሩት መንግሥታት የቤል ጅግን ወረራ እንዲያቆም በሚቀጥለው ቀን ጠየቁ ። ሐምሌ 14 ቀን 1960 በፕሬዚዳንት ካዛቩቡና በጠቅላይ ሚኒስትር ሉሙምባ የሚመራው የኮንጎ መንግሥት የቤልጅግን ወረራ ለመቋቋም ከሶቪዬት ኅብረት ርዳታ ጠይቆ ለመርዳት ፈቃደኛነቷን ሶቪዬት ኅብረት በሚቀጥለው ቀን ገለጸች ። የኮንጎ መንግሥት የሶቪዬት ኅብረትን ዕርዳታ በጠ የቀበት ቀን የተባበሩት መንግሥታት የፀ ጥታው ምክር ቤት ወደ ኮንጎ የጦር ኃይል ለመላክ ወሰነ ። በዚሁ ቀን ሐምሌ 14 ፤ 1960 ኢትዮጵያ ወታደሮቿን ወደኮንጎ እንደምትልክ በማስታወቅ ድጋፏን ሰጠች[12] በዚህ መሠረት 3,200 ወታደሮችን፤በዚያው ዓመት ከዩናይትድ ስቴትስ ካገኘቻቸውና ኤንኤፍ-86ኤፍ ከተባሉት 14 የጦር አው ሮፕላኖች ውስጥ አራቱን፣ ሌሎች ቦም ብ ጣይ አውሮፕላኖችን በመላክ በጦርነቱ ተሳተፈች።[13] ወታደሮች ወደኮንጎ የተላኩት ከአፍሪካ አገሮች ብቻ ነበር ። የኢምፔሪ ሪያሊስት አገሮች በተለይም የአሜሪካ ተቀ ዳሚ ፍላጐት በኮንጎ ሰላም እንዲሰፍን ሳይ ሆን በአገሪቷና በሶቪዬት ኅብረት መካከል የነበረው ግንኙነት እንዳይጠናከር ማድረግ ነበር ። የአሜሪካ ተቀዳሚ ዓላማ ይኸው መሆኑን ለመረዳት የቀድሞው የኒው ዮርክ ገዥ የነበረው ደብሊዩ ኤቨረል ሐሪማን በዚያን ጊዜ የዲሞክራቲክ ፓርቲው እጩ ፕሬዚዳንት የነበረውን ጆን ኤፍ ኬኔዲን በመወከል ኮንጎን ጎብኝቶ ሲመለስ በመስ ከረም 1960 ለንደን ከተማ ለእንግሊዝ የዜና ወኪሎች በተናገረው ቃል ምዕራቡ ዓለም «ወደኋላ ገሸሽ በማለት ኮንጎ በሶቪዬት ኅብረት እንድትወሰድ አይፈቅድም»[14] ማለ ቱን መጥቀስ ይበቃል ።

የኃይለ ሥላሴ መንግሥት በመካከ ለኛው ምሥራቅ የአሜሪካ ኢምፔሪ ሪያሊዝምን ፖሊሲ አራማጅነት

የአሜሪካ ኢምፔሪያሊስቶች በመካከ ለኛው ምሥረቅ የሚከተሉትን ፖሊሲ እን ዲያራምድላቸው የኃይለ ሥላሴን መንግ ሥት ከጎናቸው አሰልፈው ነበር ። ይህም በተለይ እ. ኤ. አ. በ1956 ግብፅ የስዊዝ ቦይን በቍጥጥሯ ሥር በማዋልዋ ምክንያት ከኢምፔሪያሊዝም ጋር የነበራት ቅራኔ በተ ካረረበት ወቅትና በሚቀጥለው ዓመት «የአ ይዘንሐወር ዶክትሪን» በተሰኘ ስም ዋሽን ግተን ለመካከለኛው ምሥራቅ የቀየሰውን ፖሊሲ በሚመለከት ረገድ በግልጽ የታየ ነው ።

የስዊዝ ቦይ ብጥብጥ የተጀመረው የግ ብፅ ተራማጅ ፕሬዚዳንት ገማል አብደል ናስር እንግሊዝና ፈረንሣይ በንብረትነት ይዘውት የነበረውን የስዊዝ ካናልን ኩባንያ እ. ኤ. አ. ሐምሌ 26 ቀን 1956 ከወረሰ በኋላ ነው ። ቦዩ ከመወረሱ በፊት የነበሩ ትን አንዳንድ ሁኔታዎች መቃኘት ጉዳዩን በበለጠ ለመረዳት ያስችላል ።

በ1955 የእሥራኤል የጦር ኃይል ጋዛ የሚገኘውን የግብፅ የጦር ምሽግ ካጠቃ በኋላ ፤ ግብፅ ወደፊት በጥጥ የሚከፈል የጦር መሣሪያ ለማግኘት የሚያስችላት ውል ከሶቪዬት ኅብረት ጋር ተዋዋለች ። በሁለቱ አገሮች መካከል በተደረገው በዚህ መቀራረብ በመደናገጥ እንግሊዝ ፤ ዩና ይትድ ስቴትስና የዓለም ባንክ የአስዋንን ግድብ ለማሠራት የሚያስችላት የገንዘብ ዕርዳታ እንደሚያደርጉላት በዚያው ዓመት መጨረሻ ለግብፅ ገለጹ ። ነገር ግን በግን ቦት ወር 1956 ግብፅ ቀደም ሲል 10 ሚሊ ዮን ፓውንድ የሚያወጣ ጥጥ የገዛቻትን የቻይናን ሕዝባዊ ሪፐብሊክ በማወቋ ዩና ይትድ ስቴትስ ለአስዋን ግድብ ማሳሪያ ልትሰጣት ቃል የገባችውን ዕርዳታ ላለ መስጠት መወሰኗን አስታወቀች ። እንግሊ ዝና የዓለም ባንክም የዩናይትድ ስቴትስን ፈለግ በመከተል ላለመርዳት ወሰኑ ። ከዚ ህም በኋላ ግብፅ ከቦዩ በሚገኝ ገቢ ግድቡን አሠራለሁ በማለት የስዊዝ ቦይን ወረሰች ። በዚህ ጽሑፍ ውስጥ እንግሊዝ ፈረንሣይና እሥራኤል ቦዩ እንደተወረሰ በግብፅ ላይ የፈጸሙትን ወረራ በስፋት ለማየት ሙከራ አይደረግም ።ሆኖም በፈቃዳቸው የተነሳሱ ተዋጊዎችን ወደግብፅ ለመላክ ማቀዷን ሶቪዬት ኅብረት በማስታወቋ ሶስቱ ኢም ፔሪያሊስት አገሮች በግብፅ ላይ የሰነዘሩትን ወረራ ለማቆም መገደዳቸውን መጥቀስ ተገ ቢ ነው ።[15] የኃይለ ሥላሴ መንግሥት የነበ ረው ሚናም ዩናይትድ ስቴትስና ተባባሪ ዎቿ ቦዩን ከግብፅ በመንጠቅ "ዓለም አቀፋ ዊ ቁጥጥር» በሚል ሳቢያ እንደገና በቁጥ ጥራቸው ሥር ለማዋል አድርገውት ከነ በረ መፍጨርጨር ጋር የተያያዘ ነበር ።

ኢትዮጵያ በዚህ በስዊዝ ቦይ ብጥብጥ ውስጥ እጇን ያስገባችው በነሐሴ ወር 1956 ለንደን ከተማ ውስጥ ስለቦዩ ጥያቄ ስብሰባ በተካሄደበት ጊዜ ነበር ። ይህ ስብ

ሰባ የተቀነባበረው በዩናይትድ ስቴትስ ፤ በእንግሊዝና በፈረንሣይ መንግሥታት ሲሆን «የቦዩ በሥራ ላይ መዋል በይበልጥ የሚመለከታቸው» በሚል ሳቢያ እነዚሁ ኢምፔሪያሊስት አገሮች የመረጧቸው አገሮችም በስብሰባው ላይ እንዲገኙ ጥሪ ተደርጎላቸው ነበር ። ኢትዮጵያ በስብሰባው ከተካፈሉ ሃያ ሁለት አገሮች አንዷ ከመሆኗም በላይ የዩናይትድ ስቴትስ መንግሥት የቀየሰውንና «ቦዩ ዓለም አቀፋዊ ቁጥጥር ይኑረው» የሚለውን ሃሣብ ከደገፉት ከአሥራ ስምንቱ አገሮች አንዷ ሆናለች ። እንዲያውም በጊዜው የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበረውና ሀገሪቱን ወክሎ በስብሰባው የተካፈለው አክሊሉ ሀብተወልድ ስብሰባው ያሳለፈውን ውሣኔ ለግብፅ መንግሥት ለማስማት የተሰየመ ኮሚቴ አባል በመሆን አገልግሏል ። በመስከረም ወር 1956 አሥራ ስምንቱ ሀገሮች በለንደን ከተማ ሁለተኛውን ስብሰባ አድርገው "የስዊዝ ቦይ ተጠቃሚዎች ማኅበር" ለማቋቋም ያሰቡ መሆናቸውን አስታወቁ ። የማኅበሩም ዓላማ የአባላቱን በቦዩ የመጠቀም መብት ለማስከበር ነው በማለትም ለፈፉ ። አሥራ ስምንቱ አገሮች ፤ ኢትዮጵያም ጭምር ፤ በተገኙበትና በጥቅምት 1956 ለንደን በተደረገው በሦስተኛው ስብሰባ "የስዊዝ ቦይ ተጠቃሚዎች ማኅበር" ተመርቆ ተከፈተ ። እርግጥ ግብፅ በቦዩ ላይ ያላትን ቁጥጥር እያጠናከረች በመሄዷ ይህ ማኅበር ወዲያውኑ ሊፈርስ ችሏል ። የኃይለ ሥላሴ መንግሥትም ግብፅ በተለይ በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ሊኖራት የሚችለውን ተጽዕኖ በመገመት በማኅበሩ ውስጥ ሙሉ ተሳትፎ ለማድረግ የወሰነ መሆኑን በይፋ አልገለጸም ።[16] ሆኖም የኃይለ ሥላሴ መንግሥት በስዊዝ ቦይ ብጥብጥ ጊዜ ተከትሎት የነበረው ፖሊሲ የኢምፔሪያሊስቶችን ጥቅም የሚያራምድና በአንፃሩም በጊዜው ራሷን ከኢምፔሪያሊስቶች ብዝበዛ ለማላቀቅ ከፍተኛ ጥረት ታደርግ የነበረችውን አፍሪካዊት አገር የግብፅን ጥቅምና ነፃነት የሚፃረር እንደነበረ አያጠራጥርም ።

በ1956 የተነሣው የስዊዝ ካናል ብጥብጥ ዩናይትድ ስቴትስ በመካከለኛው ምሥራቅ አካባቢ የምታደርገውን እንቅስቃሴ እንድታሳድግ አደረገ ። በአካባቢው የአሜሪካን የበላይነት ለማረጋገጥ ፕሬዚዳንት አይዘንሐወር የመካከለኛውን ምሥራቅ የሚመለከት አንድ መልዕክት ለአገሩ ምክር ቤት በጥር ወር 1953 አስተላለፈ ። ይህ «የአይዘንሐወር ዶክትሪን» በመባል የታወቀው ፖሊሲ ፤ «(በመካከለኛው ምሥራቅ) አካባቢ የሚገኙ አገሮች በዓለም አቀፍ ኮምዩኒዝም ጥላ ሥር ካሉ አገሮች ወረራ ቢቃጣባቸው አሜሪካ ዕርዳታና ትብብር ለማድረግ ዝግጁ መሆኗን የሚገልጽና የዕርዳታውም ዓይነት የአሜሪካን ወታደሮች በጦርነቱ ማሰማራትን» እንዲጨምር ለማድረግ ብቻ ሣይሆን «በአካባቢው ለሚገኝ አገር ወይም አገሮች የሚሊተሪ ዕርዳታና የትብብር ፕሮግራም ለማካሄድም» የሚያስችል ነበር ። በሚቀጥለው ወር የአሜሪካ መንግሥት የመካከለኛው ምሥራቅ አገሮች ናቸው ያላቸውን አገሮች ስም ዝርዝር ሲያወጣ ኢትዮጵያንም በስም ዝርዝሩ ውስጥ አስገባት ። በመጋቢት ወር የአሜሪካ ምክር ቤት አይዘንሐወር የቀየሰውን ፖሊሲ በማጽደቅ ለዚሁ ተግባር ሁለት መቶ ሚሊዮን ዶላር ወጭ እንዲሆን ፈቀደ ።[17]

«የአይዘንሐወር ዶክትሪን» መቀየስ በኃይለ ሥላሴ መንግሥትና በአሜሪካ መካከል የነበረውን ግንኙነት ይበልጥ አጠናከረው ። ይህ ፖሊሲ ይፋ በወጣ በወሩ በአውሮፓ የአሜሪካ ጦር ምክትል አዛዥ፣ ጄኔራል ዲከር አዲስ አበባ መጥቶ ከኃይለ ሥላሴ ጋር ሲገናኝ የአሜሪካ ምክትል ኤታማዦር ሹም ሌተና ጄኔራል ክለድ ኢድልማንም በጊዜው የኢትዮጵያ መከላከያ ሚኒስትር ከነበረው ከአበበ አረጋይ ጋር ውይይት አካሄደ ። እንዲሁም በመጋቢት ወር በዚያን ጊዜ የአሜሪካ ምክትል ፕሬዚዳንት የነበረው ሪቻርድ ኒክሰን «በተለይ በመካከለኛው ምሥራቅ ብጥብጥ ሳቢያ የኢትዮጵያን ስትራተጂያዊ ጠቃሚነት ዋሽንግተን የተረዳው መሆኑን ለማሳየት» ኢትዮጵያን ጐበኘ ። ከኒክሰን ጉብኝት በፊትም ቢሆን የኢትዮጵያ ንጉሥ «የአይዘንሐወርን ዶክትሪን» በደስታ መቀበሉን ለኒውዮርክ ታይምስ ጋዜጣ ወኪል ፤ ለሆመር ቢጋርት በሰጠው ቃለ መጠይቅ በማረጋገጥ ፤ «የአይዘንሐወርን የመካከለኛው ምሥራቅ ወታደራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕርዳታ ፕሮግራም ኢትዮጵያ በደስታ ተቀብላዋለች . . ለዕቅዱም ተባባሪ መሆን የኛ ጽኑ ምኞት ነው» ብሎ እንደነበር የሚታወስ ነው ። በተጨማሪም የአሜሪካ ምክር ቤት የውጭ ጉዳይ ኮሚሽን ሊቀመንበርና በኋላም የፕሬዚዳንቱ የመካከለኛው ምሥራቅ ጉዳይ ልዩ ረዳት የነበረው ጀምስ ሪቻርድስ በሚያዝያ ወር አዲስ አበባን በጎበኘበት ወቅት «የኢትዮጵያ መንግሥት . . . ለአሜሪካ ዶክትሪን (ፖሊሲ) ሙሉ ድጋፉን እንደሰጠ» ተናግሯል ። ሚስተር ሪቻርድስም በበኩሉ የዩናይትድ ስቴትስ መንግሥት

ለኢትዮጵያ ተጨማሪ የኢኮኖሚ ና ወታደ ራዊ ዕርዳታ መስጠት ያለበት መሆኑን ገልጾነበር ።[18]

የኃይለ ሥላሴ መንግሥት በአፍሪካ የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝምን ፖሊሲ አራማጅነት

እ. ኤ. አ. ከ1957 በኋላ ኢትዮጵያ የአ ሜሪካን ፖሊሲ ለማራመድ ከመካከለኛው ምሥራቅ ይልቅ በአፍሪካ አህጉር ጉዳይ ብታተኩር የሚሻል መሆኑ እየጎላ መጣ ።

«በዚያ አጭር ጊዜ (1956—57) ውስጥ ናስር የስዊዝን ወረራ ተቋቋመ ፤ ጠንካራና ገለልተኛ የሆነ የዓረብ ንቅናቄ እንደሚኖርም ግልጽ ሆነ ። በዚያኑ ወቅት እንግሊዝ ለጋና ነፃነቷን ለመስጠት መገደዷ የአፍሪካን ከቅኝ አገዛዝ ቀንበር መላቀቅ እያፋጠነው ሄደ ። ከፍተኛ እንቅስቃሴ በአህጉሩ ውስጥ እንደ ሚካሄድ ግልጽ ነበር ። . . . ኢትዮጵያም በመካከለኛው ምሥራቅ አነስተኛ ሚና በመ ጫወት ፈንታ በአፍሪካ አህጉር ውስጥ ከፍ ተኛና የአደራጅነት ሚና ለመጫወት ወሰ ነች ።»

ኢትዮጵያ በጥቁር ሕዝቦች መካከል ባላት የተለየ ሥፍራ ምክንያት «አህጉር የመቀየሩ» ጉዳይ ለኃይለ ሥላሴ መንግሥት ብዙም አዳጋች አልሆነበትም ነበር ። ኢትዮጵያ ኮሎኒያሊዝምንና በቀለም ልዩ ነት ላይ የተመሠረተ ጭቆናን ለመቋቋም ያደረገችው ተጋድሎ በጥቁር ሕዝቦች መካ ከል ልዩ ሥፍራ ሊያሰይዛት ችሏል ። የአው ሮፓ ኢምፔሪያሊስት አገሮች በተያያዝ ነው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ ላይ አፍሪ ካን በመካከላቸው ቆራርሰው ሲያበቁ በው ጭ ካፒታል ቁጥጥር ሥር ከነበረችው ከላይ ቤሪያ በስተቀር የፖለቲካ ነፃነቷን እስከ ብራ የተገኘች አፍሪካዊት አገር በአድዋ የኢጣሊያን የመስፋፋት ዓላማ ያከሸፈችው ኢትዮጵያ ብቻ ነበረች ።

በዚህ አኳኋን ከአፍሪካ ሀገሮች መካ ከል በብቸኛነት የፖለቲካ ነፃነቷን ጠብቃ የቆየችውን ኢትዮጵያን እ. ኤ. አ. በ1935 ፋሺስት ኢጣሊያ በግፍ መውረሯ ብዙ ሕዝቦችን በተለይም ጥቁር ሕዝቦችን እጅግ አስቆጥቶ እንደነበር የሚ ታወስ ነው ። በፋሺስት ኢጣሊያ ወረራም ጊዜ ኢትዮጵያውያን ያሳዩት ጀግንነት የአገሪ ቷን ዝና እጅግ ከፍ ከማድረግ ተርፎ በሽሽት እንግሊዝ አገር ቆይቶ የተመለሰውን ኃይለ ሥላሴን እንኳ በአገሪቷ ስም ክብር እንዲያ ገኝ አድርጎት ነበር ። ይህን ኢትዮጵያ በአ ፍሪካ አህጉር ውስጥ ያላትን ልዩ ቦታ በመ ገንዘብ እ. ኤ. አ. በ1958 የአፍሪካ የኢኮ ኖሚ ኮሚሽንና በ1963 የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ጽ/ቤቶች እንዲቋቋሙባት የአፍ ሪካ ሀገሮች አዲስ አበባን ሊመርጧት ችለ ዋል ።[19]

የኃይለ ሥላሴ መንግሥት የአሜሪካን ፖሊሲ በአፍሪካ ለማራመድ ያደረገውን አስተዋጽኦ በአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒ ስቴር የአፍሪካ ጉዳይ ረዳት ኃላፊ የነበረው ዴቪድ ኒውሶም እ. ኤ. አ. በ1965 በሚቀ ጥሉት ቃላት አስቀምጦታል ።

በ1950 ዎቹ ዓመታት የአፍሪካ አገሮች ከቅኝ አገዛዝ ቀንበር መላቀቅ ጀመሩ ። በብ ዙዎች አመለካከት በነዚህ ዓመታት ውስጥ አፍሪካ ባልለየለት ሁኔታ ውስጥ ተንጠልጥላ ትገኝ ነበር ። . . . ሶቪዬቶች አዲስ ነፃ በወጡ አገሮች ውስጥ ተጽእኖአቸውን ለማስፋፋት በማሰብ ከፃር ሆነው ሁኔታውን ያጤኑ ነበር ። . . . በአፍሪካ የሚገኙ ተስፈንጣሪዎችም ከተ ጨባጭ ሁኔታዎች የራቁ ዕቅዶችን ይቀይሱና መፈክሮችን ይደረድሩ ነበር ።

በዚህ አስጊ ወቀት የንጉሡ (የኃይለ ሥላሴ) ክብርና ድምፅ አዲሶቹ መንግሥታት ኃላፊነት የሚሰማቸው እንዲሆኑ ለማድረግ በጣም ረድቷል ። በአፍሪካ አገሮች ውስጥ መረጋጋት እንዲሰፍንና አፍሪካ ዓለም አቀፍ ትግል ውስጥ እንዳትገባ የሚፈልጉ መንግሥ ታት ሁሉ ፤ የኛም መንግሥት ሳይቀር ፤ ባለ ውለታው ናቸው ።[20]

ከአምስት ዓመታት በኋላም በአሜሪካ የጦር ሠራዊት ውስጥ የጦር ተራድኦ ዲሬ ክተር የነበረው ፤ ጄኔራል ሮበርት ጀ ውድ እንዲህ ብሎ ነበር ፤

«ኢትዮጵያ በጥቁር አፍሪካ ካሉት መን ግሥታት ሁሉ ይበልጥ የተረጋጋች አገር ነች ብለን እናምናለን ። ኃይለሥላሴ ለአፍሪካ አመራር ዓይነተኛ ኃይል ነው ። በአፍሪካ መን ግሥታት መካከል መልካም አዝማሚያን ያሰ ራጫል ። . . . ይህ ሁሉ አገሪቷ ተረጋግታ እን ድትቀይና የጦር ኃይሏ እንዲጠናከር ለማ ድረግ በቂ ምክንያት ነው ።»[21]

ጄኔራሉ ፤ ንጉሡ «በአፍሪካ መንግሥ ታት መካከል መልካም አዝማሚያን ያሰራ

ጫል» ሲል ምን ማለቱ እንደሆነ በሚገባ ለመረዳት ቀደም ሲል የአፍሪካን አንድነት ለመመሥረት ጥረት ሲደረግ የነበሩ አንዳንድ ሁኔታዎችንና ውዝግቦችን መለስ ብሎ መመልከቱ ተገቢ ይሆናል ። አንደኛው አመለካከት የአፍሪካን አንድነት በአስቸኳይ ተግባራዊ ማድረግን የሚደግፍ ሲሆን በግልጽ ፀረ ኢምፔሪያሊስት የሆነና በጋናው ፕሬዚዳንት በክዋሚ ንክሩማ የሚመራ ነበር ። ሌላው ደግሞ በኃይለ ሥላሴ የሚመራና «ኅብረት ቀስ በቀስ» በተሰኘ መርህ ላይ የተመሠረተ ነበር ። ጋናና ጊኒ «የምዕራብ አፍሪካ መንግሥታት አንድነት ጽንስ» ለመሆን ዕቅድ እንዳላቸው እ. ኤ. አ. በ1958 አስታውቀው ነበር ። ከሁለት ዓመታት በኋላ ደግሞ ጋና ፤ ጊኒና ማሊ «በጋራ የዲፕሎማቲክ ውክልናና በጋራ የኢኮኖሚና የገንዘብ ፖሊሲ ላይ የተመሠረተ . . . አንድነት ለመፍጠር ወስነው ነበር ።» እ. ኤ. አ. በጥቅምት ወር 1961 በነዚህ በሦስቱ አፍሪካ አገሮች በሥልጣን ላይ የነበሩት ፓርቲዎች ሞስኮ ላይ በተደረገው የ22ኛው የሶቪዬት ኅብረት ኮምዩኒስት ፓርቲ ጉባኤ ላይ «ብቸኛ ኮምዩኒስት ያልሆኑ ፓርቲዎች» በመሆን ተካፈሉ ። በዚሁ ዓመት ንክሩማ የሌኒንን የሰላም ሽልማት ከሶቪዬት ኅብረት ተቀበለ ።[22]

የአፍሪካ አንድነት ድርጅት እ. ኤ. አ. በግንቦት ወር 1963 አዲስ አበባ ላይ በተመሠረተበት ወቅት በአፍሪካ መሪዎች መካከል የነበሩት ሁለቱ የተለያዩ አመለካከቶች በንክሩማና በኃይለ ሥላሴ ተገልጸው ነበር ። በጋናና በጊኒ የሚመራ የአፍሪካን አንድነት ምሥረታ ስለመቃወም ከደጎል ጋር ፓሪስ ላይ እ. ኤ. አ. በ1959 ውይይት አድርጎ የነበረው ኃይለ ሥላሴ[23] «እኛ የምንፈልገው አንድነት ተግባራዊ ሊሆን የሚችለው ቀስ በቀስ ብቻ ነው» በማለት ተናገረ ። ንክሩማም ይህን የዝግታ እርምጃ አመለካከት በመቃወም በዚያን ጊዜ እንዲህ ሲል ሃሣቡን አቅርቧል ።

«ይህ አመለካከት (ማለትም የአፍሪካን ኅብረት በዝግታ መፍጠር) በአህጉራችን ላይ የሚሰነዘሩ የውጭ ግፊቶችን በትክክል አያጤንም ። በጊዜ መጓተት የተነሣ መነጣጠላችንና ግለኝነታችን በመባባስ ልዩነታችንን አስፍቶ ወደ እጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ መረብ ውስጥ ሊያስገባን እንደሚችልም አያገናዝብም ።''

የጋናው ፕሬዚዳንት «በአፍሪካ ከፍተኛ ዕዝ የሚመራና የአፍሪካን መረጋጋትና ደህንነት የሚያረጋግጥ የጋራ መከላከያ ተቋም» ያቀፈ የአፍሪካ መንግሥታት አንድነት ድርጅት «እዚሁና አሁኑኑ» እንዲቋቋም ፤ እንዲሁም አፍሪካን «ከኑክሌር ነፃ ክልል»[24] የሚያደርጋት መግለጫ እንዲወጣ ጠየቀ ። በተለይ በመጨረሻ የተጠቀሰውን የንክሩማን ጥያቄ ተግባራዊ ለማድረግ በጊዜው በአፍሪካ አህጉር የነበሩትን የባዕድ ጦር ሠፈሮች (በኤርትራ ይገኝ የነበረውንም ጭምር) መዝጋት አስፈላጊ መሆኑ ግልጽ ነው ።

የ«ክፍት በር» ፖሊሲ

የውጭ ንግድና መዋዕለ ንዋይን በሚመለከት ኢትዮጵያ ታራምደው የነበረው የ«ክፍት በር» ፖሊሲ በወቅቱ ከነበረውና ለወደፊትም ከታቀደው በተለይ ከአሜሪካ መንግሥትና ባጠቃላይም ከበለጸጉት የካፒታሊስት አገሮች ጥቅም ጋር የተቀናጀ ነበር ። ኢትዮጵያ ለውጭ ካፒታል የማታስፈራ ቦታ መሆኗን ኃይለ ሥላሴ በመኩራራት እንደሚከተለው ገልጾት ነበር ።

«የውጭ ካፒታሊስቶች ከሕዝባችን ጋር ተባብረው እንዲሠሩ ወይም ገንዘባቸውን በዕድገት መስክ በግላቸው እንዲያውሉ ማበረታታችንን አቋርጠን አናውቅም . . . የውጭ ሰዎችን ንብረት ከሕግ ውጭ መውረስ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ታይቶ አይታወቅም ። ይህም ለኢትዮጵያ የኩራት ምንጭ ነው ።»[25]

የውጭ ካፒታል በኢትዮጵያ ውስጥ ደህንነቱ በሚገባ ከመጠበቁም በላይ በመዋዕለ ንዋይ ሕግም አንፃር ልዩ አስተያየት ሲደረግለት ቆይቷል ። እ. ኤ. አ. በ1963 «የውጭ አገርና የሀገር ውስጥ ገንዘብ (ካፒታል) በኢትዮጵያ ውስጥ በልማት ሥራ ላይ እንዲውል ለማበረታታት» በወጣው አዋጅ መሠረት የአልኮል መጠጥን ከሚያመርቱት በስተቀር አዲስ የተቋቋሙ ድርጅቶች ሁሉ በሀገሪቱ ውስጥ ከ200,000 ብር ያላነሰ ገንዘብ በሥራ ላይ ካዋሉ ለአምስት ዓመታት ከገቢ ቀረጥ ክፍያ ነፃ ሆነዋል ። ቀደም ሲል የተቋቋሙ ድርጅቶች ደግሞ ሥራቸውን ለማስፋፋት 400,000 ብር በሥራ ላይ ካዋሉ ለሶስት ዓመታት ከገቢ ቀረጥ ክፍያ ነፃ ሆነዋል ። ከውጭ የሚገቡ የእርሻና የኢንዱስትሪ ማሽኖች እንዲሁም የኢንዱስትሪ ሕንፃዎችን ለመገንባት ከውጭ የሚገቡ ቁሶች ሁሉ ከውጭ በሚገቡ ዕቃዎች ላይ ከሚከፈሉት ቀረጦች

ነፃ ሆነዋል ። በአገር ውስጥ ተመርተው ወደ ውጭ የሚላኩ ዕቃዎችም እንዲሁ ከውጭ ንግድ ቀረጥ ነፃ የመሆን ዕድል ነበራቸው ። ማንኛውም የውጭ ካፒታሊስት በልማት ሥራ ካዋለው ገንዘብ የሚያገኘውን ትርፍ ወደአገሩ ለማስተላለፍ ወይንም ድርጅቱን በከፊልም ሆነ በሙሉ በሸጠ ወይንም ሂሣቡን ባጣራ ጊዜ ከዚሁ የሚገኘውን የተጣራ ገንዘብ ለመውሰድ ፤ ወይንም በልማት ሥራ ላይ ለዋሉ ዕቃዎች መለዋወጫ ዕቃዎችና ለሥራው አስፈላጊ ለሆኑ ሌሎች ልዩ ልዩ ዕቃዎች መግዣ የሚያስፈልግ የውጭ ምንዛሪ የማስተላለፍ መብት ያለገደብ ተሰጥቶት ነበር ። የውጭ ምንዛሪ ከኢትዮጵያ ማስወጣትን ከሚመለከቱ ሌሎች ጉዳዮች መካከል የውጭ ካፒታሊስት ከውጭ አገር የሚዋዋለው ብድር ወለድና የዋናውም ብድር ክፍያ ፤ እንዲሁም የውጭ ካፒታሊስቱ ያቋቋመው ድርጅት የሚቀጥራቸው የውጭ አገር ሠራተኞች ከሚያገኙት ደመወዝ አጠራቅመው ወደአገራቸው መላክ ይገኛሉ ። በተጨማሪም ለውጭ ካፒታሊስቶች የልማት ሥራ ድርጅት ለማቋቋሚያ የሚያስፈልግ መሬት የማግኘት መብት ተሰጥቷቸው ነበር ።

እርግጥ የኃይለ ሥላሴ መንግሥት አውጥቶት የነበረው ይህ ድንጋጌ በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ ገደብ ጥሎ ነበር ። ለምሳሌ ድርጅቶቹን ለማቋቋም ለሚያስፈልጉ ሕንፃዎች ሥራ የሚያገለግሉ መሣሪያዎች ከውጭ ቀረጥ ነፃ ሊገቡ የሚችሉት የእነዚህ ዓይነት የሕንፃ ሥራ መሣሪያዎች በኢትዮጵያ ውስጥ የማይሠሩና በውጭ ካፒታል የሚካሄዱ ድርጅቶች ምርታቸውን ለውጭ ገበያ ከቀረጥ ነፃ የሚልኩት ዕቃዎቹ በውጭ አገር ገበያ ሊወዳደሩ እንዲችሉ ከቀረጥ ነፃ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ መሆኑ ተገልጿል ። ሆኖም የኃይለ ሥላሴ መንግሥት በውጭ ካፒታል ላይ ያደርገው የነበረው ገደብ በአጠቃላይ ሲታይ እጅግ አነስተኛ እንደነበረ ግልጽ ነው ። የሕጉ ሁኔታ ለውጭ ካፒታል በኢትዮጵያ ውስጥ መስፋፋት ይበልጥ አመቺ እየሆነ መምጣቱንም ለመረዳት ያህል ቀደም ሲል የተቋቋሙ ድርጅቶች ለተወሰነ ጊዜ ከገቢ ቀረጥ ክፍያ ነፃ ለመሆን የሚያበቃቸው አዲስ በሥራ ላይ የሚያውሉት ገንዘብ መጠን እ. ኤ. አ. በ1965 ከ400,000 ብር ወደ 200,000 ብር ዝቅ ማለቱን[26] መጥቀስ ይበቃል ።

በኢትዮጵያ ውስጥ ስለግል ድርጅቶች ጉዳይ ከላይ የተጠቀሱት መንግሥታዊ ሕጎች ሁለት ፍሬ ነገሮችን ይዘዋል ። አንደኛ ፤ በአገር ውስጥ ካፒታሊስቶችና በውጭ አገር ካፒታሊስቶች መካከል ምንም ዓይነት ልዩነት ባለመኖሩ ዓለም አቀፋዊና ጠንካራው ካፒታል ከደካማውና ከአገር ውስጥ ካፒታል ጋር «ነፃ ውድድር» እንዲያካሂድ አስችሎታል ። ሁለተኛ ፤ ከገቢ ታክስና ከመሳሰሉት ድርጅቶችን ነፃ ስለማድረግ ጉዳይ በልዩ ልዩ ድርጅቶች መካከል የተደረገ ምንም ዓይነት ልዩነት አልነበረም ። ከፍተኛ አትራፊዎች የሆኑና ዝቅተኛ አትራፊዎች የሆኑ ፤ ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገባና ቅድሚያ ሊሰጣቸው የማይገባ ድርጅቶች ሁሉ ለዚህ ጉዳይ በአንድነት ይታዩ ነበር ። በሌላ አነጋገር የውጭ ካፒታልን በሚመለከት ረገድ የኃይለ ሥላሴ መንግሥት ይከተለው በነበረ የ«ክፍት በር» ፖሊሲ ላይ ምንም ዓይነት ገደብ አልነበረም ቢባል ከእውነት የራቀ አይሆንም ።

ኢትዮጵያ ለውጭ ካፒታል በሯን ወለል አድርጋ እንድትከፍት በተለይ የአሜሪካ መንግሥት ከፍተኛ ግፊትና ጥረት አድርጓል ። ለምሳሌ እ. ኤ. አ. በ1943 በአሜሪካና በኢትዮጵያ መካከል የተፈረመውን የዕርዳታ ስምምነት በማስመልከት ሁለቱ መንግሥታት የተለዋወጧቸው ማስታወሻዎች «ማንኛውም አገር ለዓለም ንግድና ጥሬ ዕቃዎች» በር ሊከፈትለት የሚገባ መሆኑን ገልጸዋል ። እ. ኤ. አ. በ1953 በሁለቱ መንግሥታት መካከል የተፈረመው «የጋራ መከላከያ ኃይል የርዳታ ስምምነት'' የአሜሪካ መንግሥት የሚፈልጋቸውና በኢትዮጵያ ውስጥ ሊገኙ የሚችሉ ጥሬ ዕቃዎችና ያላለቀላቸው ዕቃዎች እንዲመረቱና ወደአሜሪካ እንዲላኩ እንዲደረግ» የኢትዮጵያን መንግሥት ቃል አስገብቶት ነበር ። በተጨማሪም «ለሰላም በዓለም መስፈን እንቅፋት በሚሆኑ አገሮች ላይ የንግድ ግንኙነትን የመቆጣጠር እርምጃ አሜሪካ ብትወስድ እንድትተባበራት» ማስታወሻዎቹ ኢትዮጵያን አስገድደዋታል ።[27] በመጨረሻ የተጠቀሰው በሶሻሊስት አገሮች ላይ የተተለመ መሆኑን የሚጠቁመው ለምሳሌ ቀደም ሲል እ. ኤ. አ. መስከረም 12 ቀን 1951 የዩናይትድ ስቴትስ ብሔራዊ የፀጥታ ምክር ቤት «የኬም ማሻሻያ የተባለውንና ከአሜሪካ ዕርዳታ የሚሹ አገሮች ለሶሻሊስት አገሮች መሸጥ የማይችሏቸውን ዕቃዎች ስም ዝርዝር የያዘውን ደንብ» በተግባር ከተረጎሙ ሃያ ሁለት አገሮች መካከል ኢትዮጵያን መጥቀሱ ነው[28]

ሆኖም ከዚህ በላይ ከተጠቀሰትና በሁለቱ መንግሥታት መካከል ከተፈረሙት

በምምነቶች መካከል እ. ኤ. አ. መስከረም 7 ቀን 1951 የተፈረመውን «የወዳጅነትና የኢኮኖሚ ግንኙነት ውል» ኢትዮጵያን የ«ክፍት በር» ፖሊሲ እንድትከተል በማ ድረግ ረገድ የሚወዳደር አንድም አይገኝ ። ሂሪ ማግዶፍ «ያለማወላወል ክፍት በር» ውሎች በማለት በአንድነት ከዘረዘራቸው ውሎች ውስጥ የሚገኘው ይህ በአሜሪካና በኢትዮጵያ መካከል የተፈረመው ውል ፤ ለአሜሪካውያን ወደ ኢትዮጵያ የመግባትና በኢትዮጵያ ውስጥ ተንሰራፍቶ የመኖር መብት ፤ በኢትዮጵያ ውስጥ ለራሳቸውና ለንብረታቸው የደኅንነት ዋስትና ፤ ከማን ኛውም የባለቤትነትና የአስተዳደር ጣልቃ ገብነት ነፃ በሚሆኑ ድርጅቶች በኢትዮጵያ ውስጥ በኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የመሳተፍ መብት ፤ የፓቴንት መብቶች ፤ የውጭ ምን ዛሪ ከኢትዮጵያ ውስጥ ያለገደብ የማውጣ ትና በንግድና በባሕር ላይ ጉዞ ለማንኛውም ሦስተኛ አገር የሚደረግ ሁሉ እንዲደረግ ላቸው የመጠየቅ መብት ሰጥቷቸዋል ። ይህ ውል በዚህ ሳያበቃ ከኢትዮጵያ መን ግሥት ልዩ አስተያየት ከተደረገላቸው የመ ንግሥት ድርጅቶች ፤ ሞኖፖሎችና ሌሎች ድርጅቶች ጋር በግዥና በሽያጭ ለመወዳ ደር የሚያስችለው «በቂ ዕድል» ለአሜሪካ ካፒታል ሰጥቷል ።

በተጨማሪም ሁለቱ መንግሥታት በ 1951 ከፈረሙት ውል ጋር በአባሪነት የተ ፈራረሟቸውና የኢትዮጵያን ፍርድ ቤት የሚመለከቱ ማስታወሻዎች ነበሩ ። ያንዱን አገር መብት ለሌላው አገር አሳልፎ የመስ ጠት ይዘት ያለውና በይዘቱ እ. ኤ. አ. በ1942 እና በ1944 በኢትዮጵያና በእንግ ሊዝ መካከል ተፈርመው ከነበሩት ስምም ነቶች ጋር ተመሳሳይነት ያለው ይህ አባሪ አሜሪካውያን ዘመናዊ ፍርድ ቤት አገል ግሎትና የሕግ አስተዳደር እንዲያገኙ እንድ ታደርግ ፤ በከፍተኛው ፍርድ ቤት ውስጥ ከሚሰየሙ ዳኞች አንዱ በሌሎች አገሮች የዳኝነት ልምድ ያለው እንዲሆን የመጠ የቅ መብት ለአሜሪካውያን እንድትሰጥ ፣ አሜሪካውያንን የሚመለከቱ የፍርድ ቤት ጉዳዮች ከዝቅተኛ ፍርድ ቤቶች ወደከፍተ ኛው ፍርድ ቤት እንዲዛወሩ የማድረግ እና አሜሪካውያን በኢትዮጵያ ውስጥ ቢታሠሩ የዘመናዊ እሥር ቤቶች አስተዳደር ልምድ ባለው ሰው ብቃቱ ከተረጋገጠ እሥር ቤት ውስጥ ብቻ እንዲታሠሩ የመጠየቅ መብት እንድትሰጥ ኢትዮጵያን አስገድዷታል ።[29] ኢትዮጵያ የዚህ አባሪ ተግባራዊነት እንዲ ያበቃ አሜሪካን የጠየቀችው ምንም እንኳ እ. ኤ. አ. መስከረም 16 ቀን 1965 ቢሆንም በዚህ ጉዳይ የአሜሪካ መንግሥት የተስማ ማው እ. ኤ. አ. ጥቅምት 16 ቀን 1972 ነበር ። እ. ኤ. አ. ጥር 26 ቀን 1973 ፕሬዚ ዳንት ኒክሰን ለአሜሪካ ምክር ቤት የሕግ መወሰኛ ስለዚህ ጉዳይ በላከው ደብዳቤ ፤ የተባለው አባሪ ተግባራዊነቱ እንዲያበቃ ለማድረግ የወሰነው አሜሪካ ከሌሎች አገ ሮች ጋር የምታደርገውን ስምምነት በእኩ ልነት ላይ የመመሥረት ፖሊሲ ስለምት ከተል ነው ማለቱ[30] በሁለቱ አገሮች መካ ከል የነበረው ስምምነት ቢያንስ እ. ኤ. አ. እስከ 1972 ድረስ በእኩልነት ላይ ያልተ መሠረተ እንደነበር ፕሬዚዳንቱ በይፋ የተ ቀበለው መሆኑን ያስገነዝበናል ።

የ«ክፍት በር» ፖሊሲንና የአሜሪካን ካፒታል ደህንነት በኢትዮጵያ ውስጥ ለማ ስከበር የሚያስችል የሕግ መሠረት ለመ ጣል በሁለቱ አገሮች መካከል እ. ኤ. አ. በ1951 የተፈረመው ውል ለአሜሪካ መን ግሥት በቂ አልነበረም ። በተጨማሪ እ. ኤ. አ. በ1962 እና በ1968 የካፒታል ደህንነት ዋስትና ስምምነቶች በሁለቱ አገሮች መካ ከል መፈረም ነበረባቸው ። በእነዚህ ስምም ነቶች አማካኝነት ባንድ በኩል የአሜሪካ መንግሥት በኢትዮጵያ ውስጥ ገንዘባቸ ውን በሥራ ላይ ለሚያውሉ አሜሪካው ያን ግለሰቦችና ኩባንያዎች የኢትዮጵያን ገንዘብ ወደውጭ ምንዛሪ ለመለወጥ ባለመ ቻላቸውና ድርጅቶቻቸው ወደኢትዮጵያ መንግሥት ባለቤትነት በመዛወራቸውና በ መንግሥት በመወረሳቸው ሊመጣ ስለሚ ችል ኪሣራ ዋስትና ሲሰጥ ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ከላይ የተጠቀሱት ችግሮች ደርሰው ባቸው የአሜሪካ መንግሥት ለዜጎቹና ለአ ገሩ ኩባንያዎች ክፍያ ቢያደርግ ይህንኑ ለአሜሪካ መንግሥት ለመክፈል የኢትዮ ጵያ መንግሥት ተስማምቶ ነበር ።[31]

ንግድና ዕርዳታ

አሜሪካ የኢትዮጵያን የውጭ የኢኮኖሚ ግንኙነት በተለይም የንግድና የዕርዳታውን ዘርፍ በቁጥጥሯ ሥር አውላው ነበር ። የኢ ትዮጵያና የአሜሪካ የንግድ ግንኙነት በዚሁ ወቅት ከፍተኛ ዕድገትን ሊያሳይ ቻለ ። እ. ኤ. አ. በ1951 አሜሪካ የገዛችው ከጠቅ ላላው የኢትዮጵያ የውጭ ንግድ 7.7% ያህሉን ብቻ ነበር ። ይህ ድርሻ በ1955 ወደ 25.2% ፤ በ1960 ወደ 39.4% ፤ እን ዲሁም በ1965 ወደ 53.5% ከፍ አለ ። ኢት ዮጵያ ከአሜሪካ የገዛቻቸው ዕቃዎች መጠን ግን በተጠቀሰው በእያንዳንዱ ዓመት ከነ

በረው ጠቅላላ የገቢ ንግድ መጠን ከ20% ያነሰ ነበር ።[32] የአሜሪካ ኢምፔሪያሊስቶች አፍሪካ ውስጥ ለነበራቸው ፖሊሲ በመሣሪያነት ካገለገላቸው ከኃይለ ሥላሴ መንግሥት ጋር የነበራቸው የንግድ ግንኙነት በዚህ አኳኋን የተዛባ ቢሆንም ፤ በአጠቃላይ ከአፍሪካ አህጉር ጋር የነበራቸውና ያላቸው የንግድ ሚዛን ለነርሱ የሚያደላ መሆኑን በዚህ አጋጣሚ መጥቀስ ተገቢ ነው ።

ኢትዮጵያ መጠኑ የማይናቅና ዕድገትን የሚያሳይ የውጭ ዕርዳታ ማግኘት የጀመረችው አሜሪካ በኢትዮጵያ ውስጥ ቀንደኛ ኢምፔሪያሊስትነቱን ከእንግሊዝ ከተረከበች በኋላ ነበር ። እ. ኤ. አ. ከ1944—74 ባለው ጊዜ ከልዩ ልዩ አገሮችና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ለኃይለ ሥላሴ መንግሥት ከተፈቀደ የሁለት ቢሊዮን ብር ያህል ብድር ውስጥ ከአሜሪካ የተገኘው 22% ፤ እንዲሁም ወጪ ሆኖ ከተሠራበት ከጠቅላላው 37% ነበር ። ምንም እንኳን ከሶሻሊስቱ ዓለም ለኢትዮጵያ የተፈቀደው ከጠቅላላው 26% ቢሆንም ወጭ ሆኖ የተሠራበት ከጠቅላላው 10% ብቻ ነበር ።[33] የዚህ ዋና ምክንያት በኃይለ ሥላሴ መንግሥት ላይ የነበረ የአሜሪካ ተጽእኖ መሆኑን ለመረዳት እ. ኤ. አ. በ1959 ሶቪዬት ኅብረት ለኢትዮጵያ ብድር ለመስጠት እንደተስማማች ይህ ስምምነት የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ከሶሻሊስቱ ዓለም ጋር የበለጠ ሊያቆራኝ ይችላል የሚል ስጋት በአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ላይ የደረሰ መሆኑን[34] መጥቀስ በቂ ነው ።

አሜሪካ ለኢትዮጵያ ትሰጠው የነበረው ብድር ከአጠቃቀሙ አንፃር ሲታይ ግን ቁሳዊ ምርት በቀጥታ የሚመረትባቸውን የኢኮኖሚ መስኮች ችላ ያለና መከላከያና መገናኛ ላይ ያተኮረ ነበር ። አሜሪካ ከሰጠችው ጠቅላላ ብድር 55% ለትራንስፖርት መገናኛ ሲውል ኢንዱስትሪን ለማስፋፋት የዋለው 3% ብቻ ነበር ። ማዕድን ለመፈለግና ለማውጣት የተሰጠ ምንም ብድር አልነበረም ።

ከአሜሪካ ተገኝቶ የነበረው ብድር በኢትዮጵያ ውስጥ ኢንዱስትሪን ለማስፋፋት ለምን በበለጠ ለመዋል እንዳልቻለ ለመረዳት ይቻል ዘንድ የአሜሪካ መንግሥት እ. ኤ. አ. በ1959 ለአንድ ኢትዮጵያ ውስጥ ለሚገኝ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ ሰጥቶ የነበረውን አነስተኛ ብድር በማስመልከት በ1962 በአሜሪካ ምክር ቤት ውስጥ የሰሜን ካሮላይና ተወካይ ሂዩግ አሌግዛንደር ፤ ሲናገር ፤ «ምንም እንኳ ብድሩን ያገኘው ፋብሪካ የሚያመርተው ጨርቃ ጨርቅ የሚሸጠው አገሩ ውስጥ ቢሆንና የአሜሪካ ጨርቃ ጨርቅ ኩባንያዎችን ከአገሩ ክልል ውጭ ገበያ ሊሻማቸው ባይችልም ፤ እዚያው አገር ውስጥ ገበያ ሊሻማቸው ስለሚችል የዚህ ዓይነት ብድር ወደፊት እንደማይሰጥ እርግጠኛ ነኝ» ሲል የተናገረውን መጥቀስ ተገቢ ነው ።

ኤ. አይ. ዲ. በመባል የሚታወቀው የአሜሪካው ዓለም አቀፍ ዕርዳታ ሰጭ ድርጅት በኢትዮጵያ ውስጥ የነበረው እንቅስቃሴ በትምህርትና በጤና ላይ ያተኮረ ነበር። ይህንንም አድራጎት በመደገፍ በአሜሪካ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የአፍሪካ ጉዳይ ቢሮ ባልደረባ ኦሊቨር ትሮክሴል እ. ኤ. አ. በ1963 ሲናገር ፤ «ለምናወጣው ገንዘብ ከፍተኛ ጥቅም ለማግኘት የምንችለው በነዚህ ሁለት መስኮች ነው ። በሁለቱ መስኮች ባለን ፕሮግራም የኢኮኖሚና የፖለቲካ ግባችንን መምታት ከቻልን ስለሌሎች መስኮች ምን አሳሰበን?» ብሎ ነበር ። እርግጥ አሜሪካ ለኢትዮጵያ ከሰጠችው ብድር ውስጥ 18 ከመቶ ለእርሻ ተመድቦ ነበር ። ነገር ግን ምንም እንኳ አሜሪካ ለኢትዮጵያ ብድር መስጠት የጀመረችው እ. ኤ. አ. በ1943 ቢሆንም ለእርሻ ከተመደበው ጠቅላላ ብድር 80 ከመቶ በሥራ ላይ መዋል የጀመረው እ. ኤ. አ. በ1970ዎቹ የመጀመሪያ ዓመታት መሆኑና በአሜሪካ ብድር የተካሄደው የመጀመሪያው የእርሻ ፕሮጀክት የተጠነሰሰው እ. ኤ. አ. በ1965 መሆኑ[35] አሜሪካ ለኢትዮጵያ የሰጠችው ብድር ችላ ያለው ኢንዱስትሪንና ማዕድን ፍለጋንና ማውጣትን ብቻ ሳይሆን እርሻንም ጭምር መሆኑን ያሳያል ።

አሜሪካ ለኃይለ ሥላሴ መንግሥት በስጦታ መልክ ያደረገችው ዕርዳታ በአብዛኛው ለወታደራዊ ጉዳዮች የዋለ ነበር ። በሁለቱ አገሮች መካከል የጋራ መከላከያ ውል ከተፈረመበት እ. ኤ. አ. ከ1953 እስከ 1972 አሜሪካ ለኢትዮጵያ በስጦታ መልክ ያደረገችው ወታደራዊ ዕርዳታ 434.1 ሚሊዮን ብር ያህላል ። ይህም በዚሁ ጊዜ ውስጥ አሜሪካ ለመላው አፍሪካ ከሰጠችው ወታደራዊ እርዳታ 46.9% ያህል ነው ። እ. ኤ. አ. ከ1950—67 ባለው ጊዜ 2,448 ኢትዮጵያውያን በአሜሪካ ውስጥ በወታደራዊ ትምህርት ሠልጥነዋል ። ይህ ቊጥር በአሜሪካ ዓለም አቀፍ ወታደራዊ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራም በዚያን ጊዜ ከተሳተፉት አፍሪካውያን 72% ያህሉን ይሸፍናል። ከ1968—73 በተመሳሳይ ሥልጠና የተሳ

ተፉ ኢትዮጵያውያን አማካይ ዓመታዊ ቊጥር 160 ወይንም ከመላው አፍሪካ ተሳታፊዎች 43.3% ነበር ። ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ቊጥሮች በአሜሪካ የሰለጠኑ የፖሊስ አባሎችን አይጨምሩም ። ከ1961—71 በአሜሪካ ዓለም አቀፍ እርዳታ ሰጭ ድርጅት (ኢ.አይ.ዲ.) ሥር በሚካሄድ «ፐብሊክ ሴፍቲ» በተባለ ፕሮግራም አማካይነት 114 የኢትዮጵያ ፖሊስ አባሎች አሜሪካ ውስጥ ሰልጥነዋል ። ይህም በሰልጣኞች ብዛት በአፍሪካ ውስጥ ኢትዮጵያን ከሶማሊያ ቀጥሎ በሁለተኛ ደረጃ ያስልፋታል ። ከ1955—74 ባለው ጊዜ አሜሪካ ለኢትዮጵያ የሰጠችው የጦር መሣሪያዎች ግምት 184 ሚሊዮን ዶላር ሲሆን ይህም ለመላው አፍሪካ ከተሰጠው 38.7% ይሆናል ። እ. ኤ. አ. ከ1946—74 አሜሪካ ለአፍሪካ ከሰጠችው ጠቅላላ የኢኮኖሚ ዕርዳታ ውስጥ ግን ለኢትዮጵያ የተሰጠው 6.1% ብቻ ነበር ። ይህ ብቻ አልነበረም ። ኢትዮጵያ ከአሜሪካ አግኝታ የነበረው የኢኮኖሚ ዕርዳታ በአብዛኛው የብድርና የክሬዲት መልክን የያዘ ሲሆን ወታደራዊ ዕርዳታው ግን በስጦታ መልክ ነበር ።[36] በእነዚህና ከዚህ በታች በሚዘረዘሩ ሌሎች ምክንያቶች አሜሪካ ለኃይለ ሥላሴ መንግሥት ያደረገችው ዕርዳታ የሰፊውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ኑሮ ደረጃ በማሳደግ ረገድ አስተዋጽኦ ሊኖረው አልቻለም ፤ እንዲኖረውም የታቀደ አልነበረም ።

አሜሪካ ለኢትዮጵያ የሰጠችው ዕርዳታ በሕዝቡ የኑሮ ደረጃ ላይ ጤናማ ተጽእኖን ሊያሳድር ያልቻለባቸው ሌሎች ተጨማሪ ምክንያቶች አሉ ። ከእነዚህም መካከል ለቁሳዊ ምርት ትኩረት ላልሰጡት በአሜሪካ ዕርዳታ ለተካሄዱት ፕሮጀክቶች ተጨማሪ ወጪ ከአገር ውስጥ እንዲመደብ መደረጉ ፤ በአሜሪካ ዕርዳታ የሚካሄዱ ፕሮጄክቶችና በኢትዮጵያ ተመድበው የሚሠሩ አሜሪካውያን ኤክስፐርቶች ከፍተኛ ወጪ ማስከተላቸው ይገኛሉ ። የአሜሪካን ዕርዳታ በሥራ ላይ ማዋል የኢትዮጵያን መንግሥት ወጪ የሚጠይቅ ስለመሆኑ ለምሳሌ «ፖይንት ፎር» እየተባለ ይጠራ የነበረውን የአሜሪካ ፕሮግራም እ. ኤ. አ. ከ1952—1958 በኢትዮጵያ ውስጥ ለማካሄድ የአሜሪካ መንግሥት 12.2 ሚሊዮን ብር ሲያወጣ የኢትዮጵያ መንግሥት በበኩሉ 14.8 ሚሊዮን ብር ማውጣት እንደነበረበት መጥቀስ ይቻላል ። በአሜሪካ ቁጥጥር ሥር የሚገኘውና የዓለም ባንክ የሚባለው ዓለም አቀፋዊ ድርጅት ለመጀመሪያ ጊዜ እ. ኤ. አ. በ1950 ለኢትዮጵያ በሰጠው ለመንገድ ሥራ የሚውል የአምስት ሚሊዮን ዶላር ብድር ስምምነት መሠረት ኢትዮጵያ ለዚሁ ጉዳይ ወጪያውኑ አምስት ሚሊዮን ብር ፤ ለሚቀጥሉት ሶስት ዓመታት በየዓመቱ ስድስት ሚሊዮን ብር፣ ከዚህም በኋላ ለአሥራ ሰባት ዓመታት በየዓመቱ አምስት ሚሊዮን ብር ለመመደብ ቃል ገብታ ነበር። ኒው ዮርክ ታይምስ የተሰኘው ጋዜጣ አብዮታችን ከመፈንዳቱ ጥቂት ዓመታት ቀደም ሲል «ኢትዮጵያ ምንም እንኳ መጠኑ የማይናቅ ዕርዳታ ከውጭ የምታገኝ ቢሆንም አብዛኛው በሥራ ላይ ለመዋል ተጨማሪ ወጭን ከኢትዮጵያ ይጠይቃል ። በቅርቡ የመንግሥት ገቢ ከማደጉ በፊት ኢትዮጵያ ይህን ተጨማሪ ወጭ ለመሸፈን በምትችልበት ሁናቴ ላይ አትገኝም ነበር» በማለት በአምዱ ላይ አሥፍሯል ።[37] ጋዜጣው ስለዚህ ጉዳይ ማከል የነበረበት ነገር ቢኖር ኢትዮጵያ ከኢምፔሪያሊስት አገሮች ያገኘችው ዕርዳታ በቀጥታ ቁሳዊ ምርትን የሚያመርቱ የኢኮኖሚ መስኮችን ችላ የሚል በመሆኑ የዚህ ዓይነቱን ዕርዳታ በሥራ ላይ ለማዋል ኢትዮጵያን ተጨማሪ ወጭ መጠየቁ አገሪቷ የራሷን ጥሪት እንኳ ቁሳዊ ምርትን ለማሳደጊያ የማዋል ነፃነት እንዳይኖራት ማድረጉን ነው ።

በአሜሪካ መንግሥት ርዳታ ይንቀሳቀሱ የነበሩት ፕሮጄክቶችና የአሜሪካ ኤክስፐርቶች እጅግ ከፍ ያለ ገንዘብ የሚወጣባቸው ነበሩ ። እ. ኤ. አ. ከ1956—63 ድረስ ይካሄድ የነበረውና 4.5 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር የወጣበት የጥቁር አባይ ሸለቆ ጥናት ፕሮጄክት በአሜሪካ እርዳታ የሚንቀሳቀሱ ፕሮጄክቶች ምን ያህል ውድ መሆናቸውን የሚያሳይ ጥሩ ምሳሌ ነው ። ይህን ያህል ገንዘብ «ለሌላ ነገር ሳይሆን በጠረጴዛ ላይ ለተቆለሉ የወረቀቶች ክምችት ፤ በኔ ግምት ከፍተኛ ገንዘብ ይመስለኛል ፤» ሲል እ. ኤ. አ. በ1962 በአሜሪካ ምክር ቤት ውስጥ የሉዊዚያናው ወኪል አቶ ፓስማን ስለዚሁ ጥናት ያለውን አስተያየት ሰንዝሯል ። ከአንድ ዓመት በኋላ ደግሞ «በምክር ቤቱ ውስጥ ከገባሁ ጀምሮ ለጥናትና ለዕቅድ ብቻ 3 ሚሊዮን ዶላር የጨረሰ የዚህ ዓይነት ፕሮጄክት ሰምቼም አላውቅም ፤» ሲል የኒው ሜክሲኮ ወኪል የሆነው ጆሴፍ ሞንቶያ ይህንኑ ጥናት ተችቶታል ። የዚህን ጥናት ውድነት ይበልጥ ለመረዳት በሦስተኛው አምስት ዓመት የኢትዮጵያ ዕቅድ ውስጥ ጥናቱ «የመጀመሪያ ደረጃ ነው ። ሪፖርቱ ሊካሄዱ ይችላሉ ብሎ የጠቆማቸው ፕሮጀክቶች የሚያዋጡ ወይንም የማያዋጡ መሆናቸው ከመ

ታወቁ በፊት ብዙ ተጨማሪና ዝርዝር ሥራ መሥራት ያስፈልጋል» ሲል የሰፈረውን መጥቀስ ይቻላል ። በጥናቱ ውስጥ ቀርበው ከነበሩት ፕሮጀክቶች ውስጥ አንዱ ለኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨት እንዲሠራ የታቀደው የፊንጫ ግድብ ነበረ ። ለዚህ ግድብ ሥራ የአሜሪካ የውጭ እርዳታ ሰጪ ድርጅት፣ ኤ. አይ. ዲ. እ. ኤ. አ. በ1966 የ21.7 ሚሊዮን ዶላር ብድር ለመስጠት ከተስማማ በኋላ ግድቡን ለመሥራት ጨረታው በአሜሪካ ኩባንያዎች መካከል ተካሂዶ ከቀረቡት መካከል ዝቅተኛ የሆነው የጨረታ ዋጋ የአሜሪካ ኢንጂነሮች ከገመቱት 68% በልጦ ተገኘ ። የኃይለ ሥላሴ መንግሥትም ፕሮጀክቱን ለማካሄድ ብዙም የተሻለ አማራጭ ያልሆነውንና በአሜሪካ ቁጥጥር ሥር የሆነውን የዓለም ባንክን እርዳታ ጠይቆ አገኘ ።

በአሜሪካ መንግሥት የተካሄዱ ፕሮጀክቶች ውድ ከሆኑባቸው ምክንያቶች ውስጥ የአሜሪካ ኤክስፐርቶች ውድነት አንደኛው ነው ። ለምሳሌ ያህል ኤ. አይ. ዲ. ለጥቁር አባይ ፕሮጀክት እ. ኤ. አ. በ1963 ከመደበው ከ715,000 ዶላር ውስጥ 588,000 ዶላር ወይንም ከጠቅላላው 80% የሚሆነው የወጣው በተባለው ፕሮጀክት ውስጥ ይሠሩ ለነበሩ የአሜሪካ ቴክኒሺያኖች ነው ። በኢትዮጵያ በአንድ የገጠር ልማት ድርጅት ውስጥ በ1969 ለሚሠሩ ሁለት ኤክስፐርቶች ለስድስት ወራትና ለአንድ ኤክስፐርት ለአንድ ዓመት 80,000 ዶላር እንደተመደበ በተነገረው ጊዜ የአሜሪካ ምክር ቤት አባል ኦቶ ፓስማን «እነዚህ ሥራዎች ከምክር ቤቱ ለመሰናበት ለሚፈልግ አባል ክፍት ናቸውን?» ብሎ እንደቀልድ በመጠየቅ ክፍያው ከፍተኛ መሆኑን ገልጿል ። ሳሙኤል አዳምስ በኤ. አይ. ዲ. ውስጥ የአፍሪካ ቢሮ ረዳት አስተዳዳሪ እ. ኤ. አ. በ1975 ለአንድ አሜሪካዊ ኤክስፐርት በዓመት 55,000 ዶላር ተከፍሎት በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲሠራ ያቀረበውን ጥያቄ በመደገፍ ኤ አይ. ዲ. ቀጥሮ ከአሜሪካ ውጭ የሚመድባቸው ሰዎች የሚያገኙት ዓመታዊ ደመወዝ በ50,000 እና በ60,000 ዶላር መካከል መገኘቱን መግለጹ በኢትዮጵያ ይሠሩ የነበሩ አሜሪካዊ ኤክስፐርቶች አማካይ ደመወዝ ምን ያህል እንደነበር ፍንጭ ይሰጣል። የአሜሪካን ኤክስፐርቶች ውድነት በኢትዮጵያ ውስጥ ይገኙ የነበሩ አሜሪካዊ ኤክስፐርቶች ቁጥር ከፍተኛ ከመሆን ጋር በመደመር አሜሪካ ለኢትዮጵያ ሰጠሁ የምትለውን የኢኮኖሚ ዕርዳታ ሊያሚጥጠው ችሎ ነበር ። ለምሳሌ በኢትዮጵያ ውስጥ በቋሚ የኤ. አይ. ዲ. ሠራተኛነት ይሠሩ የነበሩ አሜሪካውያን ቁጥር እ. ኤ. አ. በ1961 129 እና በ1973 82 መሆኑ ኢትዮጵያን በእነዚህ ዓመታት በዚህ ረገድ ከአፍሪካ አገሮች መካከል አንደኛ ያደርጋታል ። የአሜሪካ ኤክስፐርቶች በኢትዮጵያና በሌሎችም አገሮች ውስጥ ከፍተኛ ወጭን የሚጠይቁበት ምክንያት ደመወዛቸው ከፍተኛ መሆኑ ብቻ አይደለም ። እንደቤት ኪራይ አበል ያሉ በልዩ ልዩ ስም የሚከፈሉ አበሎችና ተቀጣሪዎቹ በተመደቡባቸው አገሮች ውስጥና በውጭ አገር ለጉዞ የሚያወጧቸውን ወጪዎች ለመሸፈን የሚደረጉ ክፍያዎችም አነስተኛ አይደሉም ። አንዳንዴም ኤክስፐርቶቹ ጠባብ በሆነ የሥራ መስክ የሠለጠኑ መሆናቸው ለአሜሪካ ኤክስፐርቶች የሚከፈል ክፍያን እንዲያድግ አድርጎታል ። ለምሳሌ በኢትዮጵያ ውስጥ በአምስት የአሜሪካ ኤክስፐርቶች ይካሄድ ለነበረ አንድ ጤናነክ ፕሮጀክት ጥናት የሚረዳ የስታቲስቲክስ ዘዴ እንዲጠቁም ለአንድ የአሜሪካ ዩኒቨርሲቲ የ12,000 ዶላር ኮንትራት መስጠቱ የአሜሪካን ምክር ቤት አባል ፓስማንን አስገርሞት ነበር ። በአጠቃላይ አሜሪካ ለኢትዮጵያ ሰጠሁ የምትለው ዕርዳታ ውጤት አልባ ስለመሆኑ «እኛ የምናየው ባለከፍተኛ ደመወዝተኞች አሜሪካውያን በአዲስ አበባ ውስጥ በረጃጅም መኪኖቻቸው ሲንሸራሸሩና ምርጥ በሆኑ ቤቶቻችን ውስጥ ሲኖሩ ብቻ ነው» በማለት «አንዳንድ ኢትዮጵያውያኖች» ይተቻሉ ሲል የኢምፔሪያሊስቶች ልሣን የሆነው ኒውዮርክ ታይምስ እንኳ ያሰፈረውን[38] መጥቀስ በቂ ነው ።

ትምህርትና ባሕል

የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም በኢትዮጵያ ውስጥ ስላሳየው እንቅስቃሴ ሲነሳ በትምህርቱ መስክ ያካሄደው ተግባር ካልታከለበት የተሟላ ሊሆን አይችልም ። በአሜሪካና በኢትዮጵያ መካከል ጠንካራ የትምህርት ግንኙነት ሊመሠረት የቻለው የአሜሪካ መንግሥት እ. ኤ. አ. በ1950 «ፖይንት ፎር» የተሰኘ ፕሮግራም ማካሄድ ከጀመረ በኋላ ነበር ። ይህ ፕሮግራም እንደተጀመረ ወዲያውኑ በሁለቱ መንግሥታት መካከል ትምህርትን በሚመለከት «የቴክኒክ ስምምነት» ተፈረመ ። በ«ፖይንት ፎር» ፕሮግራም መሠረት ከ1951—1959 ባሉት ዓመታት ውስጥ 433 ኢትዮጵያውያን ወደ ውጪ ተልከዋል ። ከነዚሁ መካከል 248ቱ ወደ

ዩናይትድ ስቴትስ ፣ 180ዎቹ ደግሞ ቤይሩት ወደሚገኘው ወደአሜሪካ ዩኒቨርሲቲ ፤ እንዲሁም የቀሩት አምስቱ ወደ ሌሎች አገሮች ተልከዋል ። እ. ኤ. አ. በ1960ዎቹ የመጀመሪያ ዓመታት «ፖይንት ፎር»ን የተካውና የዓለም አቀፍ ልማት ድርጅት (ኤ. አይ. ዲ.) የተሰኘው ድርጅት እ.ኤ.አ. እስከ 1974 ድረስ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ብቻ ቁጥራቸው ከ200 በላይ የሚሆኑ ኢትዮጵያውያን መምህራንን አሰልጥኗል ።[39]

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በእርግጥም አሜሪካ በተማሩ ምሁራን የተጥለቀለቀ ነበር ። ዩኒቨርሲቲው እ. ኤ. አ. በ1973 ባወጣው ዝርዝር መግለጫ ውስጥ እንደተገለጸው ከፍተኛውን ሥፍራ ከያዙት 10 «የዩኒቨርሲቲው ባለሥልጣኖች» መካከል ስምንቱ ፤ የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚደንት ጭምር ፤ ኢትዮጵያውያን ሲሆኑ ፤ ከእነዚሁ ከስምንቱ ሰባቱ የማስተርስ ዲግሪአቸውን ከአሜሪካ ፤ ስምንተኛው ደግሞ ቤይሩት ከሚገኘው ከአሜሪካ ዩኒቨርሲቲ ያገኙ ነበሩ ። ከስምንቱ አራቱ የዶክትሬት ዲግሪ ሲኖራቸው አራቱም የዶክትሬት ዲግሪያቸውን ያገኙት ከአሜሪካ ነበር ። በዚሁ ዝርዝር መግለጫ መሠረት በዩኒቨርሲቲው ውስጥ የነበሩ ኢትዮጵያውያን «የአካዳሚ ኦፊሰሮች» ቁጥር ውጭ በትምህርት ላይ የነበሩትን ሳይጨምር 34 ነበር ። ከእነዚሁ መካከል የማስተርስ ዲግሪ ያላቸው ኑሥር ፤ የዶክትሬት ዲግሪ ያላቸው 17 ነበሩ ። የማስተርስ ዲግሪ ካላቸው ከአሥሩ መካከል ሁሉም ፤ እንዲሁም የዶክትሬት ዲግሪ ካላቸው ከ17ቱ 15ቱ በመጨረሻ ያገኙትን ዲግሪ ያገኙት ከአሜሪካ ነበር ። ዝቅ ባለ ደረጃ በዩኒቨርሲቲው ውስጥ በአስተዳደር ሥራ ተሰማርተው ከነበሩት ውስጥ የማስተርስ ዲግሪ ከነበራቸው ከስምንቱ መካከል ሁሉም የማስተርስ ዲግሪያቸውን ያገኙት ከአሜሪካ ነበር ። በማስተማርና በምርምር ሥራ ላይ በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ለሙሉ ጊዜ ተሰማርተው ከነበሩት 395 ምሁራን መካከል 268ቱ ወይንም ከመቶ 67.5% የሚሆኑት ኢትዮጵያውያን ነበሩ ። ከእነዚህ ኢትዮጵያውያን ምሁራን መካከል 77ቱ የዶክትሬት ዲግሪ ነበራቸው ። ከእነዚህ ከ77ቱ የዶክትሬት ዲግሪዎች መካከል 49ኙ ፤ ወይንም 64% የተገኙት ከአሜሪካ ነበር ። ሁለቱ ደግሞ ቤይሩት ከሚገኘው የአሜሪካ ዩኒቨርሲቲ የተገኙ ነበሩ ። እንግሊዝ ከእነዚህ ምሁራን መካከል ዘጠኙን በዶክትሬት ዲግሪ በማሠልጠን የሁለተኛውን ደረጃ ለመያዝ ችላ ነበር ። ከሶሻሊስቱ ዓለም ዶክትሬቱን ያገኘ አንድ ቼኮዝሎቫኪያ የተማረ ምሁር ብቻ ነበር ። የዶክትሬት ዲግሪያቸውን ከአሜሪካ ካገኙ 49 ኢትዮጵያውያን መካከል 39ኙ ቀደም ብለው የባችለር ወይንም የማስተርስ ዲግሪ ከዚያው ከአሜሪካ የተቀበሉ ሲሆን ፤ የዶክትሬት ዲግሪያቸውን ከአሜሪካ ውጭ ካገኙት 28 ኢትዮጵያውያን መካከል ደግሞ ሰባቱ ቀደም ብለው ከአሜሪካ የባችለር ወይንም የማስተርስ ዲግሪ ያገኙ ነበሩ ። የፋኩልቲ አባሎች ከነበሩት ከ268 ኢትዮጵያውያን መካከል 83ቱ ደግሞ በመጨረሻ ያገኙት የማስተርስ ዲግሪ ነበር ። ከነዚህ 65 ወይንም ከጠቅላላው 78.3% የሚሆኑት ይህንኑ ዲግሪ ያገኙት ከአሜሪካ ሲሆን ፤ በተጨማሪም 3ቱ ቤይሩት ከሚገኘው የአሜሪካ ዩኒቨርሲቲ ያገኙ ናቸው ። የማስተርስ ዲግሪ ካላቸው ከ83ቱ ኢትዮጵያውያን መካከል 6ቱ ይህን ዲግሪ ያገኙት እንግሊዝ አገር መሆኑ አሁንም እንግሊዝን የሁለተኛውን ደረጃ ሲያሲዛት ከሶሻሊስቱ ዓለም የተገኘው የማስተርስ ዲግሪ አንድ ምሁር ከቼኮዝሎቫኪያ ያገኘው ብቻ ነበር ።[40]

አሜሪካ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲን በቁጥጥሯ ሥር ያዋለችው ኢትዮጵያውያን መምህራንን በማሠልጠን ብቻ አልነበረም። ቁጥራቸው በርካታ የሆነ ዜጎቿንም ለአስተማሪነት ወደዩኒቨርሲቲው ልካለች ። ይህ በተለይ "የሰላም ጓድ" የተባለ ፕሮግራም ተዘርግቶ ይሠራ በነበረበት ወቅት ጎልቶ የታየ ነበር ። እ. ኤ. አ. መስከረም 1962 ቁጥራቸው ወደማንኛውም ሌላ አገር ከተላኩት የላቀ 244 የአሜሪካ "የሰላም ጓድ" አባሎች ወደኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ ከተላኩበት እስከ 1969 ድረስ ኢትዮጵያ በየዓመቱ ውስጧ በሚገኙ "የሰላም ጓድ" አባሎች ቁጥር ከአፍሪካ አገሮች መካከል የአንደኛነትን ወይንም የሁለተኛነትን ደረጃ ከናይጄሪያ ጋር ተካፍላለች ። እ. ኤ. አ. በ1966 ፤ 566 "የሰላም ጓድ» አባሎች ኢትዮጵያ ውስጥ ይገኙ ነበር ። እርግጥ "የሰላም ጓድ» ፕሮግራም ፀረ ኢምፔሪያሊስት አቋም ያለው የተማሪዎች ንቅናቄ በመጠናከሩ ምክንያት እ. ኤ. አ. ከ1970 ጀምሮ በኢትዮጵያ ውስጥ እየመነመነ ለመሄድና ከአብዮታችን ፍንዳታ በኋላም ሊከስም ችሏል ።[41] ሆኖም ረዘም ላለ ጊዜ በኢትዮጵያ የትምህርት ሥርዓት ውስጥ ከፍተኛ ቦታ ይዞ ነበር ። ለምሳሌ እ.ኤ.አ. በ1966 440 የአሜሪካ "የሰላም ጓድ" አባላት በመንግሥት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ያስተምሩ ነበር ። ይህም በእነዚህ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ከሚያስተምሩ መምህራን ጠቅላላ ቁጥር 23.6% እንዲሁም ከውጭ አገር መምህራን 51.8%

ይሆናል ። በዚሁ ዓመት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ከነበሩ መደበኛና በትርፍ ጊዜያቸው ያስተምሩ ከነበሩ 308 መምህራን መካከል 66ቱ ወይንም 21.4% የአሜሪካ "የሰላም ጓድ" አባላት ነበሩ ።[42] የአሜሪካ "የሰላም ጓድ" አባላት ፕሮግራም በኢትዮጵያ መካሄድ በዩኒቨርሲቲ ውስጥ ያስተምሩ ከነበሩ የውጭ አገር ዜጎች መካከል የአሜሪካውያንን ቁጥር ከፍ አደረገ ። ለምሳሌ በ1964 በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ያስተምሩ ከነበሩት 175 የውጭ ዜጎች መካከል 159ኙ ወይንም ከጠቅላላው 90.9% ከዳበሩት የካፒታሊስት አገሮች የመጡ ነበሩ ። ከእነዚህ መካከል አሜሪካውያን 75 ፤ ወይንም ከጠቅላላው 42.9% ነበሩ ።[43]

ትምህርትን ፤ በተለይም ከፍተኛ ትምህርትን ፤ በሚመለከት ለኃይለ ሥላሴ መንግሥት ዕርዳታ በማድረግ ረገድ አሜሪካ የበላይነትን ይዛ ነበር ። ለምሳሌ እ. ኤ. አ. በ1963 የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በስጦታ መልክ ካገኘው የ6.8 ሚሊዮን ብር ዕርዳታ ውስጥ 81.6%ቱ የተገኘው በዓለም አቀፍ ልማት ድርጅት (ኤ. አይ. ዲ.) እና በ«ሰላም ጓድ» ፕሮግራሞች አማካኝነት ከአሜሪካ ነበር ።[44] እንደፎርድ ድርጅት ፤ የአፍሪካና የአሜሪካ ኢንስቲቲዩትና የሮክፌለር ድርጅት ያሉ ሌሎች የአሜሪካ ድርጅቶችም ለኢትዮጵያ ከፍተኛ ትምህርት እርዳታ መስጠታቸው ይታወሳል ። የአሜሪካው የዓለም አቀፍ ልማት ድርጅት አስተዳዳሪ የነበረው ጆን ኤ. ሃና እ.ኤ.አ. በ1971 «የኃይለ ሥላሴ (ያሁኑ አዲስ አበባ) ዩኒቨርሲቲ በሚገኝበት ሁኔታ ለመገኘት የቻለው በአሜሪካ ዕርዳታ አማካይነት ነው»[45] ያለው ስለዚህ ላያስገርም ይችላል ።

የኢትዮጵያን ተማሪዎች በማስተናገድም ረገድ አሜሪካ ከፍተኛውን ሚና ተጫውታለች ። ለምሳሌ እ. ኤ. አ. ከ1956—57 በ1960 እና በ1969 በአሜሪካው አለም አቀፍ ትምህርት ድርጅት ሪፖርት መሠረት በአሜሪካ ይማሩ የነበሩ ኢትዮጵያውያን ቍጥር 100 ፤ 170 እና 422 ነበር ። በነዚሁ ዓመታት በአሜሪካ ይገኙ የነበሩት ኢትዮጵያውያን ተማሪዎች ከአፍሪካ አገሮች ከመጡ ተማሪዎች መካከል በብዛት የ3ኛ ፤ የ2ኛ እና የ3ኛ ሥፍራ ይዘው ነበር ። አብዮቱ በፈነዳበት ዓመት ቍጥራቸው ከ 1,500 በላይ የሆነ ኢትዮጵያውያን በአሜሪካ ይማሩ ነበር ። በአሜሪካ መንግሥት ሙሉ ዕርዳታ ይማሩ የነበሩ ኢትዮጵያውያን ወጣቶች ቍጥር እ. ኤ. አ. በ1960 25 የነበረው በ1969 ወደ 137 ከፍ ብሎ ነበር ። ይህም ኢትዮጵያን ከአፍሪካ አገሮች መካከል የአንደኛውንና የሁለተኛውን ሥፍራ አስይዟት ነበር ። እ. ኤ. አ. በ1972 በአሜሪካው ዓለም አቀፍ ልማት ድርጅት አማካይነት 330 ኢትዮጵያውያን ተማሪዎች (312 በአሜሪካ ፤ የተቀሩት በሦስተኛ አገር) ሙሉ ዕርዳታ እየተደረገላቸው ይማሩ ነበር ። ይህም ኢትዮጵያን ከአፍሪካ አገሮች መካከል የመጀመሪያውን ደረጃ አስይዟታል ።[46] በተለይ እ. ኤ. አ. በ1950ዎቹ እና በ1960ዎቹ ዓመታት ውስጥ ሊባኖስ ዋና ከተማ ቤይሩት የሚገኘው የአሜሪካ ዩኒቨርሲቲ አሜሪካ በኢትዮጵያ ታካሂደው ለነበረው ትምህርት ነክ የኢምፔሪያሊስ ትነት ተግባር ደህና አድርጎ ተባብሮ ነበር ። «በቅርብ ምሥራቅ የአሜሪካን ተጽእኖ ለማስፋፋት የሚበጅ ደጀን» ሲል የአሜሪካ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እ. ኤ. አ. በ1954 ወደአስታወቀለት ወደዚሁ ዩኒቨርሲቲ እ. ኤ. አ. ከ1950—59 180 ኢትዮጵያውያን ወጣቶች በአሜሪካ ዕርዳታ ተልከው ተምረዋል ።[47]

አሜሪካ በኢትዮጵያ ውስጥ ለትምህርቱ መስክ ፤ በአጠቃላይም ለዓለም አቀፍ ትምህርት ጉዳይ ትኩረት ለመስጠት የተነሣሣችው የኢምፔሪያሊስት ጥቅሟን ለማራመድ መሆኑ ግልጽ ነው ። ይህንንም ለመረዳት ትምህርት ነክ ግንኙነትን እንደ አንድ ዋና ኢምፔሪያሊዝምን የማስፋፊያ ዘርፍ እንዲሆን ባጸደቀችበት ወቅት ፤ ማለት ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት መደምደሚያ እስከ 1960ዎቹ የመጀመሪያ ዓመታት ፤ ስለዚሁ ጉዳይ የተሰጡ ፖሊሲ ነክ መግለጫዎችንና ከዚሁ ጋር የተዛመዱ ተግባሮችን መቃኘት ይበቃል ። ከዚህ በታች እንደሚታየው የአሜሪካ ዓለም አቀፍ የትምህርት ግንኙነት ዋና ዓላማ ዓለም አቀፍ ኮምዩኒዝምን ለመዋጋት መሆኑን የአሜሪካ ባለሥልጣኖች ደግመው ደጋግመው ገልጸውታል ። አሜሪካ በኢትዮጵያ ውስጥ የነበራት ዓላማም ከዚህ የተለየ ሊሆን አይችልም ። የአሜሪካ ኢምፔሪያሊስቶች በእርግጥም ዓለም አቀፍ የትምህርት ግንኙነታቸውን ኮምዩኒዝምን ለመዋጋትና እንዳይስፋፋም ለማድረግ የሚያካሂዱት ዘመቻ አካል አድርገው ይገምቱታል ። እ. ኤ. አ. በ1950 የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ሔሪ ትሩማን «የዕውነት ዘመቻ» ብሎ ስለሰየመው ፀረ ኮምዩኒስት ፕሮፓጋንዳ ማፋፋም አስፈላጊነት እንዲህ ሲል ተናግሯል ።

«ለመላው ዓለም ሕዝብ ሐቁን ለማሳወቅ ጥረታችንን በበለጠ ማስፋፋትና ማጠናከር ይገባናል የሚል እምነት አለኝ ። በአሜሪካ

ድምፅ ሬዲዮ ጣቢያችን ፤ በዓለም ውስጥ በብዙ ቦታዎች ተሰራጭተው በሚገኙት ቤተ መጻሕርቶቻችንና ለማስታወቂያ አገልግሎቶቻችን አማካይነት ፤ በተማሪዎች ለውውጥ ፕሮግራማችን ፤ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅትና በልዩ ልዩ ቀርንጫፍ ድርጅቶች በኩል አሁንም ቢሆን ጥሩ ሥራ እየሠራን ነው ። . . . ይሁን እንጂ ከዚህ በበለጠ መሥራት አለብን ።

. . . የውጭ አገር ተማሪዎች በየትምህርት ቤቶቻችንና በየዩኒቨርሲቲዎቻችን እንዲያጠኑ የበለጠ ዕድል እንድንከፍትላቸው ያስፈልጋል ።»

ንግግሩን በመቀጠል ፕሬዚደንቱ እንዲህ አለ ፤

«የጥረታችን ሌላው ከፍተኛ ክፍል በታላላቆቹ የዜና ማሠራጫዎቻችን ማለትም በጋዜጦች ፣ በመጽሔቶች በራዲዮና በሲኒማ አማካይነት መካሄድ አለበት ። . . .

የኛ ተግባር ገና ላልሰሙ ወይም ለተወናበዱ ወይም ገና ላላመኑ በሚሊዮን ለሚቆጠሩ ሰዎች ሐቁን ማቀረብ ነው ። . . .

ይህ ተግባር ከውጭ ፖሊሲያችን ሌሎች ዘርፎች ተነጥሎ የሚታይ ወይም የተለየ አይደለም ። የወታደራዊ ጥንካሬአችንና የኢኮኖሚ ዕርዳታችንን ያህል ሊቀጠር የሚገባው ነው ። የኮሚዩኒስት ፕሮፓጋንዳ እንደሚያቀርበን ሳይሆን ትክክለኛውን ገጽታችንን ማሳወቅ አለብን ። . . .

የሰዎችን ሃሣብና ታማኝነት ለመማረክ በሚደረገው ትግል ከፍተኛ ብልጫ አለን ። ሐቅና ነፃነት በኛ ጎራ ውስጥ ናቸውና ።»[48]

በዚያው ዓመት ፤ ማለትም በ1950 ፤ የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ባቀረበው አንድ ዘገባ እንዲህ ብሏል ፤«የሶቪዬት ኅብረት ፕሮፓጋንዳ ጥረት ለውጭ ፖለቲካ ዓላማችን አስጊ መሆኑ ታውቋል»። ስለሆነም «ሐቁን የመናገር ተግባር ከሌሎች የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ዘርፎች ተነጥሎ የሚታይ ወይም የተለየ አይደለም ።» ይኸው ሚኒስቴር በዓለም አቀፋዊ የማስታወቂያና የልውውጥ ፕሮግራሙ መሠረት ያከናወነውን ተግባር በማተት እንደሚከተለው ቀጥሏል ፡ «ያከናወንናቸው ተግባራት ያተኮሩት በልዩ ልዩ መንግሥታት ፖሊሲዎች ላይ ወሳኝነት ባላቸውና ወደፊት ይኖራቸዋል ተብለው በሚገመቱ ሰዎችና ቡድኖች ላይ ነው ። ይህም ማለት ከመንግሥት ባለሥልጣኖች ፤ የፖለቲካ መሪዎች ፤ የጽሑፍ አዘጋጆችና ደራሲያን ፤ ፕሮፌሰሮችና ተማሪዎች ፡ የወዝአደር መሪዎች ፤ እንዲሁም ከልዩ ልዩ ድርጅቶችና ማኅበሮች ጋር ግንኙነት መፍጠር ማለት ነው ።[49] ዌይን ሞርስ የተባለ በአሜሪካ ምክር ቤት ውስጥ የኦሪገን ተወካይ የአሜሪካ የትምህርትና የባሕል የጋራ ልውውጥ (ፉልብራይት-ሒይዝ) የተሰኘውን ፕሮግራም በመደገፍ እ. ኤ. አ በ1961 እንደሚከተለው ተናግሯል ።

«እኔ እንደምገምተው የፉልብራይት የነፃ ትምህርት ፕሮግራምና እርሱ የሚደግፋቸው ሌሎች የባሕል ፕሮግራሞች ለአገራችን ደህንነት ከተወሰዱ ዋና ዋና እርምጃዎች መካከል የሚገኝ ነው ። . . . በሚቀጥሉት ጥቂት አሥር ዓመታት ውስጥ ከወታደራዊ ወረራ ይልቅ በባሕል ወረራ በዓለም ላይ ነፃነትን የማስፈን ዕድል አለን ። ሰላምን ለመመሥረት የምንችለው ይህ የሕግ ረቂቅ በቀየሰው መስመር ነው ። በሚሳይልና በቦምብ ጣይ አይሮፕላኖች ፈንታ የሰዎችን አስተሳሰብ እንማርካለን ማለት ዘበት ነው ።»[50]

አፍሪካን በሚመለከት የአሜሪካ ምክትል ፕሬዚዳንት የነበረው ኒክሰን እ. ኤ. አ በ1957 ልዩ ልዩ የአፍሪካ አገሮችን ፤ ኢትዮጵያንም ጭምር ፤ ከጎበኘ በኋላ በአፍሪካ ውስጥ «የኮምዩኒዝምን ተጽእኖ ለመቋቋም» ሲባል አሜሪካ በአፍሪካ አገሮች ውስጥ ለምታካሂዳቸው ቤተመጻሕፍትና የንባብ ቤቶች ፤ ለተማሪዎች ልውውጥ ፤ እናም አፍሪካውያንን ለትምህርትና ለሽርሽር ወደ አሜሪካ ለማምጣት ፤ እንዲሁም በአፍሪካ ውስጥ የትምህርት ተቋሞችን በማደራጀት ረገድ ለመሳተፍ ከፍ ያለ ተጨማሪ እርዳታ መደረግ ይኖርበታል ።»[51] የሚል ሃሣብ አቀረበ ።

አሜሪካ «የዕውነት ዘመቻ» የሚል ስም የሰጠችው ፀረ ኮምዩኒስት ፕሮፓጋንዳ ፕሮግራም በተቀየሰበት ዓመት ፤ ማለት እ. ኤ. አ. በ1950 ፤ በኢትዮጵያ ውስጥ መካሄድ ጀምሮ ነበር ። በዚያው ዓመት የአሜሪካ ቤተመጻሕፍት በአዲስ አበባ ውስጥ ይካሄድ እንደነበር የታወቀ ሲሆን በዓመቱ ሁለተኛ አጋማሽ ብቻ የአሜሪካ የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር በኢትዮጵያ ውስጥ 233 የፊልም ትርዕይቶችን ለ27,000 ኢትዮጵያውያን አሳይቷል ። እ. ኤ. አ. በ1950 ዎቹ ውስጥ የዩናይትድ ስቴትስ ማስታወ

ቂያ አገልግሎት (ዩ. ኤስ. አይ. ኤስ.) በኢትዮጵያ ውስጥ ካካሄዳቸው ተግባራት መካከል ኢትዮጵያና ነፃው ዓለም የተሰኘ ፊልም ማሳየቱ ይገኛል ። የኢትዮጵያ ወታደሮች በኮርያ ጦርነት ያደረጉትን ተሳትፎ የሚያሳየው ይህ ፊልም «ኢትዮጵያ ውስጥ በአማርኛ ቋንቋ ከታዩት የመጀመሪያ ፊልሞች አንዱ ነው ።»[52] እ. ኤ. አ. በ1961 በወጣ ጽሑፍ መሠረት የዩናይትድ ስቴትስ ማስታወቂያ አገልግሎት በኢትዮጵያ ውስጥ ያከናወናቸው ተግባራት ፊልሞችን ከማሳየት ሌላ ስለአሜሪካ መጻሕፍትን ለሚያትሙ ኢትዮጵያ ውስጥ ለሚገኙ ኤታሚ ድርጅቶች ዕርዳታ መስጠት ፤ የአሜሪካን ባሕል ልዩ ልዩ መልኮች የሚያሳውቁ ኤግዚቢሽኖች ማሳየት ፤ የአሜሪካን ባሕል የሚያስፋፉ የተለያዩ ጽሑፎች ማሠራጨት፣ በአዲስ አበባ ሬዲዮ የሚተላለፉ ፕሮግራሞች ማዘጋጀትና ከሀገሪቱ የባሕልና የትምህርት ኃላፊዎች ጋር የጠበቀ ግንኙነት መመሥረትና ለነሱም የመጻሕፍትና የመጽሔት ስጦታ ማድረግ ይገኙባቸዋል ። ኤ. እ. አ. በ1946 ከአሜሪካ መንግሥት ጋር በተደረገ ውል መሠረት በትራንስ ወርልድ አየር መንገድ የተቋቋመው የኢትዮጵያ አየር መንገድም በሀገሪቱ ውስጥ በተካሄደው «የዕውነት ዘመቻ» እንዲሳተፍ ተደርጎ ነበር ። ለምሳሌም ያህል እ. ኤ. አ. በ1952 «የኢትዮጵያ አየር መንገድ አውሮፕላን አብራሪዎች በአሜሪካ የማስታወቂያ አገልግሎት ተዘጋጅተው የታሸጉ ጽሑፎችን በልዩ ልዩ ሥፍራዎች ከአየር ላይ በትነዋል ። በዚህ ዓይነት ከተበተኑትም ውስጥ መጽሔቶች ፤ ፖስተሮች ፤ ፎቶግራፎች ፤ ካርታዎች፣ ፓምፍሌቶችና መጻሕፍት ይገኛሉ ።»[53]

«የዕውነት ዘመቻ» የተሰኘው የአሜሪካ ፕሮፓጋንዳ ሌሎችም ቅርጾች ነበሩት ። እ. ኤ. አ. ከ1955—60 ዘጠኝ የጃዝ ፤ ሌሎች የአሜሪካ ሙዚቃና የቲያትር ቡድኖች ኢትዮጵያን ጎብኝተዋል ። እ. ኤ. አ. ነሐምሌ 1 ፤ 1960 — ሰኔ 30 ፤ 1961 ባለው አጭር ጊዜ ውስጥ ዘጠኝ የአሜሪካ የአትሌቲክ ቡድኖች በኢትዮጵያና በሌሎች የአፍሪካ ሀገሮች ውስጥ ተዘዋውረዋል ። በአሜሪካው ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አባባል ፤ እነዚህ አትሌቶች «የአፍሪካ ወጣቶች ስለአሜሪካ የአትሌቲክስ ተቋሞችና የስፖርት ሰዎች ጥሩ አመለካከት እንዲኖራቸው ለማድረግ ችለዋል ።» አሜሪካ የባሕል ወረራ ከምታካሂድበት ዘዴዎች አንዱ ለጋ ወጣቶችን ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ወደአገሯ አስመጥታ (በአሜሪካ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የትምህርትና የባሕል ጉዳዮች ረዳት ሚኒስትር በነበረው በፊሊፕ ኮምብስ አባባል) «በአሜሪካ ቤተሰቦችና ኅብረተሰብ ውስጥ በጥንቃቄ የታቀደ ልምድ እንዲቀስሙ» ማድረግ ነበር ። እ. ኤ. አ. በ1960—61 የትምህርት ዓመት ሦስት ኢትዮጵያውያን ወጣቶች በአሜሪካ ፊልድ ሰርቪስ ፕሮግራም ለመሳተፍ ወደአሜሪካ መሄዳቸው በአሜሪካ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የወጣቶች ፕሮግራም በኢትዮጵያ ከተጀመረ ረጅም ጊዜ ያለፈው መሆኑን ያስረዳል ።[54] በተጨማሪም የአሜሪካ ኢምፔሪያሊስቶች አሜሪካ ተምረው ወደአገራቸው ከሚመለሱ ወጣቶች ጋር የተጠናከረ ግንኙነት በመመሥረት ጥቅማቸውን ለማስከበር ይጥራሉ ። ዌይን ሔይዝ እ. ኤ. አ. በ1961 በአሜሪካ ምክር ቤት ውስጥ የተናገራቸው የሚከተሉት ቃላቶች፣ የአሜሪካ ኢምፔሪያሊስቶች ይህን ተግባር በኢትዮጵያ ውስጥ እንዴትና ለምንስ ያካሂዱት እንደነበረ ይጠቁማል ።

«ባለፈው ሣምንት በአዲስ አበባ ውስጥ መገኘታችንን ምክንያት በማድረግ አምባሳደር ሪቻርድስ በፉልብራይት ዕርዳታ ወይም በዓለም አቀፍ ትብብር አስተዳደር ወይንም በወታደራዊ ፕሮግራም አማካኝነት በአሜሪካ ትምህርታቸውን የተከታተሉ ብዙ ኢትዮጵያውያንን በኢምባሲው ቀጥር ግቢ ግብዣ በማዘጋጀት ጠርቶ ነበር ። ሁኔታው እሱንም አስደነቀው ። እንደምገምተው በዚህ ግብዣ ላይ ከ 300 እስከ 400 ሰዎች ነበሩ ። አዲሲቱን ኢትዮጵያ ማየት ከፈለጋችሁ በግብዣው ላይ የነበሩን ሰዎች ማየት ነው ። . . . ከነዚህ ውስጥ ብዙዎቹ ወጣቶችና በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች ውስጥ የሚሠሩና ወደፊትም እነዚህን ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች የሚመሩ ናቸው ። አመራሩን የሚይዙበት ቀን መቼ እንደሆነ ብቻ በትክክል አይታወቅም ። ሌሎቹም በዩኒቨርሲቲ ውስጥ በማስተማር ተግባር ላይ የተሰማሩ ናቸው ። ዋናው ቁም ነገር አንድ ቀን ከፍተኛ ፍሬ ሊያፈራ የሚችል የጥቅም መተሳሰር በእነዚህ ሰዎችና በኛ መሀከል መኖሩ ነው ።»[55]

በኢትዮጵያ ውስጥ ያካሄደው «ፀረ ኮምዩኒስት ዘመቻ» ፍሬአማ መሆኑን ስለማመኑ የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እ. ኤ. አ. በ1951 ባቀረበው ዘገባ የሚከተለውን ገልጿል ።

«ከንጉሡና ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር የተደረገው የአሜሪካ የማስተወቂያና የት ምህርት ልውውጥ ፕሮግራም በንጉሡና በኢ ትዮጵያ መንግሥት ዘንድ ተቀባይነት እንዲ ኖረው ለማድረግ የታቀደው የመጀመሪያ ደረጃ እርምጃ ተሳክቷል ለማለት ይቻላል ። በአገሪቱ ውስጥ እየጨመረ የመጣውን የኮ ምዩኒስት ፕሮፓጋንዳ ለመቋቋም የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ከአሜሪካ የማስተወቂያና የትምህርት ልውውጥ ፕሮግራም እርዳታ የማግኘቱን አስፈላጊነት በይበልጥ እየተረ ዳው መጥቷል ።»[56]

ከዚህ በላይ የተገለጸው በአጠቃላይ የሚያሳየው የአሜሪካ መንግሥት ከኢት ዮጵያ ጋር የነበረውን የትምህርትና የባሕል ግንኙነት የተመለከተው ዓለም አቀፍ ኮም ዩኒዝምን ለመውጋት የዘረጋው ሰፊ ፕሮግ ራም አንድ አካል አድርጎ መሆኑን ነው ።

አሜሪካ ከኢትዮጵያ ጋር የነበራትን የትምህርት ግንኙነት ያቀደችው የኢምፔ ሪያሊስት ፍላጎቷን ለማርካት ቢሆንም በአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝምና ዘመናዊ ትም ህርትን በቀሰሙ ኢትዮጵያውያን መካከል ቅራኔዎች አልዳበሩም ማለት አይደለም ። በተለይም እ. ኤ. አ. ከ1960ዎቹ መጨረሻ ጀምሮ በአገር ውስጥና በውጭ አገር በሚ ኖሩ ኢትዮጵያውያን ተማሪዎች መካከል የፀረ ኢምፔሪያሊስት አመለካከት ማቆጥቆጥ ጀመረ ። በሰሜን አሜሪካ የኢትዮጵያ ተማ ሪዎች ማኅበር ልሣን በሆነ መጽሔት ውስጥ «ኢምፔሪያሊዝምና የብሔር አርነ ነት» በሚል ርዕስ እ. ኤ. አ. በ1971 የወጣ ጽሁፍ በኢትዮጵያውያን ወጣቶች መካከል ፀረ ኢምፔሪያሊዝም ምን ያህል እየተጠና ከረ እንደመጣ ይገልጻል ።

«የብሔራዊ አርነት ጥያቄ ኢምፔሪያ ሊዝም ከሚያስከትለው ችግር ጋር እጅግ የተሳሰረ ነው ። ዓለምን በቁጥጥሩ ሥር ለማ ዋል ዘዴ የቀየሰውና ወታደራዊ ኃይሉን በከ ፍተኛ ደረጃ አዳብሮ የሚገኘው ዓለም አቀፍ ኢምፔሪያሊዝም በአሁኑ ወቅት የብሔራዊ አርነት ትግሎች ቀንደኛ ጠላት ነው ። ኢም ፔሪያሊዝም ባይኖር ኖሮ በብዙ አገሮች ፤ ኢትዮጵያንም ጨምሮ ፤ የሚገኙ አሻንጉሊት መንግሥታት ዕድሜ በጣም አጭር ይሆን ነበር ። በቅርቡ በዶሚኒካን ሪፐብሊክ ፤ በኮ ንጎ ፤ በቦሊቪያ ፤ በላኦስ ፤ በካምቦዲያና በደቡብ ቪዬትናም የታዩት ሁኔታዎች የብሔ ራዊ አርነት እንቅስቃሴዎች ቀንደኛ ጠላት . . . የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም እንደሆነ በግልጽ አሳይተዋል ።

አብዮታዊ ለውጥ በኢትዮጵያ ሊካሄድ የሚችለው በፀረ ኢምፔሪያሊስት የትግል መድረክ ብቻ ነው ።»[57]

ይሁንና ከዚህ በላይ የተገለጸው ፤ የኢ ትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ ፀረ ኢምፔ ሪያሊስት አቋም ለመጀመሪያ ጊዜ ይፋ የወጣበት አይደለም ። የአሜሪካው ምክትል ፕሬዚዳንት ሀምፍሬ እ. ኤ. አ. በ1968 ኢትዮጵያን በጎበኙበት ጊዜ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ፕሬዚዳንት ጆንሰን ተሰቅሎ የሚታይበትን ምስል በማዘጋጀት መፈክሮች በማሰማትና የአሜሪካ ኢምፔ ሪያሊዝምን ተጻራሪ የሆኑ ጽሑፎችን በመ ያዝ ሰላማዊ ሰልፍ አድርገው አሜሪካ በቬ ዬትናም ውስጥ የተጫወተችውን ሚና ተቃ ውመዋል ። የልብስ ፋሺን ትርኢትን በመ ቃወም በዚያው ዓመት ያደረጉት ሰላማዊ ሰልፍም የኢምፔሪያሊዝምን የባሕል ወረ ራና ከዚሁ ጋር የተያያዘውን የኢትዮጵያን ያልተመጣጠነ ዕድገት በጉልህ የሚቃወም ነበር ። የልብስ ፋሺኑን ትርኢት በመቃወም ሰላማዊ ሰልፍ ካደረጉ በኋላም ተማሪዎቹ በአዲስ አበባ የአሜሪካ የማስታወቂያ አገልግሎትና ቤተመጻሕፍት ይገኙበት የነበረውን ሕንፃ መስታወት ሰባበሩ ። የውጭ አገር አስተማሪዎች ከሀገር እን ዲባረሩም ጠየቁ ። በተከታዩ ዓመት ማለ ትም በ1969 በተለይ የአሜሪካ የሰላም ጓድ አባላት ከሀገር እንዲወጡ የዩኒቨርሲቲ ና የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ጥያቄ አቀ ረቡ ። በተጨማሪም ፤ አዲስ አበባ የሚገ ኘውን የአሜሪካን የሰላም ጓድ ጽሕፈት ቤት በድንጋይ ከመደብደባቸውም በላይ በአሜ ሪካ ኤምባሲ ቅጥር ግቢ ውስጥ ቀላል ፈንጂ ወርውረዋል ።[58]

በ1970 መጀመሪያ ላይ ተማሪዎች የሰ ላም ጓድ አባሎችን ማርበድበዳቸው ከፍ ተኛ ደረጃ ላይ በመድረሱ አንድ የዚሁ ፕሮግራም ተሳታፊ በአሜሪካ ምክር ቤት ለሚይን ተወካይ ፤ ለማርጋሪት ቼዝ ስሚዝ የቅሬታ ደብዳቤ ላከ ።[59] ከዚያም በማከታ ተል በተለይ በትምህርት ቤቶች ውስጥ ያስተምሩ የነበሩ የሰላም ጓድ አባላት በብ ዛት ኢትዮጵያን ለቀቁ ።

ተማሪዎቹ የሰላም ጓድ ፕሮግራምን የተ መለከቱት ፤ ኃይለ ሥላሴን ሥልጣን ላይ ለማቆየትና ጥቅሙን ለማስከበር የአሜሪካ መንግሥት በኢትዮጵያ ውስጥ ከወሰዳቸው እርምጃዎች እንደ አንዱ አድርገው ነበር ።

ኒውዮርክ ታይምስ እ. ኤ. አ. በነሐሴ 1970 ባሰፈረው ጽሑፍ መሠረት ፤

«አንድ ተማሪ ከተለያዩ ት/ቤቶች የተውጣጡ ስድስት ተማሪዎችን በመወከል ለአሚሪካ ፕሮፌሰሮቿንና የዕርዳታ ፕሮግራሟን ከአገራችን ታስወጣ» ሲል ተናግሯል ። «የአሚሪካ ዕርዳታ ባይኖር ኖሮ ጠቅላላው ሥርዓት ከረዥም ጊዜ በፊት በፈራረሰ ነበር» ሲል አንድ የኢኮኖሚክስ ተማሪ ተናገረ ።

ዘግየት ብሎም በዚሁ ጋዜጣ የተሰጠ ዘገባ እንዲህ ይላ ፤

በአብዛኛው ሥር ነቀልነታቸው የሚነገርላቸው በአዲስ አበባ የሚገኙ የኢትዮጵያ ተማሪዎች የቃኘው ጣቢያን መኖር አጥብቀው በመቃወም «ቃኘው ይዘጋ» በማለት ትዕይንተ ሕዝብ አድርገዋል ። የኃይለ ሥላሴን ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ ዕድሜ ያራዘመው የቃኘው ጣቢያ መኖሩ መሆኑን ብዙ ተማሪዎች ያምናሉ ።

በአሜሪካ ውስጥ በነበሩ የኢትዮጵያ ተማሪዎችም የተደረጉ ሰላማዊ ሰልፎች የአሜሪካን መንግሥት ሳያሳስቡት እንዳልቀሩ ይገመታል ። የኃይለ ሥላሴን የአሜሪካ ጉብኝት በማስመልከት በዋሽንግተን እ. ኤ. አ. በ1969 ስለተደረገው ትዕይንተ ሕዝብ ኒውዮርክ ታይምስ እንዲህ ሲል ጽፏል ። «የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በዋሽንግተን ውስጥ በሚገኙ የውጭ አገር ኤምባሲዎች ላይ የሚደርሰውና ከጊዜ ወደጊዜ እየተባባሰ የመጣው አደጋ ያሳሰበው መሆኑን ገልጿል ። ይህንንም የገለጸው በቅርቡ በኢትዮጵያ ኤምባሲ ላይ ስለደረሰው ጉዳት የኢትዮጵያን መንግሥት ይቅርታ የጠየቀ መሆኑን ባስታወቀበት ጊዜ ነው» ። ጋዜጣውም ጽሑፉን በመቀጠል የአሜሪካ መንግሥት የኢትዮጵያ ተማሪዎች በኤምባሲው ላይ ላደረሱት ጉዳት ካሣ እንደሚከፍልና ቀደም ሲል የዋሽንግተን ፖሊስ ዋና አዛዥ የነበረውንና በጡረታ የተገለለውን ጀን ቢ. ሌይተንን «የውጭ አገር ዲፕሎማቲክ ተቋሞችን ደኅንነት በመጠበቅ ረገድ የሚገጥሙ ችግሮችን እንዲያጠና» እንደሰየመው ገልጿል ።[60]

ሰ. በኢትዮጵያ አብዮት ዋዜማ የአሜሪካ አምባገነንነት በኢትዮጵያ እየተዳከመ መምጣት

አሜሪካ በአብዮቱ ዋዜማ ከኃይለ ሥላሴ መንግሥት ጋር የነበራት ግንኙነት ይበልጥ እየተጠናከረ እንዳይሄድ ካደረጉት ምክንያቶች አንዱ ከዚህ በላይ የተገለጸው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ እየተጠናከረ መምጣት ነበር ለማለት ይቻላል።አብዮታችን በፈነዳም ጊዜ የአሜሪካ መንግሥት በቀጥታና በግልጽ ጣልቃ ከመግባት እንዲቆጠብ ካደረጉት ምክንያቶች አንዱ ይኸው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ የማይናቅ ደረጃ ላይ መድረስ እንደሆነ ይገመታል ። ይሁን እንጂ አብዮታችን እንደፈነዳ የአሜሪካ መንግሥት ከሽርኩ ከኃይለ ሥላሴ መንግሥት ጎን በመቆም በአብዮታችን ውስጥ ጣልቃ ገብነቱን ለማጠናከር ያላስቻሉት ሌሎች ዋና ዋና ምክንያቶችም ነበሩ ።

በኃይለ ሥላሴ መንግሥት ላይ የውስጥና የውጭ ግፊት እያየለ በመሄዱ ከአብዮታችን ፍንዳታ ቀደም ብሎ ለጥቂት ዓመታት አሜሪካ በኢትዮጵያ ውስጥ ታደርገው የነበረውን እንቅስቃሴ ወደማቀዝቀዙ አዘንብላ ነበር ። እ. ኤ. አ. በ1960 በአሜሪካ መንግሥትና በኃይለ ሥላሴ መንግሥት መካከል የተካሄደው የምስጢር ስምምነት በ1970 ይፋ በወጣ ጊዜ የአሜሪካን ምክር ቤትና ሌሎች አሜሪካውያንንም አስቆጥቶ ነበር ። አሜሪካ ለኢትዮጵያ የግዛት አንድነትና ለኃይለ ሥላሴና ለአገዛዙ የደህንነት ዋስትና የሰጠችበት ይህ ስምምነት[61] ለአሜሪካ ምክር ቤት እንኳ ሳይገለጽ ቆይቶ በ1970 በምክር ቤቱ ውስጥ የምክር ቤቱ አባላት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርና የመከላከያ ሚኒስቴር ባለሥልጣኖችን በጥያቄ ባፋጠጡበት ወቅት ሊገለጽ ቻለ ።

የዚህ ስምምነት ይፋ መውጣት በሁለቱ አገሮች መንግሥታት መካከል የነበረው ወዳጅነት እየተጠናከረ እንዳይሄድ አድርጎታል ። ለምሳሌ ስምምነቱ ይፋ በወጣበት ጊዜ የአርከንሳሱ ሴኔተር ፉልብራይት ስለዚሁ ስምምነት ሲናገር ፤ «በአሠራራችን ውስጥ በጣም ረቂቅ እና ጠለቅ ያለ ጉዳይ» ብሎታል ። ስምምነቱ በምስጢር የቆየው የኢትዮጵያ መንግሥት ጉዳዩ በምስጢር እንዲጠበቅ ስለፈለገ ነው ተብሎ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ባለሥልጣኖች በተነገረው ጊዜ «የአሜሪካን ሕዝብ ላለማሳወቅ በኢትዮጵያ ንጉሥ ሃሣብ እየተመራችሁ ናችሁ ። ይህ አሠራር አንዳንዶችን ስለዲሞክራሲ ሥርዓታችን አሠራር ከምናስበው ጋር አይጣጣምም» ሲል ሴኔተሩ ተናግሯል ። የሚዙሪው ሴኔተር ሳይሚንግተንም የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ስለኢትዮጵያ ደህንነት መጠበቅ የሚያገባው ከሆነ የአሜሪካ ሕዝብ ስለዚሁ ጉዳይ የማወቅ መብት አለው ፤ የሚል

ሃሣብ ሰነዘረ ። የኢትዮጵያና የአሜሪካ ግንኙነት «ብጥብጥ ባለበት አገር ውስጥ የአሜሪካን ወታደሮች እንደመላክ» ተደ ርጎ የሚቆጠር መሆኑን በመግለጽ አሥመራ የሚገኘው ቃኘው የተባለው የአሜሪካ መገ ናኛ ጣቢያ ተግባር በኦካባቢው ወደሚገኝ አንድ ደሴት ወይም ወደመርከብ እንዲዛ ወር ሃሳብ አቀረበ ። ሴኔተሩ በተጨማሪም ሲናገር ፤ «ሌላ ቪዬትናም ወይም ሌላ ካም ቦዲያ ፤ ወይም ሌላ ላኦስ ወይም ሌላ ኮርያ ከመቅጽበት ሲፈጠር ለማየት አልሻም»[62] ብሏል ።

የምስጢሩ ስምምነት ይፋ መውጣትና ፤ በአጠቃላይም የሁለቱ አገሮች የግንኙነት ባሕርይ በአሜሪካ የዜና ማሠራጫዎች ተተ ችቶበት ነበር ። ለምሳሌ ፤ ኒውዮርክ ታይ ምስ እ. ኤ. አ. ጥቅምት 26 ፤ 1970 በርዕሰ አንቀጹ እንደገለጸው፡ የምስጢር ስምምነቱ «ብዙ አሜሪካውያንን አስቆጥቷል ።» «የአ ሜሪካን ጦር በውጭ አገር ውስጥ ጣልቃ ሊያስገባ የሚችል ስምምነት በውል መልክ በግልጽ መታወቅና ለምክር ቤቱ ቀርቦ መጽደቅ ይገባዋል» ። አንድ ጆሴፍ ፎርድ የተባለ ሰው ለጋዜጣው አዘጋጅ በላከው ደብዳቤው «በኢትዮጵያ ውስጥ አዲስ ላኦስ መፈጠር» በሚል ርዕስ እንደሚከተለው ጽፏል ።

«በብዙ መንገዶች የአሜሪካ ወታደራዊ ጣልቃ ገብነት ኢትዮጵያን ከካምቦዲያ ፤ ከታይላንድ ወይም ከላኦስ ጋር ያመሳስላ ታል ። ምክንያቱም የአሜሪካን ጥቅም ብቻ የሚያስከብር የጦር ሠፈር በኢትዮጵያ ውስጥ በመኖሩና ፀረ ኮምዩኒስት ነው በሚል ሳቢያ ሕዝቡን በግፍና በአረመኔነት ለሚጨ ቁን መንግሥት በተለይ የመሣሪያ ዕርዳታ አሜሪካ መስጠቷ ነው ።»[63]

ስለዚህ በአንድ በኩል የአሜሪካ መን ግሥት በኢትዮጵያ ውስጥ የሚያደርገውን ጣልቃ ገብነት እንዲገታ የአሜሪካ ሕዝብ ፍላጐት ነበር ። በሌላ በኩል የኃይለ ሥላሴ መንግሥት ተጻራሪዎቹ እየተጠናከሩ በመ ምጣታቸው በርካታ ወታደራዊ ዕርዳታ ከአሜሪካ ፈለገ ። በተጨማሪም አሥመራ ይገኝ በነበረው የቃኘው ጣቢያ ያን ጊዜ በነበረው አቋም አሜሪካ እንድትገለገል በት የኤርትራ ተገንጣይ ቡድኖች ምቹ አላደረጉትም ። ለምሳሌ እ.ኤ.አ. በ1970 ጥቂት አሜሪካውያን የነጻነት በዓማቸውን ምክንያት በማድረግ ለሽርሽር ወጣ ባሉ በት ሥፍራ በተገንጣይ ቡድን አባላት ተይዘው ለጥቂት ሰዓት ያህል በቁጥጥር ሥር እንዲቆዩ ተደርጎ ነበር።በዚያው ዓመት ውስጥ አሥመራ ይገኝ የነበረው የአሜ ሪካ ቆንሲል በሌሎች ተገንጣይ ቡድን አባ ላት ተይዞ ገለጻ ተደርጎለት ተለቋል ። በሚ ቀጥለውም ዓመት አንድ አሜሪካዊ ከም ጽዋ ወደአሥመራ በመኪና ሲመጣ ተገ ድሏል ።[64]

በእነዚህና እነዚህን በመሳሰሉ ምክንያ ቶች የአሜሪካ መንግሥት ከኃይለ ሥላሴ መንግሥት ጋር የነበረው ግንኙነት የሚያ ስከትለውን ጉዳትና ጥቅም እንደገና መገ ምገምና ስለወደፊት ግንኙነቱ ውሣኔ ላይ መድረስ አስፈላጊ መሆኑን ተረዳ ። በዚህ መሠረት ጄኔራል ዊልያም ዌስትሞርላንድ ፤ የአሜሪካ ጦር ሠራዊት ኤታማዦር ሹምና በቬዬትናም የነበረው የአሜሪካ ጦር ኃይል የቀድሞው አዛዥ ፤ እንዲሁም ብሪጋዴር ጄኔራል ሮበርት ሜየር ፤ የአሜሪካ ስትራቴ ጂያዊ ግንኙነት ዕዝ አዛዥ ከኢትዮጵያ መን ግሥት ባለሥልጣኖች ጋር ለመወያየትና የቃኘው ጣቢያን ለመጎብኘት እ. ኤ. አ. በ1971 በተለያዩ ወቅቶች ወደ ኢትዮጵያ መጡ ። ከዚያም በኋላ እ. ኤ. አ. በጥቅምት 1973 ፤ የቃኘው ጣቢያ በሚቀጥለው ሐምሌ ማለትም ስለጣቢያው አጠቃቀም ሁለቱ መንግሥታት የተፈራረሙት ስምምነት ከማ ብቃቱ በፊት አራት ዓመት ቀደም ብሎ እንደሚዘጋ ተገለጸ ። ይህ ውሣኔ በተላለፈ በት ጊዜ የቃኘውን ጣቢያ አንዳንድ ተግባ ሮች የተሻሻሉ የሳተላይት መገናኛ ዘዴዎች የተኳቸው ከመሆናቸውም በላይ ከኢትዮ ጵያ ብዙም ባልራቀችና በሕንድ ውቅያ ኖስ ውስጥ በምትገኝ ፤ በእንግሊዝ ሥር ባለች «ዲያጐ ጋርሲያ» በምትባል ደሴት ላይ የአሜሪካ መንግሥት የመገናኛ ጣቢያ አቋቁሞ ነበር ። ይህም ጣቢያ ሥራውን የጀመረው የቃኘው ጣቢያ እንዲዘጋ ከመ ወሰኑ ጥቂት ወራት ቀደም ሲል እንደነበረ ተረጋግጧል ።[65]

በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚያደርገው ጣልቃ ገብነት የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም ያሳየው ይህ ጊዜያዊ ማፈግፈግ ኋላቀር አገሮች ከካፒታሊስት ብዝበዛ እንዲላቀቁ አመቺ ሁኔታን ሊፈጥር የሚችል የዘመኑን አንድ የካፒታሊዝም ዋና ቅራኔ የሚያሳይ ነው ። ይኸውም «ጨቋኝ መንግሥታትን በኋላ ቀር አገሮች በሥልጣን ለማቆየት የሚያስ ፈልገውና እያደገ የሚሄደው ወታደራዊ ጣልቃ ገብነት የሚያስከትለው የሰው እል ቂትና የኢኮኖሚ ወጪ በኢምፔሪያሊስት አገሮች ውስጥ ተቃውሞንና ብጥብጥን ሊያ ስነሳ መቻሉ ነው ።»[66]

ከላይ የተጠቀሰው የዓለም አቀፍ ካፒታ ሊዝም ቅራኔ የኢትዮጵያን አብዮት በሚ መለከት ረገድ ሊሠራ የቻለው አሜሪካ ከኃይለ ሥላሴ መንግሥት ጋር በነበራት ግንኙነት አንፃር ብቻ ሣይሆን በይበልጥም የኢትዮጵያ አብዮት የፈነዳው አሜሪካ የሐፍረት ካባዋን ተከናንባ ከቬትናም እንድትባረር ከተደረገ በኋላ ብዙም ሳይቆይ በመሆኑም ጭምር ነበር ። እንደሚታወ ቀው እ. ኤ. አ. በጥር ወር 1973 «የቬትናምን ጦርነት ለማቆምና ሰላምን በክብር ለማግኘት ተስማምቻለሁ» በማለት ኒክሰን አስታወቀ ። ይህም እ. ኤ. አ. ከ1961 ጀምሮ አሜሪካ በቬትናም ላይ ያካሄደችውን ቀጥታ የሆነ ወታደራዊ ጣልቃ ገብነት እንዲያበቃ አደረገ ።[67] ከዚያም በኋላ የአሜሪካ ባለሥልጣናት ወደ «አዲስ ቬትናም» በመቀየር ላይ ናት ብለው በተናገሩላት በኢትዮጵያ ውስጥ የአሜሪካ መንግሥት ጣልቃ ገብነቱን ለማጠናከር ሳይደፍር ቀረ

የቃኘው ጣቢያን ለመዝጋት ለተደረገው ውሣኔ ፤ ኢትዮጵያ ከአሜሪካና ከእሥራኤል ጋር ባላት የጠበቀ ግንኙነት ሳቢያ አንዳንድ ዓረብ አገሮች በኃይለ ሥላሴ መንግሥት ላይ ያሳደሩት ተጽእኖም አስተዋጽኦ እንዳደረገ ይገመታል ። ለምሳሌም እ. ኤ. አ. በግንቦት 1973 የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የተመሠረተበትን አሥረኛ ዓመት ምክንያት በማድረግ በአዲስ አበባ ተሰብስቦ ለነበረው የመሪዎች ጉባዔ ላይ የሊቢያ የማስታወቂያ ሚኒስትር አቡ ዛይድ ዖርዳ ፤ «ኢሻንጉሊቶች ከመካከላችን ባይኖሩ ኖሮ ቅኝ አገዛዝ አፍሪካን ምንም ሊያደርግ አይችልም ነበር ። . . . ኢትዮጵያ የእሥራኤላውያንና የአሜሪካውያን ተባባሪ ነች» በማለት ተናግሯል ። በተጨማሪም ሚኒስትሩ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ጽሕፈት ቤት ከአዲስ አበባ እንዲነሳ ቀደም ሲል ቀርቦ የነበረውን ጥያቄ በድጋሚ አንስቷል[68]። የቃኘው ጣቢያ እንዲዘጋ በተወሰነበት ወር ማለትም በጥቅምት 1973 ፤ የንጉሥ ሰለሞን ዘር ነኝ ይል የነበረው የኃይለ ሥላሴ መንግሥት ከእሥራኤል ጋር የነበረውን የዲፕሎማቲክ ግንኙነት ለማቋረጥ መገደዱ ይታወሳል ። ስለዚህ ለኤርትራ ተገንጣይ ቡድኖች ዋና ደጋፊ ከነበሩት የዓረብ መንግሥታት ጋር ግንኙነቱን ለማሻሻል የኃይለ ሥላሴ መንግሥት የነበረው ፍላጐት የቃኘው ጣቢያ እንዲዘጋ ከገፋፉት ምክንያቶች አንዱ ነበር ለማለት ይቻላል ። የሊቢያው መልእክተኛ የኃይለ ሥላሴን መንግሥት በይፋ ማውገዝ ፤ በኢኮኖሚም ሆነ በፖለቲካ ረገድ የኢትዮጵያን ኋላቀርነት ይበልጥ እየተረዱ በሄዱት በአፍሪካ መሪዎች መካከል አሜሪካ ለአፍሪካ የቀየሰችውን ፖሊሲ ለማስፋፋት ንጉሡ ሊረዳ የሚችልበት ጊዜ እያለፈ መሄዱን ይጠቁማል ። ይህም አብዮታችን እንደፈነዳ የአሜሪካ መንግሥት ዕድሜው እየገፋ ከሄደው ንጉሥ ጎን በይፋና በቀጥታ ለመቆም ላለመቻሉ እንደአንድ ዋና ምክንያት ሊቆጠር ይችላል ።

እ. ኤ. አ. በ1970ዎቹ መጀመሪያ ዓመታት ላይ ሶቪዬት ኅብረትንና የሕዝባዊት ቻይና ሪፐብሊክን ይበልጥ ለመቅረብ ኃይለ ሥላሴ ያደረገው ሙከራ አሜሪካን ያስኮረፈው ይመስላል ። ንጉሡ ይህን ሲያደርግ ዋና ዓላማው የሶሻሊስት ሀገሮች ለኤርትራ ተገንጣዮችና ለሶማሊያ ያደርጉ የነበረውን ቀጥተኛም ሆነ ተዘዋዋሪ ዕርዳታ እንዲያቋርጡ ማድረግ ነበር ። ቻይናም የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አባል ለመሆን ድጋፍ የምትሻበት ጊዜ ስለነበር የኃይለ ሥላሴን መንግሥት መቀራረብ መፈለግ አትጠላውም ነበር ። እንደሚታወሰው እ. ኤ. አ. በ1964 «በተባበሩት መንግሥታት ውስጥ የቻይናን ሕጋዊ መብቶች» እንደምትደግፍ ኢትዮጵያ ገልጻ ነበር ። ይሁንና በዚያን ጊዜ በኢትዮጵያ የነበረው የአሜሪካ አምባሳደር «ኢትዮጵያ ፤ ኮምዩኒስት ቻይናን ብታውቅ የአሜሪካ መንግሥት በጥብቅ እንደሚቃወም ለንጉሡ ገልጿ» ። ኢትዮጵያም ለሚቀጥሉት ስድስት ዓመታት የቻይናን ሕዝባዊ ሪፐብሊክ ሳታውቅ ቀረች ። እ. ኤ. አ. ኅዳር 24 ቀን 1970 ግን የቻይና ሕዝባዊ ሪፐብሊክ መንግሥት «መላውን የቻይና ሕዝብ የሚወክል ብቸኛ መንግሥት» መሆኑን አወቀች ። ሁለቱ መንግሥታትም የዲፕሎማቲክ ግንኙነት ለመመሥረትና አምባሳደሮች ለመለዋወጥ ተስማሙ ።[69] እ. ኤ. አ. በጥቅምት ወር 1971 ፤ ማለትም የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባኤ ቻይናን በአባልነት ከመቀበሉና ታይዋንን ከድርጅቱ ከማስወጣቱ ጥቂት ቀናት ቀደም ብሎ ኃይለ ሥላሴ ቻይናን በመጎብኘት ከቻይና መንግሥት ጋር የንግድና የኢኮኖሚ ዕርዳታ ስምምነት ተፈራረመ ።[70]

ከቻይና ጉብኝቱ ጥቂት ወራት ቀደም ብሎም ንጉሡ ሶቪዬት ኅብረትን ጎብኝቶ ነበር ። በጉብኝቱ መደምደሚያ ላይ የወጣው የጋራ መግለጫ ሁለቱ ሀገሮች ማንኛውንም የቅኝ አገዛዝና የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ በጋራ ለመታገል መወሰናቸውን ያትታል ። ሁለቱ አገሮች በቬትናም ላይ የሚደረገው የውጭ ጣልቃ ገብነት ያሳሰባቸው

መሆኑን በመጥቀስ የውጭ ኃይሎች ከአ ንዶ ቻይና እንዲወጡ ይጠይቃል ። በአካ ባቢው ያሉት ሀገሮች የወደፊት ዕድላቸውን በራሳቸው ለመወሰን ያላቸውን የማይገሰስ መብት ይደግፋል ።

የኃይለ ሥላሴ መንግሥት ከሶሻሊስት አገሮች ጋር የፈጠረው መቀራረብ የአሜ ሪካ ፖሊሲ አውጭዎችን ቅር ያሰኛቸው ለመሆኑ በአሜሪካ ምክር ቤት ውስጥ ሴኔ ተር ሳይሚንግተን ኃይለ ሥላሴ በሶቪዬት ኅብረት ያደረገውን ጉብኝት አስመልክቶ የተናገረውን መጥቀስ ይበቃል ።

« . . . በዓለም ዙሪያ ወግ ተብሎ የተያ ዘው ፤ ይህንንም ስናገር የምሬን ነው ፤ እስከ ተቻለ ድረስ እኛን ማለብና ስንነጥፍ ወደ ሌላዋ ላም መዞር ነው ።

ስለዚህ ንጉሠ ነገሥቱ (ኃይለ ሥላሴ) ለኢትዮጵያ ያደረግንለት ዕርዳታ ሳያረካው ቀርቶ በተጨማሪ ዕርዳታ ከሶቭዬት ህብረት. ለማግኘት ሞክሮ እንደሆን ብዬ ነው ።»[71]

ስለዚህ በአንድ በኩል ከአብዮታችን ፍንዳታ ቀደም ሲል ንጉሡ በዚህ ዓይነት ከሶሻሊስት አገሮች ጋር ለመቀራረብ ጥረት ሲያደርግ ፤ በሌላ በኩል ደግሞ በግብታዊ ነት የፈነዳው አብዮታችን ሶሻሊስታዊ ፈር ተከትሎ መጓዝ አለመጓዙ በመጀመሪያ ላይ ግልጽ አልነበረም ። እንዲያውም ኃይለ ሥላሴ ከሥልጣን ሲወርድ ዘውዳዊ አገዛዝ እንደማይሰረዝ በመነገሩ ከአገር ውጭ የነበ ረው አልጋ ወራሹ ሕገ መንግሥታዊ ንጉሥ ተብሎ በመሰየሙ[72] ማይምነትና ኋላ ቀር ባሕል በሰፈነባት በኢትዮጵያ ውስጥ ሥር ነቀል የሆነ ለውጥ ይካሄዳል ብለው የአሜ ሪካ ኢምፔሪያሊስቶች አላሰቡም ነበር ።

ይህ የአሜሪካ ኢምፔሪያሊስቶች በመ ጀመሪያ ጊዜ ስለኢትዮጵያ አብዮት ፍን ዳታና ሂደት የነበራቸው የተሳሳተ አስተ ሳሰብ ፤ በአጠቃላይም በአብዮታችን ዋዜማ የአሜሪካ አምባገነንነት በኢትዮጵያ እየተ ዳከመ መምጣት አብዮታችንን በጨቅላ ነቱ ወቅት ለመከላከልና ለአብዮቱም መጠ ናከር አመቺ ሁኔታን እንዲፈጠረ ይገመ ታል ። ይሁን እንጂ የኢምፔሪያሊዝምና የውስጥ ገዥ መደቦች ቅንጅት የሆነ ብዝ በዛና ጭቆና ያስከተለው አብዮታችን የሶሻ ሊስቱን ፈለግ የሚከተል መሆኑ ይበልጥ እየተገለጸላቸው በመጣ ቁጥር ኢምፔሪያ ሊስቶች ደባ መሸረባቸውን ሲያባብሱ ቆይ ተዋል ። ወደፊትም ይተኙልናል የሚል እምነት ሊኖረን አይችልም ። አሜሪካ በቅ ድመ አብዮት ኢትዮጵያ ታካሂደው የነበረ ውን የኢምፔሪያሊስት ተግባር በመረዳት ወደፊት ከአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም ጋር ለሚደረግ ትግል የሚረዳ ትምህርት ለመ ቅሰም በጥቂቱም ቢሆን ካስቻለች ይህች ጽሑፍ ዓላማዋን መትታለች ።

የግርጌ ማስታወሻ

1. US Congress, Senate committee on foreign relations, *US Security Agreements and Commitments Abroad: Ethiopia*, Hearings before a sub-committee on US Security Agreements and Commitemnts Abroad of the committee on Foreign Relations, 91st Cong., 2nd sess., part 8, June 1, 1970 (Washington, 1970), p. 1954.
2. *New York Times*, August 28, 1970, p. 6.
3. US Congress, House, *Foreign Assistance and Related Agencies Appropriations for* 1976, 94th Cong., 1st sess., part 4, 1976, p. 339.
4. T.N. Dupuy and Wendell Blanchard, *Almanac of World Military Power*, 2nd ed., (New York, 1972), p. 208.
5. *New York Times*, August 28, 1970, p. 6
6. *Keesing's Contemporary Archives*, xx (1974), p. 26421
7. *Ethiopian Herald*, April 24, 1977, pp. 1, 4.
8. US Congress, House, *Foreign Assistance and Related Agencies Appropriations for* 1966, 89th Cong., 1st sess., 1965, p. 274.
9. John H. Spencer, „Prepared Statement of John H. Spencer'', US Congress Senate, Hearings before the sub-committee on African Affairs of the Committee on Foreign Relations, *United States Relations with Ethiopia and the Horn of Africa*, 94th Cong., 2nd sess., 1976, p.26.
10. US Congress, *Congressional Record* 100: 7356-58.
11. *Facts on File*, XI (1951), p. 153; XII (1952), pp. 22, 77; XIII (1953), p. 178.
12. *Ibid.*, XX (1960), pp. 254-55; Peter Schwab, *Ethiopia and Haile Selassie*, (New York: Facts on File, 1972) p. 105.
13. US Congress, Senate, *US Security Agreements and Commitments Abroad: Ethiopia*, p. 1938. Stockholm International Peace Research Institute (SIPRI), *Arms Trade Registers: Arms Trade with the Third World* (Cambridge, Mass., 1974), p. 74.
14. *Facts on File*, XX (1960), pp. 355-56.

15. *New York Times*, April 2, 1957, P. ME-6 (P. ME-1 follows P. 16); Dan Hofstadter, ed., *Egypt and Nasser*, Vol I, 1952 - 56 (New York, 1973), pp. 124-25; Michael Adams, ed., *Middle East: A Handbook* (New York, 1971), p. 326.

16. *Keesing's Contemporary Archives*,X (1955 -56), pp. 15049, 15125-27; *Facts On File*, XVII (1957), p. 79.

17. *Keesing's Contemporary Archives*, XI (1957-58), pp. 15305-306, 15417, 15419.

18. *New York Times*, February 16, 1957, p. 1; February 18, 1957, p. 4, *Keesing's Contemporary Archives*, XI (1957-58), pp. 15553, 15655.

19. *New York Times*, July 28, 1935, Section 4, p. 5; March 14, 1964, p. 22. *Facts on File*, XI (1957-58), p. 147. *Keesing's Contemporary Archives*, XIV (1963-64), p. 19467.

20. US Congress, House, *Foreign Assistance And Related Agencies Appropriations for* 1966, 89th Cong., 1st sess., 1965, p. 425.

21. US Congress, Senate, *US Security Agreements and Commitments Abroad*: *Ethiopia* p. 1883.

22. *Keesing's Contemporary Archives*, XIII (1961-62), pp. 17909, 18479, 18734.

23. *Facts on File*, XIX (1959), p. 233.

24. *Keesing's Contemporary Archives*, XIV (1963-64), pp. 19464-65.

25. Government of Ethiopia, *Second Five Year Development Plan* 1963-67 (Addis Ababa, 1962), p. 10.

26. *Negarit Gazeta*, Nos. 6 (1950), 51 (1963)' 242 (1966).

27. Exchange of Notes between Cordell Hull, US Secretary of State and Yilma Deressa, Ethiopian Minister of State, *Treaties and other International Agreements of the United States of America*, 1776-1949, VII (Washington, 1971), pp. 671-73. "Mutual Defense Assistance Agreement between the Government of the United States and the Imperial EthiopianGovernment," May 22, 1953, US Department of State, *Treaties and other International Agreements of the United States of America*: 1953, Vol. IV, Part I (Washington, 1955), pp. 422-26.

28. *Facts on File*, XI (1951), p. 306.

29. "Treaty of Amity and Economic Relations between the United States and the Imperial Ethiopian Government" and exchange of notes between J.Rives Childs, American Ambassador to Ethiopia and Aklilu Habte Wold, Ethiopian minister of Foreign Affairs, September 7, 1951, *Treaties and other International Agreements of the United States of America*: 1953, Vol IV, Part II, pp. 2136-47, 2170-73.

30. US Congress, Senate, Removal of Injunction of Security, 93rd Cong., 1st sess., January 26, 1973, *Congressional Record* 119:2201.

31. "Investment Guranties," signed between the United States and Ethiopia on August 3, 1962, US Department of State, *Treaties and Other International Agreements of the United States of America*: 1962, Vol. XIII, Part 2, pp. 1856-59. "Investment Guaranties Agreement Amending the Agreement of August 3, 1962," signed between the two governments on March 17, 1967 and March 8, 1968, *Ibid*: 1968, Vol XIX, Part 4, pp. 4725-27.

32. IMF, *Direction of Trade*, Various issues

33. Ethiopia, Ministry of Finance, *Public Sector External Debt December* 31, 1974, pp. ii - iii, 18.

34. US Department of State, *Communist Economic Policy in the Less Developed Areas* (Washington, 1960), 27-28.

35. Ethiopia, Ministry of Finance, *Public Sector External Debt, December* 31, 1974; US Congress, House, *Foreign Operations Appropriations for* 1963, 87th Cong., 2nd sess., part 2, 1962, pp. 701-2.

36. US Agency for International Development, *United States Overseas Loans and Grants and Assistance from International Organizations*: Obligations and Loans Authorizations, July 1, 1945 to June 30, 1972 (Washington, 1973), pp. 84, 93. US Department of Defense, *Foreign Military Sales and Military Assistance Facts* (Washington, 1977), p. 32. US Central Intelligence Agency, *Handbook of Economic Statistics* 1975 (Washington, 1975), p. 64. Nancy Stein and Mike Klare, "Police Aid for Tyrants," Steve Weissman, ed., *Trojan Horse*: Radical Look at Foreign Aid (Polo Alto, Calif., 1974; rev. 1975 ed.), p. 234.

37. U.S. Technical Cooperation Administration Mission to Ethiopia, "Work of Point Four in Ethiopia," Special Issue, *Ethiopia Observer*, III (Feb. 1959), 4-5. *New York Times*, Sept. 14, 1950, p. 47; January 29, 1971, p. 60.

38. US Congress, House, *Foreign Operations Appropriations & Foreign Assistance and Related Agencies Appropriations*, Various years. Ethiopian Government, *Third Five Year Development Plan* 1968-73, pp. 111-13, *New York Times*, February 7, 1960, p. 6.

39. "The Work of Point Four in Ethiopia," p. 28.

40. *Haile Selassie I University General Catalogue* 1973-75 (Addis Ababa, 1973), pp. 285-315.

41. *New York Times*, September 22, 1962, p. 8. US Congress, House, *Foreign Assistance and Related Agencies Appropriations*, various issues.

42. Teshome Wagaw, "Access to Haile Selassie I University" *Ethiopia Observer*, XIV (1971), No. 1, p. 43. Theodore M. Vestal, "Peace Corps in Ethiopia", *Ethiopia Observer*, IX (1965), No. 1, pp. 16, 22.

43. International Association of University Professors and Lecturers (IAUPL) *Recruitment and Training of University Teachers* (Ghent, Belgium: IAUPL, 1967), p. 142.

44. A.H. ter weele, "Financing of Education in Ethiopia", (Addis Ababa: Ministry of Education and Fine Arts, 1972), (Mimeographed), annex III-G.

45. US Congress, House, *Foreign Assistance and Related Agencies Appropriations for* 1972, 92nd Cong., 1st sess., part 2, 1971, p. 17.

46. Institution of International Education, *Open Doors* 1960 (New York, 1960), p. 23, *Open Doors* 1964, pp. 16-17; *Open Doors* 1969, pp. 22-23. US Department of State, *International Educational, Cultural and Related Activities for African Countries South of the Sahara* (Washington, 1961), p. 39; US Agency for International Development, *Operations Report*, Fiscal Year 1972 ((Washington, 1973), p. 105. Central Statistical office, *Ethiopia: Statistical Abstract* 1976, p. 242.

47. "The Work of Point Four in Ethiopia," p. 28; US Department of State, International Educational Exchange Program, *12th Semi-Annual Report* (Washington, 1954), p. 8.

48. US Department of State, *American Foreign Policy* 1950-1955, Basic Documents (Washington, 1957), pp. 3163-65.

49. , International Information and Exchange Program, *5th Semi-Annual Report of the Secretary of State to Congress* (Washington, 1951), pp. 1, 29.

50. US Congress, House, *Mutual Educational and Cultural Exchange Act of* 1961, 87th Cong., 1st Sess., 1961, p. 212.

51. *Keesing's Contemporary Archives*, XI (1957-58), p. 15553.

52. US Department of State, *Launching the Campaign of Truth*, 6th Semi-Annual Report of the Secretary of State to Congress on the International and Educational Exchange Program (Washington, 1951), pp. 59, 61; *Waging the Truth Campaign*, 8th Semi-Annual Report (Washington, 1952), p. 46.

53. US Department of State, *International Educational, Cultural and Related Activities for African Countries South of the Sahara*, pp. 96-99. *Report of the Secretary of State to Congress on the International Information and Educational Exchange Program*, 9th Semi-annual (Washington, 1953), p. 15.

54. *International Educational, Cultural and Related Activities for African Countries South of the Sahara*, pp. 95, 98. US Department of State, Education and Cultural Exchange Program, *Annual Report to Congress*, 1961 (Washington, 1962), p. 17. US Congress, House, *Hearings on Mutual Educational and Cultural Exchange Act of* 1961, 87th Cong., 1st sess., 1961, p. 71.

55. *Ibid.*, p. 70

56. US Department of State, *Launching the Campaign of Truth*, 7th Semi-Annual Report (Washington, 1952), p. 33.

57. Ethiopian Students Union of North America (ESUNA), *Chanllenge*, 2 (Jan. 1971), p. 2.

58. *New York Times*, January 7, 1968, pp. 1,10; April 1,1969, p.12; *Times* (London), April 4,1968, p. 5; *Facts on File*, 29 (1969), pp. 173, 291.

59. *Ibid.*, 30 (1970). p. 42.

60. *New York Times*, August 31, 1970, p. 12; *Ibid.*, August 28, 1970, *p.* 4; *Ibid.*, July 9, 1969, p. 6.

61. US Congress, Senate, *US Security Agreements and Commitments Abroad: Ethiopia* 91st Cong., 2nd sess., Part 8, June 1, 1970, pp. 1885, 1897-1919; *Facts on File*, XXX (1970), p. 749.

62. US Congress, Senate. *US Security Agreements and Commitmnts Abroad: Ethiopia* pp. 1888 - 1942.

63. *New York Times*, October 26, 1970, p. 36., January 11, 1971, p. 30.

64. US Congress, House, *US Policy and Request for Sale of Arms to Ethiopia*, 94th Cong., 1st Sess., March 5, 1975 (Washington, 1974), pp. 65-66.

65. *New York Times*; February 4; 1971; p. 13; March 17; 1971; p. 16. *Facts on File*; XXXIII (1973), p. 952; XXXIV (1974), p. 80.

66. Thomas E. Weisskopf, "Capitalism, Under-development and the Future of Poor Countries," Jagdish N. Bhagwati,

ed., *Economics and World Order from the 1970's to the 1990's*, (New York: Free Press Division of MaCmillan Publishing Co., 1972), p. 64.

67. *Keesing's Contemporary Archives*, XIX (1973), pp. 25781, 25790.

68. *Ibid.*, p. 25955.

69. *Ibid.*, XIV (1963-64), p. 20064, *Facts on File*, XXX (1970), pp. 919-20.

70. *Ibid.*, XXXI (1971), p. 826; *Keesing's Contemporary Archives*, XVIII (1971-72,) p. 24963.

71. US Congress, Senate, *US Security Agreements and Commitments Abroad*: *Ethiopia*, pp. 1193-95, 1890.

72. *Negarit Gazeta*, No. 1 of September 12, 1974.

73. *Ethiopian Herald*, December 21, 1974, p. 1